

የኖርዌዩ ወጣት
የጥላቻ ማኅደር

ፕሮፌሰር መስፍን
ወ/ማርያም
3


12
የመለስ ዲስኩር
ግዝፈትና
ግድፈት

አክመል ነጋሽ
(የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት
ሲኒየር ኤዲተር)



የካድሬው
የፍቅር
ደብዳቤ 3

አቤ ቶኪቻው
12





ቅፅ 5 ቁጥር 184 አርብ ሚያዝያ 12 2004 ዓ.ም www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia ዋጋ 7.00 ብር

# እስክንድር ነጋን ሳስበው ሳስበው ...፩ 5



# ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ለውሳኔ ተቀጠረ

- አቃቤ ሕግ በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ተጨማሪ አቤቱታ አቀረበ

13


በጉራፈርዳ ወረዳ የተፈናቃይ ቤቶች በካድሬዎች መቃጠላቸውን መኢአድ ገለፀ
- አንድ ተፈናቃይም ታርዶ ተገኝቷል 15

አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ 5 ሚሊዮን ብር ተዘረፈ 15

መዐሕድና ኢአዴድ የአርሶ አደሮችን መፈናቀል ተቃወሙ 15

ቻይናዊውን የገደለው ኢትዮጵያዊ ተፈረደበት 15

የመድረክ ከየት ወዴትነት 2

ዜጎችን ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ የማባረር ሂደት ከህገ-መንግስቱ አንፃር 7

የፕ/ር ‹‹አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ››ን በጨረፍታ 8

‹‹ወጣት አደረጃጀቶች ከወረቀት በዘለለ መልኩ ነፃነታችን ይከበር›› 4

# የመድረክ ከየት ወዴትነት



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ልክ የዛሬ ሶስት ዓመት በኢትዮጵያ የፖለቲካ አደባባይ ግዙፍ ስም ያላቸው ፖለቲከኞች የሀገሪቱ ፖለቲካ በድህ-97 ከገጠመው ዕግዳት ስለማውጣት ይወያያሉ:: የአስራ ስድስት አመታት ብረታዊ ትግልን እና የስድስት ዓመታት እስርን ያሳለፉት አቶ ስዬ አብርሃ፣ የትግል ጓዳቸው ገብሩ አስራት፣ ለዘብተኛው የቀድሞው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና ብዙውን የፖለቲካ ዘመናቸውን የከሸፉ ህብረቶችን በመምራትና በብሔር እና ህብረ-ብሔራዊ ፖለቲካ መሀከል ሲንዠዋዠው የከረሙት ፕ/ር በየነ ጴጥሮስን የያዘው ይሄ ስብስብ መድረክ የተባለ ፎረምን እንዳቋቋመ ተናገረ:: ከስምንት ወራት በላይ በፈጀ ‹‹ጥልቅ›› ውይይት እና ድርድር በኋላም ባልተብራሩ ሀሳቦች የተሞላውን ‹‹መለስተኛ ፕሮግራም›› አረቀቁ:: የቀድሞ የሥርዓቱን አርክቴክቶች እና የተቃውሞ ፖለቲካው ወካይ ስብዕናዎችን ማካተቱ በውስጥም በውጪም ያሉ የፖለቲካው ተከታታዮች ፎረሙን በጉጉት እንዲጠብቁት አድርጓቸዋል:: በተለይም የጠንካራ ተለዋጭ የፖለቲካ ፓርቲን አለመኖር በመጥቀስ ለኢህአዴግ የግማሽ-ልብ ድጋፍ በመስጠት ይተቹ ለነበሩት ምዕራባውያን መድረኩ እኒህን መሰል ልሂቃንን ይዞ መምጣቱ ችላ ሊሉት እንደማይገባ ስብስብ /A force to reckon with/ እንዲቆጥሩ አስችሏቸዋል:: መድረክ ይህን ያህል ከፍ ያለ ግምት ቢሰጠውም በምርጫ 2002 የገጠመው ከባድ ተሸናፊነት እና ከዛ በቀጠሉት ዓመታት የተጠበቀውን ያህል ለመንቀሳቀስ አለመሞከሩ ስለፎረሙ እንደገና ለመነጋገር የተሰጠው ጊዜ በቂ ይመስላል::

አሁን መድረኩ ከተመሰረተ ሶስት ዓመት ሊሞላው ነው:: በእነዚህ ዓመታት የመስራቾቹም ሆነ የነገሩ ተንታኞች የሰጡትን የቢሆን ግምቶች ያህል እየሰራ ላለመሆኑ ፍትህ ያነጋገረቻቸው የመድረኩ አባላት ተቀራራቢ ዕይታ አላቸው:: ከዚህ መንፈስ አንፃር የፎረሙን ከየት ወዴትነት በከፊልም ቢሆን ማየት አግባብ ይመስላል::

### የመድረክ ቅርቃር

ሰኔ 7 ቀን 2001 ዓ.ም ወደ ፖለቲካው ተዋስኦ የመጣውን የመድረክ መለስተኛ ፕሮግራምን በተመለከተ የተሰጡ አስተያየቶች ቅንጅቱን የግራ-ዘመሞች ስብስብ አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው:: መድረክን ለዚህ መሰል ትችቶች እንዲጋለጥ ያደረገው የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከአራት አስርታት በላይ ሲነቀንቀው የቆየውን ‹‹የብሔር ጥያቄ›› አስመልክቶ በፕሮግራሙ ላይ የሰፈሩ ሀሳቦች ናቸው:: የፕሮግራሙ አንቀፅ 6 ስለብሄር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብት አከባበር ያትታል:: ‹‹የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ማንነታቸው የታወቀ እና እኩልነታቸው የተከበረ ይሆናል›› ከሚለው የፎረሙ አቋም በተጨማሪ በፕሮግራሙ ውስጥ ‹‹ብሔር›› እና ‹‹ብሔረሰቦች›› የሚሉ ከባባድ ቃላትን ማግኘት አስቸጋሪ አይደለም:: መድረኩ ‹‹መገንጠልን አልደግፍም›› ቢልም የተጠቀሱትን ከግራ-ዘመምነት የሚነሱ ፖለቲካዊ ጭብጦችን እያነሱ መገንጠልን መቃወም በቅራኔ ውስጥ መቀርቀር እንደሆነ ብዙ የፎረሙ ተከታታዮች መድረኩ በተመሰረተ ማግስት ሲከራከሩ ሰንብተዋል:: ሰማኸኝ ጋሹ የተባሉ ፀሐፊ የብሔርና ብሔረሰቦችን መብት አስከብራለሁ በማለትና መገንጠልን በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ በመቀበል መሀከል የማይበጠስ ቀጥተኛ ትስስሮሽ ስለመኖሩ አጥብቀው ይሟገታሉ:: እነዚህ መብቶች ሊከበሩ የሚችሉት የራስን እድል በራስ የመወሰንን ግራ-ዘመም አስተምህሮ በምልዕት ከመቀበል በመነሳት ነው:: ፎረሙ ከዚህ መሰል ቅርቃር ውስጥ እንዲወድቅ የተገደደበት መነሻ ግልፅ ነው:: “Marxism and the national question” በሚለው ድርሳኑ ጆሴፍ ስታሊን ለቃሉ ‹‹ብሐር ማለት ታሪካዊ ወጥነት ያለው ወጥ ቡድን ሲሆን በጋራ ባህል የሚገለጥ የጋራ ቋንቋ፣ መልካዓ-ምድር፣ ኢኮኖሚያዊ ህልውና እና ሰነ-ልቦናዊ መደላደል የኖረዋል›› የሚል ብያኔ ይሰጣል:: መድረክ በፕሮግራሙ ብሔር የሚለውን ቃል ሲጠቀም ከዚህ የስታሊን ትርጓሜ ምን ያህል እንደሚርቅ አላብራራም:: አቶ ሰማኸኝ “Is Mederk against secession clause?” በሚለው ፅሁፋቸው ይህን መሰሉ የመድረኩ ግራ-ገብነት የመገንጠልን ሃይለ-ሀሳብ በዘወርዋራ መቀበሉን ያሳያል ሲሉ ይከራከራሉ:: ከመድረክ መስራቾች አንዱ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ አሁን በገበያ ላይ ለሌለችው አንድ የፖለቲካ መጽሔት ‹‹የኦሮሞን መገንጠል ባልደግፍም የመገንጠልን በህገ-መንግስት ውስጥ መካተት እቀበላለሁ›› ማለታቸው እና በጉዳዩ ላይ ፍትህ ጋዜጣ ያነጋገረቻቸው የአረናው ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራት ፓርቲያቸው መገንጠልን በፕሮግራሙ ውስጥ አካትቶ የነበረ ሲሆንም በፓርቲው ሁለተኛ ጉባኤው ላይ አንቀፅ እንዲወጣ መወሰኑ መግለፃቸው ይህን ትችት መሰረት አልባ እንዳይሆን ያደርገዋል:: ከእርሳቸው ሙግት በተቀራረበ ፕ/ር መሳይ ከበደ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ዘውግ / Ethnic/ ከማለት ይልቅ ብሔር የሚለውን ቃል ለመጠቀም መሞከር የመድረኩ ልሂቃን ግራ-ዘመም ፖለቲካዊ እምነቶቻቸውን ለመሻገር መቸገራቸውን እንደሚጠቁም “On the right to self-determination” በሚለው ፅሁፋቸው ይጠቅሳሉ:: ለሁለቱም ሆነ ለሌሎች ፀሐፊዎች የብሔሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን ከመገንጠል መብት ለይቶ ብቻውን መውሰድ ፖለቲካዊ ተጣጣፊነት ነው እንዲሉ ያስቻላቸው ሌላው መነሻ የጉዳዮቹ ተንታኝ የሆነው ስታሊን ሀሳቦቹን ያስተሳሰረበት ሙግት ነው:: ስታሊን ከላይ በተጠቀሰው ስራው እንደሚለው ‹‹ለብሔሮች የሚሰጥ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እኒህ ብሔሮች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር ፌደራላዊ ስርዓት የመመስረትም ሆነ ከስርዓቱ የመገንጠል መብትን ያካትታል::›› የመድረኩ ፕሮግራምም ሆነ የፎረሙ መስራቾች በእነዚህ ሀሳቦች ላይ ያሏቸውን አቋሞች ሲያብራሩ አልተስተዋለም:: ፎረሙ የኢትዮጵያን ያለመበታተን /In divisibility/ እንደሚቀበል በፕሮግራሙ ላይ ቢያስቀምጥም ከላይ የተባለውን ዓይነት ፖለቲካዊ አቋም መያዝ የሀገሪቱን አንድነት በቅድመ-ሁኔታ /Conditional unity/ ላይ የተመሰረተ አድርጎ መመልከትን ሊያስከትል ይችላል::

ከዚህ ጋር ተያይዞ መድረኩ ላይ የሚቀርበው ትችት እንደ ኢህአዴግ ሁሉ ፎረሙ መከወን ካልቻለው የብሔር ብሔረሰብ ትርጓሜ ጋር ይያያዛል:: መድረኩ እነዚህን ቃላት በተደጋጋሚ የመጠቀሙን ያህል በሀገሪቱ ውስጥ ማን ብሔር፣ ብሔረሰብ አልያም ህዝብ ተብሎ እንደሚጠራም ሆነ ይህን ስያሜ ለአንድ የማህበረሰብ ክፍል ለመስጠት ምን ዓይነት የማህበረ-ፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ መበየኛዎችን እንደሚጠቀም አላስቀመጠም:: አቶ ገብሩ አስራት በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የሉም ብሎ ማመን ሀገሪቱን ወደ ጥፋት እንድታመራ ያደርጋታል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል:: ‹‹ዘውግ የሚለውን አንቀበልም›› ሲሉ ፈርጠም ባለ አንደበት መልሰዋል በዘውግ ፖለቲካ ላይ የሚፅፉ መምህራን ኢህአዴግን አብዝተው የሚወቅሱበት እኒህ መሰል ትችቶችን መድረኩ ሊሻገር አለመቻሉ ቀጣይ እንቅስቃሴዎቹን የሚወስኑ ሁነቶች ይመስላሉ::

### የተመቻመቸው ምንድን ነው?

ኢህአዴግ በትረ መንግስቱን ከያዘ ወዲህ የሀገሪቱን መንግስታዊ አወቃቀር ቋንቋ-ተኮር ፌደራሊዝም ለማድረግ ሞክሯል:: ይህ የፌደራሊዝም ቅርፅ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ፖለቲካዊ ዕግዳትን / Impasse/ ይፈታል ብለው ያምኑ የነበሩ የፓርቲው ልሂቃን የ1993ቱን የህወሓት መሰንጠቅ ተከትሎ ወደ ተቃውሞ ጎራ ተቀላቅለዋል:: ከአቶ ስዬ አብርሃ ውጪ በአረና ትግራይ ፓርቲ በኩል ወደ ፎርሙ የመጡት እነዚህ የስርዓቱ የቀድሞ አርክቴክቶች መድረኩ የፌደራሊዝምን ቅርፅ በተመለከተ ከሌሎቹ መድረኩ ውስጥ ካሉት ዘውግ ብሔርተኞች በተጨማሪ መሀከለኛ መንገድ ላይ እንዲቆም እንዳደረጉት የፎርሙ ታዛቢዎች ይናገራሉ::

ላለፉት ሁለት አስርታት የተሞከረውን ፌደራሊዝም በተመለከተ የሀገሪቱ የፖለቲካ ልሂቃን ያላቸውን ዕይታ በሶስት ክፍሎ ማየት እንደሚቻል ፕ/ር ኪዳኔ መንግስት-አብ ይናገራሉ:: የመጀመሪያው ሀገሪቱ በአሀዳዊ መንግስት መተዳደር አለባት ብሎ የሚያምን አሁን ድምፁ ብዙ የማይሰማ የትኛውንም ዓይነት የፌደራል አወቃቀር የማይቀበል ዕይታ ነው:: ፕ/ር ማዕምር መናሰማይ ይህን ሙግት የቀላቃይነት/የመለንቀጥ (Assimilation) ሀቲት ሲሉ ይጠሩታል:: እንደ ዶ/ር ማዕምር ይህ ሙግት በኢትዮጵያ ዘመናዊ መንግስት ምስረታ የተከሰቱ ግጭቶችን ለተለያዩ ጠርዘኛ ትንታኔዎች ክፍት ያደርጋል:: ሁለተኛው እና ኢትዮጵያን ልዕለ ዘውግ-ብሄር አድርጎ የሚቆጥራት የኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ምልከታ ሲሆን ቋንቋ-ተኮር ፌደራሊዝምን አብዝቶ ሲተች ይስተዋላል:: በአቋምም መልክዕ-ምድራዊ ፌደራሊዝምን ያቀነቅናል:: ዘውግ ተኮር ፖለቲካዊ ስርዓት ሀገሪቱን በጊዜ ሂደት ይበታትናታል ከሚለው ሙግቱ በተጨማሪ ‹‹የብሔር ጥያቄ›› መኖሩን ለመቀበል እንደሚቸገር ፕ/ር ኪዳኔ “Identity politics, Democratization and state building in Ethiopia’s federal arrangement” በሚለው ጥናታዊ ስራቸው ያወሳሉ:: ይህን የፖለቲከ-ታሪክ ተጋቦት የሚንተራሰውን ሙግት ዶ/ር ማዕምር የአዋሐጆች /Integrationist/ መሟገቻ እንደሆነ ይጠቅሳሉ:: “Historical wounds and democracy” በሚለው ፅሁፋቸው ዶ/ር ማዕምር ለክልላዊ የስልጣን ነፃነት እና ዴሞክራሲያዉ መለዮ ላለው አንድነት የሚተጋ አድርገው ያቀርቡታል:: አሁን በፖለቲካው ገበያ ላይ ካሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሀከል እንደ ኢዴፓ፣ መኢአድና አንድነት ያሉት በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ያርፋሉ:: ፕ/ር ማሪያን ኦታዌይ ሶስተኛውን የፌደራሊዝም ተቀናቃኝ አቋም የቋንቋ-ተኮሩ ፌደራሊዝም የተገብሮት ፍፅምና ላይ የሚነሳ ልዝብ ተቃውሞ አድርገው ያስቡታል:: ፕ/ር ኦታዌይ “Democratization and ethnic nationalism: African and eastern European experiences” በሚለው ድርሳናቸው እንደሚያትቱት የዚህኛው የፖለቲካ ልሂቃን ስብስብ የቅሬታ መነሾ የኢህአዴጉ ፌደራሊዝም ችግር በአግባቡ እንዳይተገበር የገዢው ፓርቲ ስልጣን ጠቅላይነት እንቅፋት ሆኗል የሚል ነው:: ይኸኛው ዕይታ በዚህ የተቀናቃኝነት መንፈስ እና በ‹‹ብሔር ጥያቄ›› ቀዳሚ የፖለቲካ ቅራኔ የመሆኑ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ አቋም ያላቸውን ልሂቃን ቢያቅፉም በኢትዮጵያ በአንድነት ጥያቄ ላይ ሁለት ተሰበጣጣሪ ጫፎችን ይሸከማል:: የመጀመሪያው በሀገሪቱ የሚገኙ ብሄር ብሔረሰቦች መብት መገንጠልን ባካተተ የራስን እድል የመወሰን ማዕቀፍ ውስጥ መታየት እንዳለበት ይከራከራል:: ኢትዮጵያን የብሄሮች ድምር ውጤት አድርጎ ከመመልከቱ በዘለለ ሀገሪቱ በብሄሮቹ መልካም ፍቃድ ብቻ መቆም እንደሚኖርበት ያምናል:: ሁለተኛው ዕይታ በኢትዮጵያ የግዛተ መንግስትነት ሂደት አንድ ወጥ የብሄር ጭቆና እንዳለ ቢቀበልም መፍትሄውን ከመገንጠል መብት በመለስ ባለ ማዕከላዊውን መንግስት ኢ-ማዕከላዊ (De-centralize) በማድረግ መፍትሄ ማነኘት እንደሚችል ያወሳል:: ፕ/ር ኪዳኔ እንደ ዶ/ር መራራ እና ፕ/ር በየነ ያሉት የደቡብ ልሂቃን በዚህ ውስጥ እንደሚበየኑ ይሟገታሉ:: እነዚህን የዘውግ ብሄርተኝነት መከራከሪያዎች አስመልክቶ ዶ/ር ማዕምር የከፋፋይ (fragmentation) ሀሳብ አራማጆች እንደሆኑ ይናገራሉ:: ዶ/ር ማዕምር ‹‹ኢትዮጵያዊያን የመለንቀጥንም ሆነ የከፋፋይነትን ስነ-ሙግት መቀበል ይቸግራቸዋል›› ሲሉ ለሀገሪቱ የዴሞክራሲ ልምምድ የተሻለው የአዋሐጆቹ የፖለቲካ የበላይነት እንደሆነ ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው ሞግተዋል::

በዚህ የፖለቲካው ተከታዮች የታሪክ-ፖለቲካ ትንተና ንፃሬ መድረክ ሁለተኛውን እና የሶስተኛውን ሁለተኛ ንዑስ ዕይታ በማሳሰብ መሀከል መንገድ ለማግኘት ይሞክራል:: በመለስተኛ ፕሮግራሙ ውስጥም የእኒህን ዕይታዎች አፅማድ በማካተት መሰረታዊ ትስስሮሽ እንዳላቸው ለማሳየት ሞክሯል:: ይኸንንም ለማስረገጥ በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ ‹‹ሁሉም መገንጠልን እንደማይደግፉ እና በኢትዮጵያ አንድነት ሉአላዊነት መከበር በጋራ እንደሚቆሙ›› እና ‹‹በብሄር ብሔረሰብ መብት መከበር እና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ተቃርኖ እንደሌለ›› እምነቱን አስፍሯል:: በፕሮግራሙ ላይ በግልፅ የተቀመጠው የኢትዮጵያ አንድነትን የመቀበል አቋም በሁለተኛነት ለተጠቀሱት የኢትዮጵያ ብሔርተኝነት አራማጆች የማይጠየቅ አቋም ነው:: በሌላ ጫፍ የብሔር ብሔርሰቦች ማንነታዊ መብቶች መከበር የዘውግ ብሔርተኞቹ የሙግት መነሻ ነው:: ነገር ግን ‹‹ቀደምት የሃገራችን አገዛዞች የብሄር ብሔረሰቦችን ህልውናና መብቶች ባለመቀበልና ባለማክበር›› የሚሉት በፕሮግራሙ ላይ የተፃፉ የኋላ ዘመን መተርጎሚያ ጫፎች የዘውግ ብሄርተኞቹ የአቋማቸው መከራከሪያዎች ናቸው:: ከግለሰብ መብቶች መከበር ይልቅ የቡድን መብቶች የሚከበሩባቸውን አውዶች በብዛት የሚተነትነው የፎረሙ ፕሮግራም ብዙ ጉዳዮችን ከዘውግ ብሄርተኞች ተውሶ የኢትዮጵያ ብሄርተኞቹን ዋነኛ መገለጫዎች ባለመወከሉ አንዳንድ ተንታኞች የተመቻመቸው ምንድን ነው? ብለው እንዲጠይቁ አስገድዷቸዋል::

የፌደራሊዝምን አወቃቀር በተመለከተም መድረኩ ያለውን ፌደራሊዝም በሚቀበሉ እና ሌላ ቅርፅ መሞከር አለብን የሚል አቋም የያዙትን አካትቷል:: ይህን ልዩነታቸውን በሪፈረንደም እንደሚያስወስኑት ፕሮግራማቸው ቢናገርም በድርድርም ሆነ በውይይት ሊፈቱት ካልቻሉት የመሬት ጥያቄ ጋር ሲደመር የመድረኩን ያልተሞከረ ኤክስፐርመንት ተተግባሪ የማያደርገው ይመስላል::

### መድረኩ ምንድን ነው?

አሁን ያለውን መድረክ ከመሰረቱትም ሆነ በአባል ፓርቲነት ካሉት መሀከል ከአንዱ ውጪ ሌሎቹ ብሔር-ተኮር ፓርቲዎች ናቸው:: የፎረሙ አመራሮች እንደሚሉት ከአንድነት ለፍትህ እና ዴሞክራሲ ፓርቲ ውጪ ላሉ ልዕለ-ዘውግ ፓርቲዎች ጥሪ ቢያደርጉም ወደ መድረኩ ለመቀላቀል ፍቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም:: ይህ አካሄድ መድረኩ ወደ ጥምረት የሚሻገር ከሆነ የሚኖረውን የፓርቲነት መልክ ህብረ-ዘውግ /Multi-ethnic/ አልያም ብሄርን ማዕከል የማያደርግ / Non-ethnic/ ስብስብ በመሆን መሀከል ያቆመዋል:: እኒህ ሁለት የፓርቲ ማንነቶችን በተመለከተ በጉዳዩ ምሁራን በኩል የሚቀርቡ ትንታኔዎች መሰረታዊ ልዩነቶች እንዳሏቸው የሚያስረዱ ናቸው:: ከነገሩ ፀሐፊዎቹ ቀዳሚ የሆነችው ካቻን ቻንድራ “A new cross-national data based on ethnic parties” እና “Why ethnic parties succeed: patronage and ethnic head counts in India” በሚሉት ጥናታዊ ስራዎቿ ሁለቱን የፓርቲ መልኮች ተፃራሪ መለዮ በጥልቀት ትተነትናለች:: አንድን ብሄር ማዕከሉ በሚያደርግና ከሁለት በላይ ብሔሮችን እወክላለሁ በሚል ፓርቲ መሀከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት ፓርቲዎቹ ወደራሳቸው በሚያካትቷቸው እና በሚያርቋቸው ብሄሮች ልክ ይወሰናል:: እንደ ፕ/ር ቻንድራ ብያኔ አንድ የብሄር ፓርቲ ወክያለሁ ስለሚለው ብሄር ብቻ ሲናገር ህብረ-ብሄራዊው ፓርቲ ቁጥራቸው ለበዛ ብሄሮች ውክልና እንዳለው ያምናል:: ይህ በሁለቱ መሀከል በግልፅ የሚታይ ልዩነት ቢሆንም ፖለቲካዊ ድጋፍ የሚሰጣቸውን የፖለቲካ ማህበረሰብ በተመለከተ ተመሳሳይ የቅስቀሳ መንገድ ይከተላሉ:: ዶ/ር ቻንድራ ከላይ በተጠቀሰው ሁለተኛ ጥናቷ እንደምትለው ህብረ-ብሄር ፓርቲዎች አንድን ብሄር ብቻ የድጋፍ ማዕከላቸው ባያደርጉም ወደ ማህበረሰቡ ለፖለቲካዊ ቅስቀሳ ይዘውት የሚቀርቡት ማሰባሰቢያ ስትራቴጂ ብሄርተኝነትን ይንተራሳል:: ከርዕዮተ-ዓለምም ሆነ ሀገራዊ ፖሊሲዎች ይልቅ ብሄርተኛ ማንነትን የሚያጦዙ አፈ-ነቢብን / Rethoric/ ይመርጣሉ:: ከዚህ በተፃራሪ ዘውግ-ዘለል የሆኑ ፓርቲዎች ራሳቸውን የፖለቲካው ገበያ ላይ ለመሸጥ የሚሞክሩት ብሄርን የማይታከኩ ሀሳቦችን በማቀንቀን ነው:: ‹‹እነዚህ ፓርቲዎች ብሄር ተኮር ጥያቄዎችን መመለስ እንደሚችሉ ቢያምኑም የብሄሮች ፍላጎቶችን በፖለቲካ መደላድሎቻቸው ውስጥ አያካትቱም›› ትላለች ቻንድራ “Why ethnic parties succeed” በሚለው ጥናታዊ ድርሳኗ:: መድረክን በዚህ ሙግት ለመመልከት የሚሞክሩ የፖለቲካው ተዛቢዎች ስብስቡ በሂደት ወደ ጥምረት የሚመጣ ከሆነ የብዙ ቢሆን እድሉ ህብረ-ብሔራዊ ሊሆን እንደሚችል ያወሳሉ:: ይህ እድል ለብሄርተኞቹ ፓርቲዎች መንቀሳቀሻ ማዕቀፍ ቢሰጥም ራሱን ዘውግ-ዘለል አድርጎ ለሚያስበው አንድነት ፓርቲ ከባድ ተግዳሮት ይሆናል:: ሁኔታው የፓርቲውን የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት መገለጫዎች እንዲያመቻምች ሊገፋው ይችላል:: የዚህ ተራዛሚ ተፅዕኖ ከዚህ ቀደም ፓርቲው ወደ መድረክ የገባበትን አካሄድ አስመልክቶ የተከሰተውን ዓይነት የአንጃ ፖለቲካ ሊቀሰቅስ የመቻሉ እድል የበዛ እንደሆነ ፍትህ ጋዜጣ ያነጋገረቻቸው የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ይናገራሉ:: መድረክ ወደ ጥምረት የሚያዘግም ከሆነ የሚገጥመው ሌላኛው ተግዳሮት የአመራሩ የመረጋጋት እድል ነው:: ዶ/ር ቻንድራ “A new cross-national data based on ethnic parties” በሚለው ፅሁፏ እንደምታነሳው ከህብረ-ብሄር ፓርቲ ይልቅ ብሄር-ተኮር ፓርቲ የአመራር መረጋጋት ይታይበታል:: ሴትዮይቱ ለዚህ መላምቷ መከራከሪያ አድርጋ የምታቀርበው የብሄር-ተኮሮቹ መሪዎች ከአንድ ብሔር መሆንን እና የህብረ-ብሄሮቹ ከብዙ ብሔሮች መውጣጣታቸውን ነው:: ከዚህ በተጨማሪ እንደመድረክ ያለህብረ-ብሔራዊ ፓርቲን የሚመሩ አመራሮች የቅንጅቱን አመራር መያዝ ያለመያዝን ሁነት ከየብሔሮቻቸው ጋር

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

ተወዳጇን አዲስ ታይምስ መፅሔት የፊታችን ማክሰኞ
ከበርካታ ወቅታዊ መረጃዎች ጋር ይጠብቋት



# የኖርዌዩ ወጣት የጥላቻ ማኅደር

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

የኖርዌይ ሕዝብ በጣም ሃይማኖተኛና በጣም ሰላማዊ የሚባል ነው፤ በዓለም-አቀፍ ደረጃም ግጭትና ጦርነት ባለበት ሁሉ እርቅንና ሰላምን ለማምጣት የሚጥር ህዝብ ነው፤ ነገር ግን የዛሬ ዓመት ግድም አንድ የኖርዌይ ወጣት ከኖርዌያውያን የማይጠበቅ በጣም የሚያሰቅቅ ክፉ ወንጀል ፈጸመ፤ ሰሞኑን በፍርድ ቤት ቀርቦ ጉዳዩ እየታየ ነው።

ይህ መልካም የሰው ቅርጽ የያዘ ወጣት ተግባሩ የአውሬ ነበር፤ በኦስሎ በኖርዌይ ዋና ከተማ በመኪና ውስጥ ቦምብ ጠምዶ በፍንዳታው ስምንት መንገደኞችን ገደለ፤ አልበቃ ብሎት በጣም ዘመናዊ መሳሪያ ይዞ ወጣቶች ወደተሰበሰቡበት ደሴት ሄዶ እያነጣጠረ ስድሳ ዘጠኝ ያህል ወጣቶችን ገደለ፤ አልሸሸም፤ ሆን ብሎ በእሱ ግምት በአገሩ ላይ የአንዣበበውን አደጋ ለማየት ህዝቡ እንዲነቃ ለማድረግ ነበር፤ አውሮፓ በእስላሞች እየተወረረ በመሆኑ የአውሮፓ ህዝብ ይህንን አደጋ እንዲገነዘብ ለማድረግ የፈጸመው አስፈላጊ ተግባር ነው ብሎ በአደባባይ ተናገረ፤ እስልምናንና እስላሞችን ይጥላ እንጂ ቆም ብሎ ማሰብ ቢችል እንደሱ በጥላቻ የታጨቀ እስላም ብቻውን ሆኖ ኖርዌያዊው ራሱ ከአደረሰው ጥፋት የበለጠ ምን መስራት ይችል ነበር? ስለዚህም በጥላቻ በታጨቀ እስላምና በጥላቻ በታጨቀ ክርስቲያን መሀከል ልዩነት የለም ማለት ነው፤ ሁለቱም የጥፋት መልእክተኞች ናቸው፤ ሁለቱም የሰው ልጆች ጠላቶች ናቸው፤ ሁለቱም ሃይማኖታቸውን የክፋትና የወንጀል መሸፈኛ እያደረጉ ናቸው፤ የራስን እምነትም ሆነ አመለካከት በግድ በሌሎች ላይ ለመጫን መሞከር፣ የማይሆንለት ሲሆን ደግሞ በጭካኔ በመደዳው መግደል በአንድ በኩል የማመዛዘን ችሎታ ያለው፣ በሌላ በኩል የሉዓላዊ ኃይል መንፈስን የታደለ የሰው ልጅ የሰይጣን ማኅደር ሲሆን የሚያደርገው እኩይ ተግባር ነው።

የኖርዌዩ ወጣት ጥላቻው ለእስልምናና ለእስላሞች ብቻ አይደለም፤ ጥላቻው ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፤ በአፍጋኒስታንና በኢራቅ፣ በፓኪስታንም እንደኖርዌዩ ወጣት ሰዎችን በጅምላ የሚያቃጥሉ ሰዎች አሉ፤ የእነዚህን ከኖርዌዩ የሚለየው በአገራቸው ውስጥ ‹‹ወራሪ›› የሚሉት የውጭ ኃይል መኖሩና ለትግላቸው የሉዓላዊነት ሽፋን ማግኘታቸው ነው፤

ልብ በሉ፤ ይህ የኖርዌይ ወጣት ጥላቻው በእስልምና እና በእስላሞች ላይ ይመስላል፤ ነገር ግን የጨረሳቸው ሰባ ሰባት ሰዎች የአገሩ ልጆች ናቸው፤ ግራ የሚያጋባ ይመስላል፤ ፍቅርና ጥላቻ ኃይላቸው ሙሉ የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ ፍቅርም ሆነ ጥላቻ ልብን መቶ በመቶ አፍኖ ሲይዝ መስፈሪያ ነገር ሁሉ፣ ሚዛን ሁሉ ይሰባበራል።

የኖርዌዩ ወጣት ልቡ በጥላቻ ሞልቶ፣ ዙሪያውን በሙሉ በጥላቻ ቀለም ሲቀባ ኖሮ የመጨረሻውን የጥላቻ ቅብ ሲቀባ አድሮ፣ ጠዋት ሲነሣ ዙሪያው ጠላት ሆኖ አገኘው፤ ያኔ መግደያ መሣሪያውን አነሣና ያገኘውን ሁሉ፣ ሰባ ሰባት ሰዎች ጨረሰ፤ በፍጹም አልተጸጸተም፤ ጥላቻው የጣለበትን ግዴታ ፈጸመ እንጂ ጥፋት ወይም ወንጀል መሥራቱን አላመነም፤ መግደሉን አልካደም፤ የገደላቸው የገዛ ወገኖቹ መሆናቸውን አልካደም፤ የሚጠላው እስልምናን መሆኑን ተናግሮአል፤ ከእስልምና ጋር አያይዞ የሚጠላው እስላሞችን መሆኑን ገልጾአል፤ ታዲያ እስላሞች እስልምና ሊከላከልላቸውና ሊጠብቃቸው የሚፈልገውን የሚወዳቸውን ሰዎች የገደላቸው እስላሞች እንዳይሆኑበት ነበረ?

የጥላቻን ጭካኔና ክፋት፣ የጥላቻን ጭፍንነትና ድፍንነት የምናየው የኖርዌዩ ወጣት የገደላቸው የገዛ ወገኖቹ በመሆናቸው ነው፤ ጥላቻ የመጥፎ ስሜቶች ሁሉ ቅይጥ ነው፤ ቁጣና ንዴት፣ ክፋትና ተንኮል፣ ዕብሪትና ጭካኔ፣ ፍርሃትና ጥርጣሬ በአንድ ላይ ተፈትለው የተሰሩበት መጥፎ ስሜት ነው፤ በእንዲህ ያለ የጥላቻ ስሜት ተቀስፎ የተያዘ ሰው እንቅልፍ አያገኝም፤ አካሉ በሙሉ ከአለው ሁሉ ችሎታ ጋር የጥፋት ፋብሪካ ይሆናል፤ አጋጣሚ አግኝቶ ሂትለርን ወይም ሙሶሊኒን፣ ስታሊንን ወይም ኢዲ አሚንን ከሆነ የጥፋት ፋብሪካው በብዙ ሠራዊትና በብዙ የተለያዩ መሣሪያዎች የታገዘ ስለሚሆን የጥፋቱ መጠን ሰፊና የከፋ ይሆናል፤ እንደ ኖርዌያዊው ወጣት ብቸኛ ከሆነና እንደኖርዌይ ባለ የሠለጠነ አገር ግን ጥፋቱ የተወሰነ ይሆንና ሕግ ያቆመዋል።

ሰባ ሰባት ሰዎችን ገድሎ የጥላቻው ደንዳናነት ምንም ጸጸት እንዳይሰማው ኅሊናውን የጋረደው፣ ምንም የሞቱት ሰዎች ዘመዶች መሪር ሐዘን በጨረፍታ ያላረፈበት፣ ምንም የሚኞቹ የተቋረጠ ተስፋና የተቀጨ ሕይወት ያልከነከነው ሰው እጁን ጨብጦ ‹‹ደግ አደረግሁ!›› በሚል የፉከራ ምልክት በፍርድ ቤቱ ውስጥ እጁን ጨብጦ ‹‹ደግ አደረግሁ!›› በሚል የፉከራ ምልክት በፍርድ ቤቱ ውስጥ እጁን አነሣ፤ ዕድሉን ካገኘ የሠራውን አስከፊ ተግባር እንደገና እንደሚያደርገው ሳያፍር ተናግሮአል።

እንዲህ ያለው የጥላቻ ማኅደርና የጥላቻ መልእክተኛ ሕጋዊ ሥርዓት በሰፈነበት ማኅበረሰብ ውስጥ በቶሎ ይቀጫል፤ ማኅበረሰቡም ትምህርት ያገኝበታል፤ ሕጋዊ ሥርዓት ባልሠለጠነበት ማኅበረሰብ ውስጥ ግን እንዲህ ያለ እኩይ አመለካከት እንደቆላ ቁስል ውስጥ ውስጡን እየተሰራጨ ማኅበረሰቡን መርዞ እስከመግደል ይደርሳል።

# የፋሲካ-ፖለቲካ

ዓለማየሁ ገላጋይ

‹‹ሁለት እናቶች የዶሮ ቅርጫ ገቡ አሉ››

እኔም እንደእናንተ በዘመኑ ቋንቋ ‹‹ፍተላ›› መስሎኝ ነበር። ግን አለመሆኑን አረጋገጥኩ። እንዴት እንዳረጋገጥኩ ይቆያችሁና እውነቱን ልንገራችሁ፡-

ሁለቱ እናቶች እያንዳንዳቸው ሁለት፣ ሁለት ልጆች አሏቸው በዓመት በዓል ሰሞን ልጅ መቼም ውጋት ነው። እነዚህ እናቶች በጥንድ ውጋት ተቀስፈው ኖሯል ‹‹እማ-እማዬ፣ ዶሮ አይገዛም?››

‹‹እነ እማዬ›› ደግሞ ለዶሮ መግዣ የሚበቃ ብር የላቸውም። ስለዚህ ተመካክረው በማዋጣት ለሁለት አንድ ዶሮ ገዙ። ዶሮው የሁለቱ ቤት አማካኝ ቦታ ላይ ታሰረ። የሁለቱም ቤት ህፃናት ስለዶሮው የተነገራቸው ተመሳሳይ ነው።

‹‹ዶሮው የእኛ ነው። ጐረቤታችን ዶሮ ስላልገዙ ልጆቹ እንዳያለቅሱ የእናንተ ነው ተብለዋል። ስለዚህ ሲመሽ አስገብተን እናርደዋለን።››

የቅዳሜ ሱር ዕለት ማታ ሁለቱም ቤት ሽንኩርት ተቁላላ። የሁለቱም ቤት ህፃናት በጊዜ እንዲተኙ ተደረገ። አራጁ መጥቶ ካረደ በኋላ አስራ ሁለቱን ብልት ሁለቱ እናቶች ቆጥረው ተካፈሉ። ጥቂት አለመግባባት የተፈጠረው ‹‹ፈረሰኛው›› ላይ ነበር። እሱንም እኩል ሰንጥቀው በመካፈል አለመግባባቱ በሰላም ተፈታ አሉ። ሁለቱም ቤት ግማሽ ግማሽ ዶሮ ታጥቦ ወጥ ተሰራ። የሁለቱም ቤት ልጆች ሌሊት ተቀስቅሰው በአክፋይ ወግ ዶሮውን እንዲቋደሱ ተደረገ።

ይሄን ወሬ የጠቆመኝ ሰው አለመታመኑ ስላንገበገበው ከበአሉ በኋላ አንደኛዋን እናት በስልክ አገናኘኝ እያሳቁ ነው የሚያወሩት፡-

‹‹አሁን ይሄን ወሬ ብላችሁ ነው? ምን ይጠቅማል?›› በማለት ቀጠሉ ‹‹ድሮም’ኮ የዶሮ ስጋ ወግ ነው። የሚበላው ሽንኩርቱ ነው። ጥሩ ተደርጐ ከተቁላላና ቅባት ካገኘ ሽንኩርቱ በቂ ነው!! ለነገሩ እሱም (ሽንኩርቱ) እሳት ሆኗል።››

‹‹ስንት ገባ?››

‹‹ኪሎውን አስራ አንድ፣ አስራ ሁለት ብር ይላሉ። ያው ነው፣ ቅቤውንም ያልክ እንደሆን ኪሎው መቶ ሰባ ብር ነው።››

‹‹ቅቤውም በቅርጫ…›› አላስጨረሱኝም፣ አቋረጡኝ።

‹‹ኡ-ይ፣ ቅቤውማ ሩብም፣ የሩብም ግማሽ የሚሸጥበት አለ። እንዳቅ-እንዳቅም ይገዛል።››

‹‹ያልገባኝ ነገር››

‹‹እ?››

‹‹ዶሮውን በቅርጫ ከመካፈል ሥጋ መግዛት አይሻልም?››

‹‹ኡ-ይ ያንተ ነገር! ሥጋውስ የሚቀመስ ሆኖ ነው? ግማሽ ኪሎ እኮ ሃምሳ ብር ነው።›› ስሜታቸው እየጠየመ ሲሄድ ይታወቀኛል።

ግን-ግን የበአሎቻችን መለኪያ ስለምን ምግብና መጠጥ ብቻ ሆነ? በአሎቻችንን ከምግብ ጋር እንዳይፋቱ አድርጐ ያፈጣጠማቸው ማነው? በአሎቹ ሁሉ በምግብ ሽታ፣ በምግብ ጣዕም፣ በምግብ መትረፍረፍና በመጠጥ መድፋፋት ካልሆነ በቀር አንደምቅ ማለታቸው ስለምን ይሆን?... ከዘንድሮ የበለጠ እምን አይነት የኑሮ ስርቻ ውስጥ ብንወተፍ ነው በዓልን በምግብ ከማጀብ ዕዳ ነፃ የምንወጣው?...

አባባላችን እንኳን ከዚህ የበዓል አዙሪት እንዳንወጣ የሚያበረታታ ነው። ለምሳሌ ይሄን አፋዊ ሥነ-ቃል እንመልከት፡-

‹‹ፋሲካን ሊያገኙ፣ ሁዳዴን ይመኙ››

ልብ በሉ። የአንድ ጀንበር ፋሲካ ናት በ55 ቀን ‹‹ጦም›› ልትለወጥ በንፅፅር የተቀመጠችው። ምሳሌ ነውና ‹‹ፋሲካ››ም፣ ‹‹ጦም››ም በጥሬ ትርጉማቸው አይወሰዱም። የአንድ ቀን ፌሽታ ከ55 ቀን ችግር ጋር አቻ-ለአቻ ናቸው እንደማለት ነው። ‹‹ፋሲካ የሌለው ጦም፣ ደስታ የሌለው ዓለም›› ነውና ለእኛ ፋሲካችን ከሰለቸ ወደ ሰለቸ ኑሮ የምንሸጋገርበት የአፍታ አንጓ ነው። በተንዛዛ የመከራ ጉዞ መሀል አረፍ የሚባልበት መጠነኛ ጉብታ!

ዛሬ የተለመደውን የበዓል መንፈስ አብዛኞቻችን አጥተነዋል። ዶሮ፣ በግ፣ ቅርጫ፣ ዳቦ፣ ጠላ፣ ጠጅ፣ ነጭ አረቂ፣ የሀበሻ ልብስ… የለም። ደሃው የማይደርስበት ቦታ ተሰቅለዋል። ምግብ አልተትረፈረፈም፣ ዳቦ አልተቆራረሰም፣ ሥጋ አልተበላለተም፣ መጠጥ አልተድፋፋም… ማለት በዓሉ በዓል አልሆነም ማለት ነው። በዓሉ-በዓል ካልሆነ ደግሞ የሚናጋው ቤተሰባዊ መንፈስ ብቻ አይደለም። ከዚያ ያልፋል። ይኼን የሚለን ባዕዱ ተመራማሪ Raiduef Kunt Molvear ልብ ብሎ አይቶን በቋጠረው ግንዛቤ ነው። “TRADITION AND CHANGE IN ETHIOPIA” የተሰኘ መጽሐፍ ላይ እንዲህ ይላል፡-

“In an agricultural country like Ethiopia it is natural that much attention is paid to food. Not only as a means of survival, but also for social and cultural reasons.”

(ኢትዮጵያን በመሳሰሉ፣ በእርሻ ላይ የተመሰረቱ አገሮች ዘንድ ለምግብ ልዩ ትኩረት መስጠት የተለመደ ነው። ምግብ፣ የህይወት መድህን በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊና ባህላዊ ፍቺም ስላለው ልዩ ትኩረት ይሰጡታል)

በዓሎቻችን በምግብና በመጠጥ የሚንበሸበሹት መብላት መጠጣቱ የመኖር ዋስትናችን ስለሆነ ብቻ አይደለም ማለት ነው። የበዓል ሰሞን ዶሮ፣ በግ፣ ቅርጫ፣ ዳቦ፣ ጠላ… የሚወክሉት ማህበራዊና ባህላዊ እሴት እንዳላቸው ነው ባዕዱ ተመራማሪ የሚነግረን። ሁለት ወር ተቸግረን አንድ ቀን በመደገስ የተቀረውን ዓመት ሙሉ በሰላም፣ በመከባበር፣ በመተሳሰብ…እንኖራለን። ‹‹ብቻውን የበላ ብቻ ነው፣ ብቻውን የሚሞተው።››

Molvearየኢትዮጵያውያን ሁለንተናችን ትርጓሜ የሚያገኘው ከምግብና ከመጠጥ ጋር ተያይዞ እንደሆነ ይነግረናል። ከአመታዊ በዓላት ባሻገር ሰርጉ፣ ተዝካሩ፣ ማህበሩ፣ እድሩና ዕቁቡ ሳይቀር አብሮ በመብላትና በመጠጣት ትርጓሜ እንደሚያገኝ ይነግረናል። ትዳር ሲመሰረትና ጎጆ ሲቀለስ እንኳን ‹‹እህል ውሃ›› (Grain and water) ወይም በማብሰያው ‹‹ሶስት ጉልቻ›› (Sost gulecca) ይሉታል ይላል።

Molvear የመብላትና የመጠጣት ግንኙነታችን እስከ ሃይማኖትም የዘለቀ ቦታ እንዳለው ጠቆም ያደርጋል። “The social and cultural importance of food and drink takes precedence over most other aspects of the people’s life. Even religious life is to a large extent a question of food.”

በእኛ ዘንድ የበዓላት ሽር ጉድ የማንነትን ጣጣ የተሸከመ ጉዳይ ነው። የተሰሳሰቦና የተረዳድቶ መኖራችን ፅንስ ማህፀኑ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣቱ ነው። በዓላትና መሰል ድግሶች ከማህበራዊ፣ ከባህላዊና ከሃይማኖታዊ ትርጓሜያቸው ባሻገር ፖለቲካዊ ፍቺም አላቸው። በአስተዳደር ላይ ያሉ ገዢዎች እንደ የደረጃው ተገዢውን እየጠሩ ግብር ያበላሉ። ግብር ማብላት ለፖለቲካው መረጋጋት ዋስትና ሆኖ ቆይቷል። ከዚያም ባሻገር የምግብና የመጠጥ ወቅታዊ ሁኔታ የመልካም አስተዳደር ማንፀሪያም ነበር። እስካሁንም ነው። ለምሳሌ ያህል እነዚህን ነባር አባባሎች እንመልከት፡-

-በኢያሱ ዳቦ ነው ትራሱ

-በተፈሪ ጠፋ ፍርፋሪ

-በመንግሥቱ ባዶ ነው ሌማቱ

-በመለስ ጠፋ የሚቀመስ

የዘንድሮው ፋሲካ በችግር ወቅት የተወለደ ልጅ የሆነብን የሚቀመስ በታጣበት ወቅት ስለመጣ ነው። የነጠፈ የኑሮ ጡረታችን በዚህ የችግር ወቅት በዓል ቢመዘመዝም አብሮ መኖራችን እንደማይሞት የዶሮ ቅርጫ ገብተንም እየተፍገመገምን ነው። የዶሮ ጉን ያስገቡት ሁለቱ እናቶች የልጆቻቸውን ሥነ-ልቦና ከጉዳት በማዳን ብቻ የተገቱ ይመስላችኋል? አይደለም! በስልክ ያናገርኳቸው እናት እንዲህ ብለውኛል፡-

‹‹ጠዋት ከጐረቤት ጋር ተጠራርተን ‹እንኳን አደረሰን› ተባብለንበታል። የአመት በዓል ሆድ ብዙ አይፈልግም፤ ለአመል ያህል ለኮፍ-ለኮፍ ነው። እስቲ ይሄንንም አይንፈጉን!››

በበዓል ሆነ በአዘቦት ለምግብ ልዩ ትኩረት መስጠታችን የነፍስ አድን ጉዳይ ስለሆነብን አይደለም። ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ህይወታችን በዚያ ላይ በመመስረቱ እንጂ። የምግብ ዋጋ ንረት ጉዳይ በመንግስት እንደሚታየው ከምግብ ዋስትና አንፃር ብቻ ታይቶ የሚጠቃለል አይደለም። ከዚያ በላይ፣ በላይ፣ በላይ…እንጂ።

# የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ የቱን ጥያቄ መለሷል?

ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ባለፈው ማክሰኞ በፓርላማ ቀርበው በሰጡት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ላይ በፍትህ እምነት ያልተመለሱ፣ እንዲሁም ከመረጃ እና ማስረጃ ጋር የማይዛመዱ መልሶች ተንፀባርቀዋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖም ፍትህ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከፓርላማ አባላት በኩል የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ለሁለት ከፍላ ማየቱ አስፈላጊ እንደሆነ አምናበታለች፡፡ ይህውም የገዢው ፓርቲ አባላት 99.6 በመቶ የሚሆነውን የፓርላማ መቀመጫ በተቆጣጠሩት ያለውን በአንድ ወገን፣ ሁለተኛው ደግሞ በአንድ ወንበር ብቻ ተቃዋሚ ፓርቲን በመወከል በፓርላማው የሚገኙት አቶ ግርማ ሰይፉ ያቀረቡት ጥያቄ በሌላ ወገን በማድረገ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የፓርላማ አባላት ወደ ምክር ቤቱ የሚገቡት የወከሉት ማህበረሰብ በተደጋጋሚ የሚደርስበትን በደሎች፣ ብሶቶችና ኢ-ፍትሃዊ አስተዳደሮችን በመጥቀስ መፍትሄ ለማስገኘት የሚለውን መርህ ለማስፈፀም አንዱ ነው፡፡ በዚህ ረገድም የኢትዮጵያ ፓርላማ አንድም ቀን ከገዥው ፓርቲ የተለየ ሀሳብ ቀርቦበት ውሳኔ ሲያገኝ መመልከት አልቻልንም፡፡ ከዚህም ባሻገር በፓርላማ የሚነሱት ጥያቄዎች ከውጭ ስለሚገቡ መኪኖች እና ስለሚጣልባቸው ቀረጦች፣ ምርታማነት በጣም እየጨመረ ስለሆነ ለገበሬው ምን ታስቧል?፣ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ አባይን ለማልማት ደፋ ቀና እያለ ነው፤ መንግስት ይህንን የህዝብ መነቃቃት እዳር ለማድረስ ምን እያደረገ ነው?.... የሚሉትን እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲያቀርቡ፤እርሳቸውም በኩራት ሲመልሱ ነው፡፡

ነገር ግን ፍትህ ሁሉንም የፓርላማ አባላት ትጠይቃለች፡፡ መኪና ነው የሚቀድመው የመኖር ጥያቄ? የኤርትራ ተወላጆች ብሶት ነው የሚቀድመው የወገኖቻችን በየአረብ አገራት የሚደርስባቸው እንግልትና ስቃይ? የቻይና እና የሩቅ ምስራቅ አገሮች ኢኮኖሚ ስላደገበት ምክንያት በንድፈ ሀሳብ የታገዘ ኢኮኖሚያዊ ትንተና ወይንስ እኛ ለምን ጠግበን ማደር እንዳልቻልን በግልፅ መወያየት? የአሸባሪው የአልቃይዳ መረብ እና አደጋው መተንተን ወይንስ ዝቅ ብሎ መምህራኑ ለምን ተከፉ፣ የሃይማኖት ተከታዮች እና በመንግስት ጫና እየተደረገብን ነው የሚሉትን ወገኖች ብሶት መስማት? ከግብፅ ተባርረው ወደ ኤርትራ ከመግባት ይልቅ ኢትዮጵያ ትሻለናለች ላሉ ኤርትራውያን ማንም የበለፀገ አገር ያላደረገውን እንክብካቤ አድርገን ወደ አገራችን ስለማስገባቱ ነው መብራራት ያለበት ወይንስ ዜጐች ያለምንም ህገ-መንግስታዊ መሰረት በተለያዩ ክልሎች እየደረሰባቸው ያለውን ህገ-ወጥ መፈናቀል እና ለባለሀብት ሲባል መሬታቸው እየተነጠቀ ወደ ፈለጋችሁበት ሂዱ ስለሚባሉ ዜጐች ምክንያት መፍትሄ መፈለግ? በተለይም ክቡር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሊሰጡ ይገባል፡፡

ፍትህ ከኢትዮጵያውያን ብሶት ይልቅ ለምን የኤርትራውያን ዜጐች ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርጉት ፍልሰት ትኩረት እንደተሰጠው ይብራራ ዘንድም ትጠይቃለች፡፡ ዜጐቻችን ያላገኙትን እድል ሌሎች ዜጐች እንዲያገኙ ለማድረግ ለምን ተፈለገ? ስትል ትጠይቃለች፡፡

የፓርላማው ጥያቄና መልስ እንደተለመደው የተከናወነ ሲሆን፣ አሁንም ጥያቄዎችን ከመመለስ ይልቅ የጥያቄውን አቅራቢ ፍላጎት ላይ ያነጣጠረ መልስ የተሰጠበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮ ከብዶታል፣ የሚበላው ምግብ አጥቷል፣ ፍትህ የሚባል ነገር ፈፅሞ ማግኘት የማይቻልበት ደረጃ ላይ እየተደረሰ ነው፡፡ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ብሔር ተወላጆች የመኖር ዋስትና አጥተዋል የሚሉትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሳይመለሱ ተዘለዋል፡፡

የፍትህ ሌላኛው ጥያቄ በጉራፈርዳ ‹‹ሰፋሪዎች›› ላይ የደረሰውን መፈናቀል አስመልክቶ መጠየቅ የነበረበት የፓርላማ ተወካይ ማን ነበር? አቶ ግርማ ሰይፉ ወይንስ ከጐጃም ተወክለው የመጡ? አልያም ከአማራ ክልል የተመረጡ የፓርላማ አባላት የሚለው ነው፤ነገር ግን በይፋ ያየነው የአማራ ክልልን ወክለው የገቡ አባላት በዚህ ጉዳይ ላይ አንድም ጥያቄ ሲያነሱ አለመታየታቸው ነው፡፡ መቼም ከእንግዲህ ወዲህ የህዝቡ ጥያቄ የማይነሳ ከሆነ፣ በመሬት ላይ ያለው ችግራቸው በፓርላማ ለውይይት ቀርቦ መፍትሄ እስካልተሰጠው ድረስ በተወከሉት ሰዎች ላይ የሚኖረው መተማመኛ ምን ሊሆን እንደሚችል መንግስት ሊገነዘበው ይገባል ትላለች ፍትህ፡፡


ስለተፈናቀሉት ሰዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርላማ ቀርበው እስኪናገሩ ድረስ የአማራ ክልል መሪዎች ለምን ዝምታን መረጡ? እንዲሁም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሰብዓዊነት መንግስት እንኳን ያላደረገውን መልካም ስራ በመስራታቸው ሊመሰገኑ ሲገባ ወቀሳውን ምን አመጣው? እነዚህ ሁሉ ሊጠየቁና መልስ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በመንግስት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት አካሄድም ፍትሃዊ እንዳልሆነ ፍትህ ታስገነዝባለች፡፡ የመብት ጥያቄን የጥቂቶች ነው ብሎ ብቻ ማለፍም ተገቢ አይደለም፡፡ ይህም ይሁን ቢባልስ የጥቂቶችስ ቢሆን ድምፅ ሊሰማ የሚገባው የመንግስት አካል ማን ነው? የጥቂቶች መብትስ የሚከበርበት መንገድ ሊኖር አይገባም? ጥቂቶች ላለመባልስ ቁጥሩ ስንት መሆን አለበት? በእርግጥ መንግስት ለእንደዚህ አይነት ጥያቄ ግልፅ የሆነ ማብራሪያ ሲሰጥ አይታይም፡፡

ሁለተኛው መንግስት በስርዓቱ ላይ ለሚነሳበት ተግዳሮት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየተጠቀመበት ያለው ማስፈራሪያ ከነጭ ለባሾች፣ ህገ-መንግስቱን በኃይል ለመናድ ከሚሞክሩ አሸባሪ ኃይሎች ጋር በመተባበር… እየተባለ የሚሰጣቸው ተለጣፊ ስያሜዎች ምክንያታዊነት የሚጐድላቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ መንግስት የተጠየቀውን ጥያቄ በአግባቡ ከመመለስ ይልቅ ወደ ማስፈራራቱ ማዘንበሉ ፍትሃዊ አይደለም ስትል ፍትህ ታሳስባለች፡፡ አሁንም ቢሆን ለአገራዊ ችግሮቻችን ተገቢና ምክንያታዊ ምላሽ፣ ለጠፋው ጥፋት ህጋዊ ተጠያቂነት፣ ለዜጐች ጥያቄ በቂ ማብራሪያ ይሰጥ ዘንድ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

## አስተያየት

# ‹‹ወጣት አደረጃጀቶች ከወረቀት በዘለለ መልኩ ነፃነታችን ይከበር››



**ብርሃኑ ተ/ያሬድ**
**የአዲስ አበባ የከተማ ም/ቤት አባል**

የዚህን ፅሁፍ ይዘት አብዛኞቹ የወጣት አደረጃጀት አባላትና አመራሮች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በየመድረኩ አንስተን ተከራክረንበታል፡፡ በተደጋጋሚ በብዙ ወላዋይና አድርባይ ወጣቶችና ካድሬዎች የሚያሸማቅቅ እንዲሁም የሚያስቅና እዚህ ግባ የማይባል ምላሽ ተሰጥቶናል የኛ ጥያቄ እስካልተመለሰ ድረስ ግን አሁንም እንጮሀለን፡፡

የዚህ ፅሁፍ አላማ ዝምታውን መስበር ነው፡፡ የሚያስፈራውን ዝምታ ሰብሮ መብትን ማስከበር፣ ነፃነትን ማረጋገጥ፣ የሌሎችን ሞግዚትነት አሽቀንጥሮ ጥሎ በራስ አቅምና ክህሎት መስራት እና ህገ መንግስቱን እየናዱ ህገ መንግስቱን እናስከብራለን የሚሉ ግለሰቦች ከተግባራቸው እንዲታቀቡ ማድረግ ነው፡፡

ተቋማዊና ግለሰባዊ ነፃነታችውን በህገ መንግስቱ የተደነገገ መብት እንጂ ግለሰቦች በፈለጉት ጊዜ የሚሰጡንስ ወይም በፈለጉት ጊዜ የሚነጥቁን ቁስ አይደለም፡፡ ለምንራመደው እያንዳንዱ እርምጃም ሞግዚት የሚያስፈልገን ህፃናት አይደለንም፡፡ የማንም ጥገኛና ተላላኪ መሆንንም የምንቀበል የካድሬዎች ባርያና ተላላኪዎች አይደለንም፡፡ ይህን ሁሉም ሊያውቅ ይገባል፡፡ ዛሬ እየታየ ያለው እውነት ግን ይህ አይደለም፡፡ እያልን ያለነው በየግምገማውና ስብሰባው ተቋማዊና ግለሰባዊ ነፃነታችን እየተጣሰ፣ ለነፃነታችን በመታገላችንና የጥቂት ግለሰቦችን ቃል ባለመድገማችን ብቻ ‹‹የአመለካከት ችግር›› በሚል ቡድናዊ ቋንቋ እየተጨፈለቅን፤ የማናምንበትን ሀሳብ እንዲስተካከል በመናገራችን ብቻ በጉሪጥ የምንታይበትና በተቃዋሚ ፓርቲ አባልነት ተፈርጀን የምንታይበት አሰራር ይስተካከል ነው፡፡

በወጣት አደረጃጀቶችና ሲቪክ ተቋማት ውስጥ የየትኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆንም ያለመሆንም መብት የተጠበቀ ነው ቢባልም አንዳንድ የፖለቲካ አመራሮች ግን ያልተፃፈ ግዴታ ያስቀመጡልን ይመስል የፖለቲካ ስሜት የሌላቸውንና የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባልና ደጋፊ ያልሆኑ ወጣቶች እንደ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እየታዩ የሚወገዙበትና የሚገለሉበት አሰራር ይቁም ነው እያልን ያለነው፡፡ እየሰራን ያለነው እውነተኛ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ተግባር እንጂ ለግለሰቦች ሹመትና ስም አይደለም፡፡ ከቤታችን ወጥተን ተደራጅተን ለመታገል በመወሰናችን ብቻ መንግስት ሀሳባችንን ሊቀበልና ሊያከብረን ይገባል፡፡

በተቋማችን ለወጣቱ የሚጠቅም ማንኛውም ተግባር መፈፀም እንጂ የግለሰቦችን ስሜት ብቻ መከተል አይጠበቅብንም፡፡ ወደ እውነቱ ስንመጣ ግን ከእኛ ካልወረደ በስተቀር ለወጣቱ የሚጠቅም አይደለም የሚል አይነት ይዘት ያለው ሀሳብ በአንዳንድ ካድሬዎች ሲንፀባረቅ ይታያል፡፡ ለዚህም ዋና ማሳያ የሚሆነው ማህበሩ ከኢ.ቲ.ቪ. ጋር በመነጋገር የግብር ማስከፈል ስራን በኮሚሽን ለወጣቱ በማሰራቱ ጠቃሚ ያልሆነ ስራነው ለወጣቱ የሚጠቀመው እኛ ያመጣነው የጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ብቻ ነው ብለው አንድ አመራር የተናገሩት ንግግር ነው፡፡ ዛሬ ፍራክሽን በሚል አደረጃጀት ሽፋን በግልፅ የተቋማቱ ነፃነት እየተጣሰ ይገኛል፡፡ የሀሳብ ልዩነታችንን ስናንፀባርቅ ሌላ ትርጉም ሰጥቶ ማሸማቀቅ አልፎም አድርባይ ያልሆኑ መሪዎቻችንን በየመድረኩ በቃላት መወረፍና መፈረጅ እየተለመደና ፋሽን እየሆነ መጥቷል፡፡

እኛ ለሀገራችን እድገት የበኩላችንን ድረሻ ለመወጣት ያለማንም ቀስቃሽነትና ያለምንም ክፍያ የወጣትነት፣ የመዝናኛና የትምህርት ጊዜአችንን ሰውተን የበጐ ፍቃደኝነት አገልግሎት የምንሰጥ አቅሙም፣ ተነሳሽነቱም፣ ቁርጠኝነቱም ያለን ወጣቶች ነን ስራችን የህሊና እርካታን እንጂ ገንዘብን አላማ ያደረገ አይደለም፡፡ ቢሆንማ ኖሮ መንግስት ካሉት አደረጃጀቶች መሀል አንዱን መርጦ በሚያደርገው ዘርፈ ብዙ ድጋፍ ብቻ ለኛ ድጋፍ ይደረግልን ብለን ተስፋ ቆርጠን በተበታተንን ነበር፡፡ የኛ ሀሳብ ግን አይደለም፡፡ እንደውም በተቃራኒው በቅርቡ ከብዙሃን የወጣት ፎረም አመራሮች የሚሰማው ሀሳብ መንግስት በጀቱን ወስዶ ነፃነታችንን ይመልስልን የሚል ነው፡፡

ይህ አሰራር እንዲስተካከል ፍፁም ተቋማዊ ነፃነታችን እንዲረጋገጥ የሁሉም ወጣት አደረጃጀት አባላትና አመራሮች በድፍረት መጠየቅ አለብን፡፡ ያለማንም ሞግዚትነትና መንገድ መሪነት በነፃነት የወጣቱን ጥቅም ለማረጋገጥ መራመድ መቻላችንን የምናሳይበት ጊዜ ዛሬ ነው፡፡ ለእቅዳችንና ለራዕያችን እንጂ ለሌሎች አላማና እቅድ የሚባክነውን ጊዜ ይበቃል ልንለው ይገባል፡፡ ችግሮቹ እንዲፈቱ በየደረጃው የምናደርገው ትግል የሀገራችንና የተቋማችን ፍቅር እንዲሁም የህገ መንግስቱ መከበር ጉዳይ እንጂ ሌላ የተለየ አላማና ፍላጐት መነሻ ያደርገ አይደለም፡፡

በቅርቡ ይህን የሲቪክ ተቋማትን ነፃነት መረገጥን ለማየት ወጣቶች አዲስ የወጣቶች ማህበር መመስረታቸውን አንብበናል፡፡ ይኼኛው አንድ አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ በእኔ እይታ ግን ወደር የሌለው አማራጭ ተቋማችን ነፃ ሆኖ እንዳይንቀሳቀስ ለሚያደርጉ አካላት ተቋሙን ጥሎ ከመሄድ ይልቅ ውስጥ ሆኖ መታገልና የሚመጣውን ሁሉ መቀበል ይመስለኛል፡፡ ይህንን ስል ምቹ የትግል ስልት ተቀይሷል እያልኩ አለመሆኔን ግንዛቤ ይያዝልኝ፡፡ ሁሉንም ጭቆና እና አፈና ተቋቁመን ለውጥ ማምጣት አለብን እያልኩኝ እንጂ፡፡

የሆነው ሆኖ አሁንም በተቋማችን ውስጥ ነን፡፡ ተቋማችንን ጥለንም የትም አንሄድም፡፡ ጥያቄአችንና ትግላችን ግን ይቀጥላል፡፡ ጥያቄዎቻችን ግልፅ ናቸው፡፡ ነፃነታችን ከወረቀት በዘለለ መልኩ ይከበር፣ ክህሎታችን እንጂ ፖለቲካዊ ማንነታችን አይመዘን፣ ከፖለቲካ ነፃ ሆኖ የመኖር መብታችን ተጥሶ የፓርቲ አባል ያልሆንን ወጣቶችን ማስፈራራቱ ማሸማቀቁና ማግለሉ ይቁም፤ ምንም አይነት አስተሳሰብና አመለካከት ቢኖረንም በበጐ ፍቃድ ውዷን ሀገራችንን እያገለገልን የምንገኝ ወጣቶች ነንና ክብር ይሰጠን የሚሉ ህገ-መንግስታዊ መሰረት ያላቸው ናቸውና ድምፃችን እንዲሰማ እንጠይቃለን፡፡ ለወጣቱም ለሀገርም ለመንግስትም የሚበጀው ይህ ብቻ ነውና፡፡

## ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

**የአሳታሚው አድራሻ**
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

**ሥራ አስኪያጅ**
ማስተዋል ብርሃኑ

**ዋና አዘጋጅ**
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

**አዘጋጆች**
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

**ከፍተኛ ሪፖርተሮች**
መሐመድ ነስሩ
ኤልያስ ገብሩ

**ሪፖርተር**
ሰውዓለም ታዬ

**አምደኞች**
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቅጣው እጅጉ
ታዲዮስ ታንቱ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

**የሽያጭ ሰራተኞች**
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

**አታሚ**
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ:- አራዳ
ቀበሌ:- 17
የቤት:- 984

# እስክንድር ነጋን ሳስበው ሳስበው ...፪



ተመስገን ደሳለኝ

ሰኞ ቀንን ደባሪ ነው ይሉታል-በተለምዶ፡፡ ለጋዜጠኛ ግን ሰኞን ከእሁድ የሚለየው እኩል አለመከሰታቸው ብቻ ነው፡፡ በተረፈ በእኛ ሙያ ደባሪ ወይም አስደሳች ቀን የሚለዩት በስማቸው (ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ዕረቡ…) ተብለው ሳይሆን በየቀኑ በሚከሰተው የዜና እና የመረጃ ክብደት ነው፡፡ እናም ሚያዝያ 1 ቀን 2004 ዓ.ም የዋለው ሰኞ ለእኔ ደባሪ አልነበረም፡፡ እንዲያውም በጣም ከተደሰትኩባቸው ጥቂት ቀናቶች አንዱ ነው፡፡ ለምን መሰለህ? በጠቀስኩት ዕለት ከአሲምባ (ከመኖሪያ ቤቴ) እንደወጣሁ ለስራ ጉዳይ የቀጠርኳቸው የተለያዩ ሰዎች ስለነበሩ ፈጠን ፈጠን ብዬ ጉዳዬን ለመጨረስ መዋተት ጀመርኩ፡፡ ሰአቱም እንዲህ እንዲህ እያለ እኩል ቀን ላይ ደረሰ፡፡ እለቱ ብራማ ስለነበር መንፈስን አይጨፈግግም፡፡ እንዲህ አይነት የአየር ንብረት ደግሞ ዘና ስለሚያደርግ ጥቂት የእግር ጉዞ (ወክ) ለማድረግ ይጋብዛል፡፡ እናም የጉዳናውን ጥግ ይዤ አራት ኪሎን ሰንጥቄ ወደ ፒያሳ ድንበር ተጠጋሁ፣ ይህን ጊዜም ድንገት ተንቀሳቃሽ ስልኬ የ‹‹አድምጠኝ›› ኡኡታዋን አሰማች፡፡ ለአፍታ ያህልም የተደወለውን ቁጥር አየት አድርጌ ‹‹ሀሎ›› ስል መልስ ሰጠሁ፣ ከመቅፅበትም በደስታ ሲቃ የታፈነ ድምፅ ምላሽ ሰጠኝ፡፡ የእስክንድር ነጋ ባለቤት ጋዜጠኛ ሠርካለም ፋሲል ነበረች-የደወለችው፡፡ የደስታዋ ድምፅም በውስጤ ሲዘል ይታወቀኛል፡፡ ቦርቅ ቦርቅ፣ ዝለል ዝለል፣ ጨፈቃን ንካ ንካ… የሚል ስሜትም ወረረኝ፡፡ ስልኩን ዘግቼው እንኳ ያ አብሳሪ ድምጽ ማስተጋባቱን አላቋረጠም ‹‹እስክንድርን ፔን ኢንተርናሽናል የ2012 ተሸላሚ ጋዜጠኛ አድርጎ መረጠው፡፡›› ደጋግሞ አቃጨለብኝ፡፡ እንዲህም ስል በጎዳናው ላይ ድምፄ እስኪሰማ ጮኽኩ ‹‹እስክንድር ጀግና ነህና ይገባሃል!!››፡፡

ጥሎብኝ ጀግና እወዳለሁ፡፡ ብዙ ጀግኖች ከልቤ ቀርተዋል፡፡ ዳግማዊ ቴዎድሮስ እና ዳግማዊ ምንሊክን ከልብ እወዳቸዋለሁ፡፡ ስለ አሉላ አባነጋ እና ዘርአይ ደረሰም ባወራ ባወራ አይሰለቸኝም፡፡ በተለይ ደግሞ ብዙ ለፍቶ ተገቢውን ዋጋ ያላገኘው ዘርአይ ደረስ ከምንም በላይ ያሳዝነኛል፡፡ መቼም ዛሬ ዘርአይ በህይወት ቢኖር የሞተላት ኢትዮጵያ ቀኝ ገዢ፣ የተወለደባት ክፍለሀገር ኤርትራ ደግሞ ቀኝ ተገዥ ሆነው ስለተገኙ ተለያይተዋል መባሉን ሲሰማ ምን ሊሆን እንደሚችል ሳስበው ያስደነግጠኛል፡፡ አብዲሳ አጋ፣ ጄኔራል ፋንታ በላይ እና ጄኔራል ኃየሎም አርዕያም እንዲሁ ይመቹኛል፡፡ እነዚህ እንግዲህ የጦር ጀግና ናቸው፡፡ …እንዳልኩህ መንግስቱ ኃ/ማሪያምን እና መለስ ዜናዊን ደግሞ ለመውደድ እና ለመቀበል አስብና አንዳች የሚያስወድድ ምክንያት እያጣሁ ደክሞኝ እተወዋለሁ፡፡ አንዳች እንኳ… በእርግጥ ስህተቱ የእኔ አይደለም፡፡

አሜሪካኖቹ እንደሚሉት ሲቪል ጀግኖችም አሉን፡፡ ከእነዚህ ሲቪል ጀግኖች ለዘላለም የወደድኩት አንድ ሰው አለ-አበበ ቢቂላ የሚባል፡፡ ኦ አቤ የእኔ ጀግና! መቼም አበበ ቢቂላን የማያውቀው የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ በወቅቱ ‹‹የአፍሪካ አባት›› ተብለው ከተሰየሙት አፄ ኃይለስላሴ እንኳን የማይተናነስ ስምና ዝና ነበረው፡፡ ኧረ እንዲያውም የማታ ማታ የውጭ ሀገር ሰዎች ኢትዮጵያን ያስታውሱበት የነበረውን ‹‹የኃይለስላሴ ሀገር›› የምትለው ቅጥያ ‹‹የአበበ ቢቂላ ሀገር›› በሚል እስከመቀየር ደርሰው ነበር፡፡ ይህ ብርቱ ሰው በሮም ኦሎምፒክ ማራቶን፣ ያውም በባዶ እግሩ ሮጦ አሸንፎአል፡፡ ከአፍሪካ የመጀመሪያው የወርቅ ተሸላሚ ሲሆን ከአለምም 42 ኪሎ ሜትርን በባዶ እግር ሮጦ ያሸነፈ የመጀመሪያው ሰው ነው፡፡ አቤ በዛ ኦሎምፒክ ያሸነፈው ማራቶንን ብቻ አይደለም፡፡ የጣሊያን ወራሪን የቅኝ ገዥ መንፈስም ነው፡፡ እንደሚታወቀው የውድድሩ ዕርቀት የሮም አደባባይን መዞርን ያካትት ነበር፡፡ በሮም አደባባይ ደግሞ ከኢትዮጵያ የተወሰደው የአክሱም ሀውልት (በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል) ተገትሮአል፡፡ ምንም እንኳ ሀውልቱ የጣሊያንን ዘራፊነት መስካሪ ቢሆንም፣ ጣሊያኖች ግን የአሸናፊነታቸው ወይም የአድዋን ሽንፈት በቀል ለመወጣታቸው መገለጫ አድርገው ያዩት ነበር፡፡ እናም አቤ ሀውልቱ ጋር ሲደርስ በጣም ፍጥነት ጨመረ፡፡ ይህን የታዘበው ጋዜጠኛም ውድድሩ ከአለቀ በኋላ አቤን ጠየቀው ‹‹ሀውልቱ ጋ ስትደርስ ምን ተሰማህ?›› አቤም መለሰ ‹‹ደም ፍላቴ መጣ!›› እነሆ ይህ ከሆነ ከብዙ አመታት በኋላ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ‹‹‹የአክሱም ሀውልት ለወላይታው ምኑ ነው?›› አሉና አረፉት፡፡ በዚህ አባባላቸውም እነ አቤ ሀውልቱ እንደማይመለከታቸው አረዱን፡፡ እርግጥ ይህ ፖለቲካ ነው፡፡ ሆኖም ጥሩ ያልሆነ ፖለቲካ ስለመሆኑ ግን አንዳች ጥርጣሬ አይግባህ፡፡

የሆነ ሆኖ አቤ በሮም የጀመረውን ድል በቶኪዮም ደግሞታል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም የአካል ጉዳት ከደረሰበት በኋላም በዊልቸር ተወዳድሮ አሸንፎአል፡፡ አይበገሬነት ይሉሃልም ይሄ ነው፤ ሌላ አይደለም፡፡ እስክንድር ነጋ ማለትም ይህ ነው፣ ሌላ አይደለም፡፡ ታስሮም እንኳ አለም ያከበረው፡፡

መቼም ስለዚህ ብርቱ ሰው መፃፍ በራሱ ደስታን ይፈጥራል፡፡ ዛሬ እስር ቤት ከገባ ስምንተኛ ወሩን ይዞአል፤ በታሰረ በ10ኛው ቀን በታተመችው ፍትህ ጋዜጣ ላይ ‹‹እስክንድር ነጋን ሳስበው፣ ሳስበው…›› በሚል ርዕስ ስለወጣው ዳገት፣ ስለከፈለው ዋጋ፣ በምርጫ 97 ማግስት ከነፍሰጡር ባለቤቱ ጋር በቃሊቲ እስር ቤት መግባቱን፣ ባለቤቱም በዛው እስር ቤት የመጀመሪያቸውን ወንድ ልጅ እንደተገላገለች… ፅፌልህ እንደነበር ታስታውሳለህ፡፡ እነሆ ዛሬ ደግሞ ክፍል ሁለትን ልፅፍልህ የተነሳሁት የአለም አቀፍ ተሸላሚ መሆኑን ተከትዬ ነው፡፡ ዜናው በይፋ የተገለፀው የዛሬ ሳምንት ነበር፡፡

እንዳልኩህ እስክንድር ነጋ ተራ ጋዜጠኛ ወይም ተራ የፖለቲካ ተንታኝ አይደለም፡፡ ለእኔ ከእነ አሉላ አባነጋ፣ ከእነ ዘርዕይ ደረስ፣ ከእነ አብዲሳ አጋ ትይዩ የሚቆም የሀገር ባለውለታ ነው፡፡ ሲቪል ጀግና ነው፡፡ ‹‹የያዝኩትን መሬት እንዳለቅ›› የመንፈስ ብርታት የሆነኝም ይህ ሰው ነው፡፡ በዚህ ሰው ዘመን ተገኝተህ፣ በዚህ ሰው ሙያ መሰማራት ደግሞ ምን ያህል ልብ እንደሚያሞቅ ልነገርህ አልችልም፡፡ ልክ ፕሌቶ የተባለው ግሪካዊ ፈላስፋ አምላኩን ‹‹ከምንም በላይ ሶቅራጥስ በነበረበት ዘመን እንድኖር ስላደረከኝ አመሰግንሃለሁ›› እንዳለው አይነት ምስጋናም በልቤ አቅርቤአለሁ፡፡

በእርግጥ እስክንድር ዛሬ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ነው፡፡ ወደቃሊቲ ከመላኩ በፊት ማዕከላዊ ነበረ፡፡ ማዕከላዊ የታሰሩ እስረኞች በወዳጅ ዘመድ እንዲጠየቁ ተፈቅዶላቸው እያለ እሱ አልተፈቀደለትምና ‹‹አይዞህ›› ለማለት እንኳ አልቻልኩም፡፡ ስለዚህም ለወራት አላየሁትም፡፡ ከታሰረ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘሁት ቃሊቲ ከሄደ በኋላ ነው፡፡ ነገር ግን በቃሊቲ ሳገኘው በአካል ከእስሩ በፊት የማውቀውን እስክንድርን አልነበረም፡፡ የመንፈስ ጥንካሬው እና የሞራል ልዕልናው እንዳለ ቢሆንም አካሉ ተጎሳቁሏል፡፡ ፊቱ ጠልሽቷል፡፡ ሰውነቱ በእጅጉ ከስቷል፡፡ እመነኝ ገፅታውን እንዳየከው የማታውቀው ሀዘን ከልብህ ይሰነቀራል፡፡ አንዳች ያህል ምሬትም አፍህን ይሞላዋል፡፡ በዚህ ላይ ገና ‹‹ክፉና ደግ›› ያለየ የአምስት አመት ልጁ አብሮኝ ስለነበረ የአባትና የልጅ ናፍቆት እና ፍቅር ልውውጥን ለመመልከት በእጅጉ ጠንካራ መሆንን ይጠይቃል፡፡ እምባ እንዳይፈስ መታገልንም ይፈልጋል፡፡ ስሜትህ ይደፈርሳል፡፡ ያጥወለውልሀል፡፡ በተለይ የአባትየው የበኩር ልጁን አንገቱ ስር ወሽቆ ግብግብ ሲል ማየት ብቻ ለዘላለም ከአይነ ህሊና የማይጠፋ የስቃይ ስሜት ይፈጥርብሃል፡፡

የሆነ ሆኖ ናፍቆትን ከአንገቱ ስር እንደሸጎጠው ጥቂት ቃላቶችን ተለዋወጥን፡፡

‹‹ምን ሆነህ ነው ሰውነትህ የተጎሳቆለው?››

‹‹ማዕከላዊ እያለሁ አሞኝ ነበር››

‹‹ታዲያ አሁን እንዴት ነህ?››

‹‹በጣም ሰላም ነኝ፣ ተሽሎኛል፡፡ ፍትህ እንዴት ነች? ማዕከላዊ እያለሁ አገኛት ነበር፡፡ እዚህ ግን ስለማይፈቀድ አላገኛትም››

‹‹ደህና ነች፡፡ ስለክሱ ምን እያሰብክ ነው?››

‹‹ክሱ ምንም ይሁን ምን አያሳስበኝም፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ህዝብ እስክንድር ነጋ አሸባሪ እንዳልሆነ ያውቃል፡፡ አንተም ታውቀኛለህ››

‹‹አውቅሃለሁ፡፡ ለሀገርህ ከላይ ታች ስትል ህይወትህን በቅጡ እንዳልኖርክም

ወደ ገፅ 6 ዞሯል »


# አዳዲስ መጽሐፍት በገበያ ላይ

TOP BIOLOGY 7-8
TOP PHYSICS 7-8
TOP PHYSICS 9-10
TOP PHYSICS 11-12
TOP CHEMISTRY 7-8
TOP MATIMATICS 7-8
TOP ENGLISH 5-8
TOP ENGLISH 1-4
Reference Books

NURSING ART COC
NURSING MODALE
ስለህክምና

TOP ENGLISH 1-4
TOP ENGLISH 5-8
አጋዥ

GATEWAY SPOKEN WITH CD
BEST SPOOKEN ENGLISH
ለእንግሊዘኛ ንግግር የሚጠቅም

Mythology
(የአማልክትና የጀግኖች ታሪክ)
አፈ-ታሪክ

መሠረታዊ ሳይንስ 1-4
መሠረታዊ ሳይንስ 5-6
አጋዥ

ወርቃማ የፍቅር ጥቅሶችና
አባባሎች ቁጥር 1 እና2

አዲሱ ሂሳብ አጋዥ 5-6
አዲሱ ሂሳብ አጋዥ 3-4
አጠቃላይ አማረኛ 1-4
ዘመናዊ ስነ-ዜጋ 5-8
አጋዥ

የመኖር ክህሎት
በራስ መተማመን
የጥበብ ፈለግ
የመኖር ጥበብ
አይፈራም ጋሜው
የብቃት መንገዶች
የጣፋጭ ህይወት ሣይንሳዊ ጥበብ
ሳይኮሎጂ

የእንስቷ ትንቅንቅ
አስኳል ቁጥር 3
ሳይኮሎጂ




ክቡራንና ክቡራት ደንበኞቻችን መጽሐፍቶቻችን ለማንኛውም ደረጃ ለሚገኝ ተማሪ አጋዥና የወቅቱን ስርዓተ ትምህርት አሞልተው የያዙ በመሆናቸው ማንኛውም ወላጅ ለልጆቹ ሊገዛቸው የሚችሉ መጽሐፍት ናቸው፡፡ መጽሐፍቶቹን ለማግኘት በማንኛውም የመጽሐፍት መሸጫ መደብሮች ያገኞቸዋል፡፡

ኤች ኬ አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተለያዩ መጽሐፍት በገበያላይ ካዋላቸው ከብዙ በጥቂቱ

# ፍልስፍና



# የልምድ መልክ መያዝ

**ውድ ዶ/ር አድለር**

በሰው ህይወት ውስጥ ልምድ ስላለው ኃይል ብዙ እንሰማለን። ዊልያም ጀምስ ልምድን ‹‹የማህበረሰብ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ መሣሪያ›› ሲል ይጠራዋል። አርስቶትል ደግሞ ‹‹ሁለተኛ ተፈጥሮ›› ይለዋል። ይሁንና ይሄ ልምድ እየተባለ የሚጠራው ተፅዕኖ የሚያሳድር ኃይል ምንድነው? ለምንስ በህይወታችን ውስጥስ ያን ያህል አስፈላጊ ሆነ?

ቢ.ኤች.

**ውድ ቢ.ኤች.**

እስኪ ‹‹ልምድ ሁለተኛ ተፈጥሮ ነው›› በሚለው በአርስቶትል እውቅ ንግግር እንጀምር። ልምድ የመጀመሪያ ተፈጥሮ ከሆነው ከመወለድ ተጨማሪ ሁለተኛው ተፈጥሮ ነው። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የምላሽ ችሎታ እንዲኖረን ተደርጐ ነው የተወለድነው። እንዲሁም በተጨማሪ ደመነፍሳዊ ወይም ድንገተኛ ተብለው በሚጠሩ የተወሰኑ የውስጥ ግፊቶችን ከተፈጥሮ አግኝተን እንወለዳን። በህይወት የምናከናውናቸው እነዚህ ውስጣዊና ተፈጥሯዊ ተግባራት እየበለፀጉ መልክ እየያዙ ሲሄዱ ልምድ ይሰኛሉ።

ለምሳሌ በተደጋጋሚ ልምምድ ብቻ ወደከፍተኛ ክህሎት የሚለወጥና መልክ የሚይዝ ውስጣዊ የተፈጥሮ ችሎታ አለን። በሰዋሰው አሳክተን መናገርን እንማራለን፣ ፊር በያዘ መልኩ ማሰብንም እንማራለን፣ ምግብ ማብሰል ሆነ መኪና ማሽከርከርን እንዲሁ እንማራለን፣ የበረዶ ሸርታቴ ወይም የጠረጴዛ ቴኒስ ጨዋታ እንሰለጥናለን። በዚህ በመማር፣ በመሰልጠንና በመለማመድ የምንይዘው ክህሎት ሁሉ ልምድ ይሰኛል። በእነዚህ ስልጠናዎች ትምህርቶችና ልምምዶች የምናገኘው በውልደት የነበረንን ተፈጥሯዊ ችሎታ ለማዳበር ብቻ ነው።

ለዚህም ነው አርስትቶል ልምድን ሁለተኛ ተፈጥሮ ሲል የሚጠራው። መሰረታዊው ተፈጥሯችን በትምህርትና በተሞክሮ ሊበለፅግ ወይም ሊራቀቅ በሚችል ልምድ ላይ ሥሩን-የሰደደ ነው ማለት ይችላል። የችሎታዎቹ መበልፀግም ሆነ መራቀቅ ለመሰረታዊው ተፈጥሯችን ማሚያ ከመሆኑም ባሻገር ለተጨማሪው ‹‹ሁለተኛ ተፈጥሮ›› በተተኪነት ያገለግላል።

ልምድን መልክ የማስያዝ ፍላጐታችን ደመነፍሳዊ አናሳ እንስሳ ካለመሆናችን ይመነጫል። ለአኗኗር ጠባያችን ብቻ የተመቸ ደመነፍሳዊ የተፈጥሮ እውቀት የለንም። አንዳንድ ደመነፍሳዊ እንስሳት በተፈጥሮ ግፊት በቀላሉ የሚያደርጉትን እኛ ልንማረው ግድ ይሆንብናል። ልክ የሰው ልጅ በሁለተኛ ተፈጥሮ ልምድ እንደሚኖረው ሁሉ ደመነፍሳዊ እንስሳትም እንደወረደ የውርስ ባህርያዊ እውቀት አላቸው። ቀዳማይ ተፈጥሯዊ ጠባያችን ከህይወት ጋር ጠንካራ ቁርኝነት በማሳየቱ ይለያል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉንም ነገር እንዳስፈላጊነቱ ለማበጃጂያ የሚያገለግል መጠሪያም ነው። በእራሳችን መልክ-መልክ የምናስይዘው ልምድ ደግሞ ቀዳማይ ተፈጥሯዊ ጠባያችንን ሊያስተካክለው እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። ሁለቱም አማራጭ ላይ የተመሰረተ ተስተካካይ ጠባይ ያላቸው መሆኑ ደግሞ ያመሳስላቸዋል። ጠባያችን፣ ልናጠናክር፣ ልናሰንፍ ወይም ልንተው እንዲሁም በሌሎች ልንተካ እንችላለን። እንደ ቀዳማይ ልምዳችን ሁሉ ሁለተኛው ተፈጥሯችን እንደየአለንበት የእድሜ ደረጃ ተመሳሳይና ተለይቶ የሚታወቅ ጠባይ ሲያላብሰን ይታያል። የአንድን ሰው ጠባይ ጠንቅቀህ የምታውቅ ከሆነ በየትኛው የእድሜ ክልል እንዳለ ለመገመት አያዳግትህም። የሚወድና የሚጠላውን ለመገመት ቀላል ነው።

የልምድን መልክ መያዝ ከግለሰብ አንፃር ይሄን ያህል ተመለከትን። በማህበረሰብም ደረጃ ተዘውታሪ እሳቤና ድርጊቶች አሉ። እነዚህ የወል ማህበረሰባዊ ‹‹መንገዶች›› ልማድ ይሰኛሉ።

ልማድ ነገሮች እና መሰረት የማይዙበት ዘዴ ነው ማለት ይቻላል። የጋራ ህይወት መልክ እንዲይዝም የሚያደርገው ልማድ ነው። በግለሰቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በቀላሉ እንዲከናወንና እንዲሰልጥም ይኸው በጋራ የተያዘ ልማድ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ወደ አንድ አዲስ አካባቢ ሄደን አዲስ የሚሆንብን ልማድ ተለማምደን እንጠቀምበት ድረስ መኖር የሚያዳግተን ለዚህ ነው (እንደ ፕላኔቶች ህግ የተመጠነ ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴ እንዲኖርና ውል እንዳይስት የሚያደርግ ማዕከላዊ ኃይል)

ጀምስ ይሄንን ውስጣዊ ግንዛቤውን በማህበረሰብና በግለሰብ ባህርያት ላይ ተርጉሞ ለማሳየት ሞክሯል። የአብዛኞቻችን አንጉል ጠባይ ተግባር ላይ የሚውለው ከ30 ዓመታት እድሜ በኋላ ማለትም ባለንበት ህይወት ከረካንና በማህበረሰባዊው ተመጋጋቢ እንቅስቃሴ የበቂያችንን ያህል ከተጠቀምን በኋላ ነው ይላል። ግንዛቤያችን፣ ባህሪያችን፣ ንግግራችን፣ እሳቤአችንና ማህበራዊ ጠባያችን እንደየሁኔታው በአማካኝ ሃያኛ ዓመት እድሜያችን ላይ ስንደርስ መሰረት ይዘው የአይለወጤነት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። ስለዚህ እንደመሬት ስበት ጠንካራ የሆነውን ማህበራዊ ምህዋራችንን አጥብቀን መያዝ የምንጀምረው ያኔ ነው ይላል ጀምስ።

ያም ሆነ ይህ አሮጌውን ልማድ ነቅሎ በአዲስ ልማድ የመተካት ሙከራ አዳጋች ብቻ ሳይሆን የማይቻልም እንደሆነ ማስታወስ ተገቢ ነው። አንድ ልማድ አንዴ በላያችን ላይ መሰረቱን ከጣለ በኋላ ፈፅሞ የማንቆጣጠረው ኃይል ሆኖ ይሰለጥንብናል። ነገር ግን ሰብዓዊ ልማዶች መሰረት የሚይዙት እኛ የምንፈጥራቸውን የተለያዩ ምርጫዎች ተገን አድርገው በነፃነት በመሆኑ በተመሳሳይ ሌሎች ምርጫዎችን በማቅረብ ልማድን በልማድ መተካት የምንችልበት እድል ይኖራል ብሎ የሚያስበው ደግሞ የአየርላንዱ ፀሐፌ ተውኔት ጆጅ ባርናንዶሾ ነው "Pygmalion" ወይም "My fair lady" በተሰኘ ተውኔቱ ላይ ‹‹ምንም አይነት ልምድ ይሁን፣ እንዴትም ያለ ጠንካራ፤ የመቀየር ነፃነታችንን ሊነጥቀን አይችልም›› ይላል። እንዳለውም ተስፋ በሚፈነጥቀው ተውኔቱ ሊዛ ዱሊትል የተሰኘች ገፀ ባህርይ አዳጋች ሆኖባት የነበረውን እንደወይዘሮዎ የመናገር ብቃት ትጐናፀፋለች። በልምድ ላይ ድል መጐናፀፍ ይሏል ይሄ ነው።

# እስክንድር ነጋን ... ከገፅ 5 የዞረ

አውቃለሁ። ብቻ አይዞህ በርታ››

‹‹ለእኔ አታስብ አንተ በርታ። ስራህን በጥንካሬ ስራ››

ይህንን ጊዜ ጭውውታችንን ጠጋ ብሎ ያደምጥ የነበረው የማረሚያ ቤቱ ፖሊስ ‹‹በቃ! ሰዓት ደርሶአል›› ሲል በትህትና አቋረጠን። ሆኖም በዚህ መሀል በፍጥነት ስለክሱ፣ እንዲሁም ድንገት በፍርድ ቤት ተከላከል ቢባል እንኳ እውነቱን የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቀው ዘንድ እንዴት መከላከል እንዳለበት ስለመከላከያ ምስክሮቹ አውርተን ተለያየን።

ምሬት በልቤ እንደገባ የወህኒ ቤቱን ግቢ ለቀኩ። ...ብዙ ነገርም አሰብኩ፣ ብዙ ነገር... ግና ምን ማድረግ ይቻላል? ለራሴ የጠየኩት ጥያቄ ነው። እኛስ ብንሆን እስከመቼ ነው ‹‹እከሌ ታሰረ፣ እከሌ በይቅርታ ተፈታ፣ እከሊት ተፈረደባት... እያልን ዜና ስንሰራ የምንውለው? በዚህ አጀንዳስ ሰለምንድን ነው ‹ቢዚ› እንድንሆን የተደረግነው? እኮ ሀገሩን የሚወድ፣ ለሀገሩ ራዕይ ያለው እየታሰረ፣ ራዕይ የሌለው እያሰረ እስከመቼ...›› ያጨናነቁኝ ጥያቄዎች ቢሆኑም ምላሽ እንደሌላቸው አውቃለሁ። እለቱ ደባሪ ሆነብኝ። የእስክንድር ገፅታ፣ ከልጁ ናፍቆት ጋር ናፍቆቱን ለመወጣት ያደርግ የነበረው ነገር በሙሉ ደጋግሞ እየመጣብኝ ቀኔን ብልሽትሽት አደረገው። ደግነቱ የቱንም ያህል ብከፋ፣ የቱንም ያህል ባዝን፣ የቱንም ያህል... ተስፋ የመቁረጥ ስሜት አይመጣብኝም። ይህማ እንዴት ይሆናል? ጉዳዩ የሀገር ጉዳይስ አይደል እንዴ? ያውም የምንወዳት ኢትዮጵያ። (መቼም ኢትዮጵያውን ለኢትዮጵያ መሞታቸው እንደሁ ዛሬም አላቋረጠም። ዘላለማቸውን ለማምረት፣ ለመማር፣ ለመፍጠር... ሳይሆን ለመብት ትግል የተፈጠሩ ያልተሳካላቸው ባተሌ ታጋዮች... ዳሩ የሀገር አንድነት ሲናጋ እና አንዱ ብሄር በሌላው ላይ እንዲነሳ የሚጋብዝ ፖለቲካ በስራ ላይ ሲውል ‹‹አሻፈረኝ›› ብለን ካልሞትን መቼ ልንሞት ነው? አዎ! አሊያማ ‹‹ኢትዮጵያ የእኛ መመኪያ...›› ዘፈን ብቻ ሆኖ ሊቀር ነው?)

የሆነ ሆኖ በቀጣዩ ሳምንትም ይህን ጀግና ለመጠየቅ አስቤ ለባለቤቱ አብረን እንሄድ ዘንድ ደወልኩላት። ሆኖም የመለሰችልኝ መልስ ምድርና ሰማዩን አዞረብኝ። ነገር አለሙ ድብልቅልቅ አለብኝ። የጋዜጠኛ ሠርካለም አጭር መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡-

‹‹ውይ! ተሜ ባለፈው ጠይቀከው ከሄድክ በኋላ ከእኔ፣ ከልጁ እና ከአንዲት ዘመዳችን በስተቀር ማንም ሰው እንዳይጠይቀው ተደርጓል!››

አሁን ጩኸ፣ ጩኸ... አለኝ። ግና ምን ብዬ ልጩኸ? ወደማንስ ነው የምጮኸው? አምስት ልጆች የወለደችለትን የሰማኒያ ሚስቱን በመጥረቢያ ጨፍጭፎ የገደለ ወይም በጠራራ ፀሐይ ማጅራት ሲመታ የተያዘ... ያለገደብ በወዳጅ ዘመድ ሲጠየቅ፤ ከእነ አብዲሳ አጋ እና ዘርዐይ ደረስ ተርታ የሚሰለፈው የሀገር ባለውለታ እስክንድር ነጋ በሶስት ሰው ብቻ፤ እሱም በውስን ሰዓት (ከሰኞ እስከ አርብ ለ10 ደቂቃ፣ ቅዳሜ እና እሁድ ለ30 ደቂቃ) እዚህ ሀገር ምንድር ነው እየተደረገ ያለው? በዚህስ ሁኔታ እስከ መቼ ነው የምንዘልቀው? 40 ወይስ 50 አመት? በሀገሪቱ ህገ-መንግስት መሰረት እንኳ ‹‹መታሰር›› የማይቻልበት ሁኔታስ ወዴት ያደርሰናል? አስረው ሲያበቁ ጠያቂ መገደብ፣ ሲያሻቸው በእስረኛ ማስደብደብ.. ታዲያ የትኛው ነው ህጋዊ? ታሳሪው ወይስ አሳሪው? መልሱልኛ? መልስ አለን የምትሉ ካላችሁ።

ደግሞ እኮ ጉዳዩን የከፋ የሚያደርገው ይህ አይነቱ አሰራር አዲስ ያለመሆኑ ነው። ንግረኝ ካልክ እነግርሀለሁ፣ በዚህች ሀገር ማንም ይሁን ማን፣ የቱንም ያህል ለሀገር የለፋ ይሁን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተቃዋሚ ከሆነ እንኳንም ቆሞ ሞቶም አድሎ እና በደል አይቀርለትም። ለዚህም ማጠናከሪያ የሚሆን አንድ ምሳሌ እንይ።

ደህና! በእድሜዬ በሀገር ባለውለታዎች ስርዓተ ቀብር ላይ የተገኘሁት ለሁለት ሰው ብቻ ነው። ለፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ እና ለእጅግ የተከበሩ የአለም ሎሬት ሚትር አርቲስት አፍወርቅ ተክሌ (በእርግጥ በስራ ምክንያት ሳይመቸኝ ቀርቶ ቀብራቸው ላይ መገኘት ያልቻልኩት አንድ ሶስት የሀገር ባለውለታዎች ነበሩ፤ እነሱን ባለመቅበሬ ዛሬም ድረስ ይቆጨኛል)

ሆኖም የእነዚህ ሁለት ሰዎች የቀብር ስነ ስርዓት ጉራሜይሌ ነው። እንዴት አይነት ጉራማይሌ ይሆን? ብለህ ከጠየክም መልሱ እንዲህ የሚል ነው። ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ አርበኛ ናቸው። አርበኛ ብቻም እንዳይመስሉህ ይልቁንም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን በፕሬዝዳንትነት የመሩ፣ ለ40 ዓመት ከአፍሪካ ምርጥ የቀዶ ጥገና ሀኪም ሆነው ሳለ ከሀገራቸው ኢትዮጵያ ሳይወጡ ያገለገሉ ናቸው። ነገር ግን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተቃዋሚ በመሆናቸው እና ኤርትራን አታስገንጥሉ፣ አንዱን ብሔር በሌላው ላይ አነሳስታችሁ አታጨራርሱ... በማለታቸው እስር ቤት ገቡ። በእስር ቤትም በጠና ታመው ሳለ በቂ ህክምና ሳያገኙ ቀርተው ነፍሳቸው ከስጋቸው ልትለይ ሰዓታት ሲቀር ለህክምና እንዲወጡ ፈቅደናል የሚል ቧልትን ተከትሎ እንዲወጡ ተደረገ፤ ህይወታቸውም በዛው አለፈ። ስርዓት ቀብራቸው ግን እንደብዙዎቻችን እንዲካሄድ ተወሰነ። ሌላው ቀርቶ የአርበኞች መቀበሪያ በሆነው የቅድስት ስላሴ ካቴድራል እንኳ እንዲቀበሩ አልተፈቀደላቸውም። እናም በባለወልድ ቤተክርስቲያን ተቀበሩ። ወዳጄ! ኢህአዴግ ከጠላህ እንዲህ ነው፤ ሬሳህንም ቢሆን ሳያንገላታው አይለቀውም።

አሁን ደግሞ እጅግ ወደ ተከበሩ ሎሬት ሚትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የቀብር ስነስርዓት እንመለስ። መንግስት በይፋ ኮሚቴ አዋቅሮ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ጀምሮ ሁሉም ሚኒስትሮች የአበባ ጉንጉን ልከው፣ ስርዓተ ቀብሩ በቀጥታ የቴሌቪዥን ሽፋን አግኝቶ በስላሴ ካቴድራል ተፈፅሟል። ይህ ሁሉ ስርዓትም ሆነ የመንግስት ተሳትፎ ለአንጋፋው ሰዓሊ ቢያንሳቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይደለም። ምክንያቱም አፈወርቅ ኢትዮጵያን ያስጠሩ ታላቅ ባለውለተኛ ናቸውና የቀብር ስርዓታቸው ከዚህ በተሻለ ሁኔታም ቢደምቅ የሚከፋ አይኖርም።

ጥያቄው ግን ሌላ ነው። ለምሳሌ አፈወርቅ አንድም ቀን ፖለቲካ ውስጥ (በተቃውሞም በድጋፍም) ገብተው አያውቁም። እናም በኢህአዴግ ‹‹ጥቁር መዝገብ›› ውስጥ ስማቸው የለም። ችግር ይኖር የነበረው በዚህ መዝገብ ቢሰፍሩ ነበር። አዎን! አፈወርቅ ተክሌ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተቃዋሚ ቢሆኑ ኖሮስ? ብለን ካሰብን እመነኝ ቀብራቸው እንዲህ ሊሆን ቀርቶ ከፕሮፌሰሩም ያነሰ ይሆን ነበር። አየህ! ይህ ነው የሚደብረው። ይህ ነው መንግስትና ፓርቲ የተደበላለቀበት ፖለቲካ ማለትም። ምክንያቱም አፈወርቅ የኢህአዴግ ተቃዋሚ ቢሆኑ እንኳ ይህ ሁሉ የሀገር ባለውለታነታቸውም ሆነ የአለም ምርጥ ሰውነታቸው ሊቀንስ ወይም ሊሰረዝ አይችልም። ፖለቲካ ሌላ ነው፤ ሀገር ደግሞ ከዛ የሰፋ ትልቅ ነገር ነውና። ሚዛኑም እንደ መንግስት እንጂ እንደ ፓርቲ ሊታይ አይገባውም። አስራት ወልደየስ የቱንም ያህል የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተቃዋሚ ቢሆኑም አርበኝነታቸው፣ ዩኒቨርስቲውን በፕሬዚዳንትነት መምራታቸው እና ለ40 አመታት ሀገራቸውን ከማገልገላቸው ጋር አንዳች የሚያያዘው ነገር የለም። ከተያየዘ መጥፎ ነው። መጥፎ ፖለቲካም ይሉሃል ይህ ነው። በእርግጥ የዚህ አይነቱ ፖለቲካ ሰለባ አስራት ወልደየስ ብቻ አይደሉም። ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህንም ናቸው። ልክ እኮ ነኝ! የእኒህ አንጋፋ የጥበብ ሰው ሞት ለኢህአዴግ ከዊትኒ ሆስተን ሳይቀር ያነሰ ነበር። ምክንያቱም የዊትኒ ሞት በመንግስት ሚዲያ የተጋነነ ሽፋን ሲያገኝ፣ የሎሬትን ግን ያነሳውም የለም። ፀጋዬ ገብረመድን ሀገሬን አትከፋፍሉ፣ ኢትዮጵያዬን አትግደሉ፣ ታሪካችንን አታበላሹ... ያሉት ነገር በዛ በጥላቻ መዝገብ እንዲሰፍሩ አድርጎአቸዋልና ነው።

የእስክንድርም ጉዳይ እንዲሁ ነው። እስክንድር በምንም ወንጀል ተጠርጥሮ ይታሰር፤ ነገር ግን ህገ መንግስቱ ከሰጠው የታሳሪዎች መብት አንዳች ሊሸረፍበት አይገባም። የመሸረፍም ስልጣን ያለው ማንም እንደሌለ ራሱ ህገ-መንግስቱ ይናገራል። በእርግጥ በኢትዮጵያ ህግ-መንግስቱ ጉራማይሌ ነው። ይህ የሆነው ደግሞ ኢህአዴግ በተግባር ሲሸርፈው ‹‹ህጋዊ ነው›› ወይም ‹‹ሽብርተኝነትን ለመከላከል ነው›› የሚሉት ፈሊጥ በሰበብነት ሲቀርብ በፀጋ በመቀበልህ ነው። በግልባጩ ደግሞ ተቃዋሚዎች በሀሳብ ‹‹ሲሸርፉት›› ወይም ‹‹ይህ አንቀፅ ኢትዮጵያን ይከፋፍላልና ለህዝበ ውሳኔ ይቅረብ›› ሲሉ ሽብርተኝነት ነው ይልሀል የኢህአዲግ የጫወታ ህግ። ሆኖም በዚህ ቅር አይበልህ፣ ምክንያቱም ያለህበት ሀገር ከአያት ቅድመ-አያትህ የወረስካት ያችህ የታሪክ ሀብታሟ ኢትዮጵያ ሳትሆን ጀግናው ኢህአድግ በብሄር ፖለቲካ ጠፍጥፎ የሰራት ነች። ለዚህም ነው የቀድሞዋን ኢትዮጵያ እንፈልጋት የምልህ። ወይም እናስመልሳት የምልህ።

**ሌላ ጉራማይሌ**

ደህና! ሌላ ጉራማይሌ እንይ፣ የኢትዮጵያ መንግስት ‹‹እስክንድር ነጋ አሸባሪ ነው›› ሲል አስሮታል። በሌላ በኩል ደግሞ አለም አቀፉ ‹‹የፀሀፊዎች ነፃነት›› ተቆርቋሪ የሆነው "Pen International" ሚያዚያ 5 ቀን 2004 ዓ.ም. "Journalist Eskinder Nega wins 2012 PEN Freedom Award" በሚል ርዕስ ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ እስክንድር ነጋን ‹‹a leading advocate for press freedom and freedom of expression in Ethiopia›› (በኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት እና ሀሳብን በነፃ የመግለፅ መብት እንዲከበር በመሪነት የተጋ) ሲል አሞካሽቶታል። ፔተር ጎድዊን የተባሉ በአሜሪካ የፔን ኢንተርናሽናል ማዕከል ሊቀመንበርም እስክንድርን የገለፁት እንዲህ ሲሉ ነው፡-

"The Ethiopian writer Eskinder Nega is that bravest and most admirable of writers, one who picked up his pen to write things that he knew would surely put him at grave risk."

(ኢትዮጵያዊው ፀሐፊ እስክንድር ነጋ ደፋርና በእጅጉ የሚደነቅ ፀሐፊ ነው። ብዕሩን ሲያነሳ የሚፅፍባቸው ነገሮች በእርግጠኝነት አደገኛ አደጋ ሊያመጡበት እንደሚችሉ ሁሉ ያውቃል)

የ"Freedom to write program" ዳይሬክተር ላሪ ሳይመሰ ደግሞ ለእስክንድር ያላቸውን አድናቆት የገለፁት "He is truly an extraordinary individual" (እጅግ ልዩ ሰው) ሲሉ ነበር።

የፔን ኢንተርናሽናል መግለጫ እንደሚያትተው እስከዛሬ ድረስ 46 ሰዎች የዚህ ሽልማት ተሸላሚ ሲሆኑ፣ 37ቱ በእስር ላይ ሳሉ የተሸለሙ ቢሆንም፣ ከእነዚህ እስረኛ ተሸላሚዎች መሀከል 33ቱ እንደተሸለሙ ወዲያውኑ ከእስር ተለቀዋል። እናስ! እስክንድር ይህን ቁጥር በአንድ ይጨምረው ይሆን?

እንግዲህ እስሩን ጉራማይሌ የሚያደርገው፣ ፖለቲካውን ደግሞ አደገኛ ቅርቃር ውስጥ የሚከተው ይህ ነው። እናም መልስ የሚያስፈልገው ጥያቄ ሆኖ የሚወጣው ከዚህ ቅርቃር የምንወጣው ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ይከበር ዘንድ የተጉትን በማሰር እና በማሳደድ ወይስ በአሸባሪነት ከሶ ወህኒ በመወርወር? የሚለው ነው። እርግጥ ነው የዚህን ጥያቄ መልስ የሚያውቁት የስርዓቱ መሪዎች ብቻ ናቸው።

# ዜጎችን ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ የማባረር ሂደት ከህገ-መንግስቱ አንፃር

በሽንቁጥ አየለ
shenkutayele@yahoo.com

በብሔራቸው አማሮች የሆኑ አርሶ አደር ዜጎች ከቤንች ማጂ ዞን ከጉራፋርዳ ወረዳ ሀብት ካፈሩበት፣ በህጋዊነት መሬት ይዘው እየገበሩ እያረሱ ከኖሩበት ቀያቸው አገራችሁ አይደለም፣ ደን ጨፍጭፋችሁዋል፣ ሀብታም እየሆናችሁ ባካባቢው ነዋሪ ላይ ተፅዕኖ ፈጥራችሁዋል በሚሉ ሰበቦች እንዲባረሩ እየተደረገ መሆኑን ልዩ ልዩ ሚዲያዎች በስፋትና በጥልቀት እየዘገቡት ይገኛሉ።

ስለተባረሩ ሰዎች ክልሉ በመገናኛ ብዙሃን የተለያዩና የሚቃረኑ መግለጫዎችን ሲሰጥ ይሰማል፡ ፡ የፌደራል መንግስትም በጉዳዩ ላይ ያለውን አቋዋም ግልፅ አድርጎ አስቀምጦአል። ከመንግስት ወገንም ሆነ ከተለያዩ አካላት ድርጊቱን በመደገፍና በመቃወም የተለያዩ መግለጫዎች ቢሰጡም የህገ-መንግስቱ የባለስልጣናትን ስነ ባህሪና ድርጊት ገዥነት ብሎም የውሳኔያቸው ብቸኛ መሰረት ሊሆን እንደሚገባው በጥልቀትና በስፋት ሲተነተን አይስተዋልም። የዜጎች ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ የመባረር ጉዳይ መሰፈርና መለካት ያለበት ሀገሪቱ ካላት ህገ-መንግስት ማዕቀፍ አንፃር ብቻ እንጅ ፖለቲከኞች፣ ባለስልጣኖች ወይም ተቃዋሚዎች ከሚሰጡት ትንታኔ አንፃር ሊሆን አይገባም። ስለዚህ የዚህ ፅሁፍ ዋና አላማ ይህ ድርጊት ከህገ-መንግስቱ አንፃር ምን አንደምታ አለው? ለመፃኢቱ ኢትዮጵያስ ምን ትውፊታዊ እሴት ሊያወርስ ይችላል? የሚሉት ነጥቦችን በተወሰነ ደረጃ ለመዳሰስ መሞከር ነው።

1. በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የመኖር መብት

በህገ-መንግስቱ መሰረት ወላጆቹ ወይም ከወላጆቹ አንዱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነው (አንቀፅ 6/1)። ኢትዮጵያዊ ዜጋ ደግሞ በህገ-መንግስቱ የተቀዳጃቸው መብቶች አሉት። እነሱም በህግ ይጠበቁለታል። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከፈቃዱ ውጭ ዜግነቱ ሊገፈፍ አይችልም (አንቀጽ 33/1 )፡ ፡ ደግሞም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት የሚያስገኘውን መብት፣ ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለው (አንቀጽ 33/2).። ህገ-መንግስቱ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመዘዋወር ነፃነት በአንቀፅ 32 አጎናፅፎአል። ወላይታ፣ ሲዳማ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሊ፣ ሐረሪ፣ ትግሬ ወይም ሌላ ብሄርን ሳይጠቅስ ስለመዘዋወር ነፃነት እንዲህ ይላል፡- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በህጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖርያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት አለው። ሆኖም የደቡብ ክልል መንግስት ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች ከክልሉ እንዲባረሩ በደብዳቤ ሲያዝ ከላይ የተጠቀሱ ህገ-መንግስታዊ አንቀፆችን ያገናዘባቸው አይመስልም። አንድ ሰው ከኢትዮጵያ ከየትኛውም አቅጣጫ ቢመጣም በአንድ የክልል ሀላፊ በተሰጠ የደብዳቤ ትዕዛዝ የዜግነት ህገ-መንግስታዊ መብቱ ሊጣስ አይገባም።

ደግሞም የክልሉ ፖለቲከኞች ሲናገሩ እንደሚደመጠው ክልሉ ያባረራቸው ህገ-ወጥ የሆኑትን ከሰሜን አማራ የመጡ ዜጎችን ነው። ለመሆኑ አንድ ዜጋ ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ሲንቀሳቀስ ህጋዊ ያልሆነ ዜጋ ሊያስብለውና ከዚያ ክልል እንዲባረር የሚያስደርገውምን ህገ-መንግስታዊ አንቀፅ አለ? ህገ-መንግስቱ የዜጎችን የመዘዋወርና መኖሪያን እና ስራን የመምረጥ መብትን አረጋግጦአል። አንድ ዜጋ ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ሲሄድ የክልሉን እና የአካባቢውን አስፈላጊ ህጎች እንዲያሙዋላ ይጠየቃል እንጂ ከሌላ አካባቢ መጣህ ተብሎ ከአካባቢው አይባረርም። ምንም እንኩዋን ክልሉ ህጋዊነት የሌላቸውን አባረርሁ ብሎ ቢናገርም የተባረሩት ዜጎች ደግሞ ግብር የገበሩበትን ካርኒ ሁሉ ሲያቀርቡ ተስተውለዋል። ሆኖም ዋናው ጥያቄ አንድ ክልል ከሌላ ክልል የመጣ ኢትዮጵያዊ ዜጋን የማባረር ህገ-መንግስታዊ ስልጣን አለው ወይ? የሚለው ጉዳይ ነው።

2. የዜጎች ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች

የማንኛውም ኢትዮጵያዊ የኢኮኖሚ የማህበራዊና የባህል መብቶች ሊከበሩለት እንደሚገባ በህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 43 ስር እንዲህ ሲል ተብራርቶአል፡-

- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ዉስጥ በማንኛውም ኢኮኖሚዊያ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ስራ የመስራት መብት አለው (43/1)
- ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው (43/2)
- መንግሰት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ስራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል (43/6)
- መንግስት ዜጎች ጠቃሚ ስራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል (43/7)
- ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች ኢትዮጵያውያን በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውና ለምርት ካደረጉት አስተዋፅኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው። መንግስት የኢኮኖሚና የማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ መርህ መመራት አለበት (43/8)

ሆኖም ይህን የመሰለው ውብ የህገ-መንግስት ክፍል ጉራፋርዳን አገራችን ብለው በአካባቢው ለብዙ ጊዜ ሰፍረው ይኖሩ የነበሩ ዜጎች ጋ ሲደርስ ክፋኛ ተጥሶአል። ግብርና ሙያን መርጠው በጥረታቸውና በጉልበታቸው ድህነትን አሸንፈው በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ በትጋት እየተሳተፉ ያሉ ዜጎችን ለማፈናቀል ከተሰጡ ምክንያቶች አንዱ ሀብታም እየሆናችሁ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ ጫና ታመጣላችሁ የሚል ነው። እናም አማሮቹ ገበሬዎች ይህ ህገ-መንግስታዊነት ቀርቶ የልማት ፅንሰ ሀሳብ ሊገልፀው በማይችል ህሳቤና ሰበብ ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ ይባረራሉ።

የክልሉ መንግሰት በአንቀፅ 43/8 እንደ ተደነገገው እነዚህን አርሶ አደሮች ሊያበረታታ እና ኑሮአችውም እንዲሻሻል ማገዝ ሲገባው ከቤታቸው ገፍትሮ በማስወጣት ያፈሩትን ሀብት እንኳን በቅጡ ለማደራጀት ጊዜ ሳይሰጣቸው አስገድዶ ያባርራቸዋል። ይህን ጉዳይ ሪፖርተር ጋዜጣ፣ አዲስ አድማስ ጋዜጣ እና ፍትህ ጋዜጣ በስፋት የዘገቡት ሲሆን የውጭ ሚዲያዎች የነገሩን ክብደት አፍታትተውና አብራርተው ለማቅረብ የተፈናቃዮችን ምስክርነት እያጣቀሱ አቅርበውታል። ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተለው፣ለተፈናቃዮችም መጠለያ በመስጠት፣ የተለያዩ የተቃውሞ መግለጫዎችን በማውጣት፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩም የተቃውሞና የተማፅኖ ደብዳቤ በመፃፍ የሰዎች መባረር እንዲቆም የጠየቀው ብሎም ግንባር ቀደሙን ሀገራዊ ሚና እየተወጣ ያለው ተቃዋሚው የፖለቲካ ፓርቲ የሆነው መኢአድ ደግሞ በቢሮው ለተፈናቃዮች መጠለያ ከመስጠት እስከ ምግብ ማቅረብ ተራምዶ ተፈናቃይ ገበሬዎችን በቻለው ሁሉ ለመርዳት ሲረባረብ ተስተውሏል።

ለመሆኑ በጥረታቸው ሀብት ያፈሩሰዎችን፣ የዜግነት መብታቸውን ተጠቅመው በሀገሪቱ ተዘዋውረው ግብርናን ስራ አድርገው በመምረጥ በግብርና ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ከሀገራቸው ማባረር ነው የሚገባው ወይስ በኢኮኖሚ እንዲጎለብቱ፣ በባህል እንዲጠናከሩ በልዩ ልዩ ፖሊሲዎች መደገፍ ነው ተገቢው ህገ መንግስታዊ ትዕዛዝ? ዜጎች በመረጡት አካባቢ ለመኖር እና በመረጡት ስራ ለመተዳደር ተዘዋውረውም የተሻላቸውን አካባቢ መርጠው መኖር መጀመራቸው ህጋዊ አካሄድ መሆኑን የክልሉ መንግስት ለምንድን ነው የማይቀበለው?

ክልሉ የሚሰጣቸው ምክንያቶች በሙሉ በህገመንግስቱ መነፅር ሲቃኙ የዜጎችን ህገመንግስታዊ መብት የሚንዱ እንጂ በምንም መልኩ ህገመንግስታዊ መሰረት የላቸውም። እንደሚታወቀው ህገመንግስቱ የህጎች ሁሉ የበላይ መሆኑ ቢታወጅም ይህ ህገመንግስት አሁን የተፈናቀሉት ሰዎች ላይ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቶአል። ከሰሜን አማራ የመጡ ዜጎች ደቡብ ኢትዮጵያን ስለተቆጣጠሩት ወደ መጡበት እንመልሳቸው ማለት ከላይ የሰጠነውን የዜግነት መብት መንጠቅ ስለሆነ ህገመንግስቱንም መናድ ነው፡ ፡ ለመሆኑ ክልሉ ከህገመንግስቱ በላይ የሆነ ተጠይቅና ህግ መፍጠር ይችላል ወይ? ወይስ ህግ አስፈፃሚዊ የመንግስት አካል በመሰለውና ያዋጣኛል ባለው መልክ ብድግ እያለ ህገመንግስቱ ውስጥ የቆሙ መሰረታዊ የህግ መርሆችን ሳያገናዝብ የራሱን አስተዳደራዊ ትንታኔዎች መስጠት ይችላል ወይ?

ዛፍ ሲመነጥሩ ስለተገኙ ተባረሩ የሚለው ሰበብ በህገመንግስቱ ውስጥ ከተዘረዘሩት የዜጎች መብት ጋር ሊሄድ የሚችል ጉዳይ አይደለም።

ምናልባትም ከመሃላቸው ጥፋተኛ ከተገኘ በአካባቢው ህግ እንደ ማንኛውም አርሶ አደር ፍርድ ቤት ቀርቦ መቀጣትና መታረም እና ዳለበት እሙን ነው። ሆኖም ከሰሜን አማራ የመጣ ዜጋ ስለሆነና ዛፍ ሲመነጥር ስለተገኘ ወደ ሰሜን አማራ መልሱት ማለት የዜጎችን ህገመንግስታዊ መብት መጣስ ነው።

ህገ መንግስቱም ለአካባቢ ጥበቃ ህጋዊ አካሄዶችን አንደሚከተለው በአንቀፅ 92 አስቀምጦአል፣-

- መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖር የመጣር ሀላፊነት አለበት (92/1)
- የህዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ስራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ህዝብ ሁሉ ሀሳቡን እንዲገልፅ መደረግ አለበት (92/3)
- መንግስትና ዜጎችች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው (92/4)

እንግዲህ ህገመንግስቱ አንድ የተረዳው ነገር አለ። የማህበረሰብና የዜጎች ተሳትፎ በሚወጡ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ ወሳኝ መሆኑን፡ ፡ ይህም ማለት የህዝቡ ተሳትፎ ከሌለ በማህበረሰቡ ዘንድ ስለሚወጡ ፖሊሲዎች የግንዛቤ ዝቅተኛነት ሊኖር ስለሚችል ማህበረሰቡን በፖሊሲ ቀረጻ ላይ በማሳተፍ ፕሮጋራሞችን የራሱ እንዲያደርጋቸውና አካባቢውን የመንከባከብ ግዴታም እንዳለበት እንዲረዳ የማድረግ ስራ መሰራት እንዳለበት ያስረዳል፣ የህጎች የበላይም ነውና ያዛል።

ይህ አስተሳሰብ ደግሞ በተሳትፎአዊ የልማት ሳይንስም ተቀባይነት ያገኘ አስተሳሰብ ነው። በሁሉ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ቀረፃ ላይ ህዝቡ ይሳተፍ የሚለው የዘመናችን ቁልፍ መርህ እየሆነ መጥቶዋል። ያንጊዜም ህዝብ የሚከናወኑ ልማቶችን እና ስራዎችን የራሱ የማድረግና በአካባቢም ሆነ በልማት ስራዎች ላይ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ጥፋትን አይፈጽምም።

ሆኖም ዜጎች አንድጠፋት ሲያጠፉ ማባረርያውም ከሰሜን አማራ የመጡ በሚል ህሳቤ ተነሳስቶ አባር የሚል አንደምታና ታሳቢን በህገመንግስቱ ውስጥ አንድም ቦታ የለም። ለአማሮቹ አርሶ አደሮች ቤንች ማጂ ከአካቢው ነዋሪዎች እኩል አገራቸው ስላልሆነ ደን ሲያቃጥሉ ሲያወድሙ እና ዛፍ ሲቆርጡ ስለተገኙ ወደመጡበት ይመለሱ የሚለው አስተሳሰብና ትንታኔ የሀገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ በሆነው ህገመንግስት አንድም ተደጋፊነት የለውም። አገራችን ደቡብ ኢትዮጵያም፣ ኦሮሚያም፣ ትግራይም፣ ሶማሊያ፣ ክልልም፣ አፋርም፣ ጋምቤላም ነው ብለው ለሚያምኑ ዜጎች ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች በሚል ዕሳቤ በሀይል ወደ ክልላቸው ማባረር ተገቢ ነው የሚል ዕሳቤን የቋጠረ ህገ-መንግስታዊ ስንኝ አንድም ቦታ የለም።

ደግሞሞ ይህ አይነት አስተሳሰብ በህገ-መንግስቱ ከተደነገጉ ህጎች በላይ ጎልቶ ከወጣ በበርካታ ኢትዮጵያውያን ላይ ምን አይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል የሚለውን ጣጣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በውል የሚረዳው ጉዳይ ሳይሆን አይቀርም። ብቸኛው የፓርላማ ተመራጭ የሆኑት ክቡር አቶ ግርማ ሰይፉ የሰዎቹን መባረር አስመልክተው ጥያቄ ሲጠይቁ የሚከተለውን ጥልቅና የተሰደረ ሀሳብን ለመላው ኢትዮጵያዊ ባለአዕምሮ ሁሉ አካፍለዋል’ እንደሚታወቀው ክልላቸው አዲስ አበባባ ይሆንም በርካታ ኢትዮጵያውያን በአዲስ አባባ እየኖሩና ኢንቨስት እያደረጉ ነው። ወደፊትም በርካቶች ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ። እና አዲስ አበባ የእኔ ነው የሚል ወገን ድንገት ብድግ ብሎ ወደ ክልላችሁ ወጡ ቢልስ?’ የእኝህን ሰው ጥያቄ በነፃ ልቦና ብሎም በአርቆ አስተዋይ ህሊናው የመረመረ ባለአዕምሮ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ደግሞ ጥያቄያቸውን ሰፋ አድርጎ በህሊናው ነገ የራሱን እጣ ፋንታ እያሰላሰለም ሆኑ ዛሬ በአማሮቹ ላይ የደረሰው ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ አማራ ክልል መባረርምን አይነት የትውልድ ትውፊታዊ እሴትን ያወርሰን ይሆን እያለ በሀሳብ ሳይናጥ አይቀርም። ማህበረሰብ የማይናጥና የማይናወጥ የህግ መሰረት ላይ ቆሞ እጣፋንታውን በግልፅ የህግ መርሆዎች መዳኘት እስካልቻ ለድረስ እውነትም በሃሳብ መናጡ መቆሚያ የሚኖረው ጉዳይ አይደለም። ሌላው ቀርቶ ዛሬ እጁ ላይ ጉልበትና ሀይል ተባብረው የገቡለት ወገን እንኳን በተሰደረ የህግ መሰረት ላይ ስለመቆሙ እርግጠኛ ካልሆነ በሰመመን መናጡና መናወጡ አይቀርም፡ ፡ የህግ ፈላስፋው ጆን ሎክ እንደሚለው ማህበረሰብ በህግ ማዕቀፍ ስነባህሪውና ድርጊቱ ካልተመራና ካልተገዛ የአራዊት ባህሪ ይኖረዋል።

ዜጎች በግዳጅ ከአገራችው ኢትዮጵያ ወደ ሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ክልላችሁ ካልሆነው ክልላችሁ ወደ ሆነው ተብለው ሲገፈተሩ የሚኖረውን ጫና፣ የስነልቦና ቀውስ፣ የንብረት ብክነት እና ተያያዥ ጉዳዮችን በንፁህ ልቦናው እያሰበ የሚደመም የአዳም ልጅ በህሊናው የሚርመሰመስበት መሰረታዊ ተጠይቅ የጆን ሎክ ህሳቤን እየፈተሸ በመቀመጫው ላይ ቁልቁል በሚያሰጥም ጥቁር ራዕይ ከመጻኢው ትውልዱ ጋር እያወጋ መባተት ብቻ ነው።

ዜጎች ቤንች ማጂ ዞን መኖሪያ ፍለጋ ያቀኑት ወይም በቤንች ማጂኖረው ሀብት ያፈሩት ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን ተመርኩዘው እንዲሁም መንግሰት የሚባለውን ተቁዋምታም ነው ነው። መንግሰት ደግሞ በህገመንግስቱ በአንቀፅ 89 እንደተገለፀው የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ እርምጃቸውን የመደገፍ ግዴታ አለበት፡-

- መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሀገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀዬስ ሀላፊነት አለበት (89/1)
- መንግስት መሬትን እና የተፈጥሮ ሀብትን በህዝብ ስም በይዞታው ስር በማድረግ ለህዝቡ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ ማድረግ አለበት(89/5)

የፌደራል መንግስት በግልፅ እንዳመነው በአካባቢው ሊኖር ለፈለገ ዜጋ ብቁ የሚሆን ባዶና ሰፊ ስፈራ በጉራፋርዳ ወረዳ አለ። ምናልባትም ዜጎች ህገመንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው ወደ አካባቢው መኖሪያ ፍለጋ የሚሄዱት በተናጠል፣ ለልማት በማይመችና ባልተደራጀ ሁኔታ እንኩዋን ቢሆን መንግሰት ማድረግ ያለበት ሁኔታዎችን ለዜጎች ማመቻቸትና ዜጎችም የሚሰጣቸውን መመሪያ ተከትለው በተሻለ ሁኔታ እንዲሰፍሩ አቅጣጫ ማሲያዝ እንጅ ህገመንግስታዊ መብታቸውን ጥሶ ወደ መጣቸውሁበት ጥፋልኝ ማለት ህገመንግስቱን መናድ ነው።

ህገመንግስቱ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል በሚገኝ ሀብት ለመበልጸግና ለመጠቀም ለዜጎች ሁሉ ፈቅዶ ሳለ የአንድ ክልል ሰዎች ወደ አንድ አካባቢ ሲሄዱ አንዴ ሀብታም ሆነው በአካባቢው ነዋሪ ላይ ተፅዕኖ አመጡ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ደንጨፈጨፉ ስለዚህም ወደ ሰሜን አማራ ይመለሱ ማለት አንድም ህገመንግስታዊ መሰረት የሌለው ውሳኔ ነው። ደግሞስ ክልሉ የዜጎችን ህገመንግስትዊ መብት ገፎ ሰዎቹ በአካባቢው እንዳይኖሩ የሚያባርራቸው በምንስልጣኑ ነው?

3. የንብረት መብት

ምደረ ክርስቲያን በመላው ኢትዮጵያ ፋሲካን በአል እያከበረ ባለበት ሌሊት፣ ቅዳሴና ዝማሬ ለአምላኩ ለክርስቶስ እያቀረበ ባለበት የትንሳኤ በአል፣ ፆሙን በደስታ እየፈሰከ ባለበት ሌሊት የሰባት ተፈናቃይ አርሶ አደሮች ቤት በእሳት ሲጋይ ማደሩን መኢአድ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫው ጠቅሶ ይህ ጉዳይም እንዲቆም አሳስቦአል። ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች በበዓለ ፋሲካ ከቤታቸው ተፈናቅለው ባሉበት ሁኔታ ቤታቸውና ንብረታቸው በእሳት ሲቃጠል ሌሎች ወገኖችም ወጥተው በመመልከታቸው ብቻ የእስር እንግልት እንደደረሰባቸውም በመግለጫው ላይ ተብራርቶ ተገልፆአል።

አዲስ አድማስ፣ ሪፖርተር፣ ፍትህና እና ሌሎች ሚዲያዎች ደግሞ በጥልቀት እንደ ዘገቡትና ሰፋሪዎችም እንደ ገለፁላቸው ‹‹ንብረታችሁን ያፈራችሁት እዚሁ ስለሆነ ንብረታችሁን ትታችሁ ውጡ ተብሎ ተነግሮን ባዶ እጃችንን እንድን ወጣ ተደርገናል። ሌሎቻችን ደግሞ በአጭር ጊዜ ውጡ ስንባል ንብረታችንን ቦታ ቦታ የምናሲዝበት ጊዜ ይሰጠን ብለን ስንጠይቅ ንብረታችሁን ከፈለጋችሁ ዋጡት ወይም አቃጥሉት የሚል መልስ ተሰጥቶን ከአካባቢው አንዲትም ንብረት ሳንይዝ እንድንወጣ ተደርጓል።›› ሲሉ ያብራራሉ።

ሆኖም ህገመንግስቱ የንብረትን ጥበቃ ጉዳይ በዝርዝር አስፍሮ ለዜጎችም ንብረት ከፍተኛ ጥበቃ ሊደረግለት እንደሚገባ በአንቀፅ 40 በስፋትያብራራል፡ -

- ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል (40/1)
- በጉልበት በካፒታል ወይም በፈጠራ ችሎታ የተገኘሀብት (40/2) ሁሉ ንብረት ሲሆን የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥና የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው (40/3)
- የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረነው (40/4)
- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ የመለወጥ የማውረስ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታለል (40/7)

እንዲያውም አንቀፅ 26/1 ይህን ጉዳይ ሲያብራራ ማንኛውም ሰው የግል ህይወቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖርያ ቤቱ ሰውነቱና ንብርቱን ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል ይላል፡ ፡

እንግዲህ በህገመንግስቱ መሰረት እነዚህ ዜጎች ግልፅ የሆነ የንብረት መብት አላቸው። ሆኖም ደቡብ ኢትዮጵያ ያፈራህውን ሀብት እዚችው ትተሃት ወደ አማራ ክልልህ ነቅለህ ጥፋልኝ የሚለው ህሳቢ ህገመንግስቱን መቃረን ወይም መናድ ነው። ደግሞም እንደማንኛዉም ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር እነዚህ ሰዎች በየትኛውም ክልል መሬት በነፃ የማግኘትና ሀብት የማፈራት መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን ህገመንግስቱ በግልፅ ደንግጎአል (40/4)። ከላይም እንደ ጠቀስነው በይትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ተዘዋውረውም መኖር ህገመንግስታዊ መብታቸው ነውና በየትኛውም ክልል መርጠው መኖር ይችላሉ። ምናልባትም አንድ ሰው ወንጀል ቢሰራ፣ ጥፋት ቢያጠፋ ፍርድ ማግኘት ያለበት በፍርድ ቤቶች ነው እንጅ ከሚኖርበት አካባቢ ወይም ሊኖርበት ከመረጠዉ አካባቢ ይባረር የሚል ህግ የለም፡ ፡ ህጉ አስፈላጊውን ቅጣት ሁሉ ጥፋቱን ባጠፋው ግለሰብ ላይ የሚወስደውም በፍርድ ቤቶች ሲሆን በፍትሐብሄሩም ሆነ በወንጀል ህጉ ውስጥ አንድ ዜጋ ጥፋት በማጥፋቱ ከአካባቢው ይባረር የሚል አንቀፅ የለም። ቢኖርም ቅሉ ህገ መንግስቱ የህጎች የበላይ ነውና ገዥ ሆኖ የሚወጣው ህገመንግስቱ ውስጥ ያለው ህሳቤ ይሆናል ማለት ነው።

4.የተፈናቃዮች የፍትህ ጥያቄ

በተለያዩ ሚዲያዎች የተለያዩ ተፈናቃይ አርሶ አደሮች የፍትህ ጥቂያቸውን በተለያዬ መልክ ሲያቀርቡ ተደምጠዋል። ሆኖም ሲጠቀለልና ሲጨመቅ፡- ‹‹እኛ ገበሬዎች ነን። ሰርተን እና አፈርገፍተን በሀገራችን በኢትዮጵያ መኖር ብቻ ነው የምንፈልገው። ጥቂያችንም የተነጠቅነው ህገመንግስታዊ መብታችን ይከበር፣ ሀብታችን ይመለስ፣ ወደ ነበርንበት ቦታችንም እንመለስ፣ ቦታውን መንግስት ለልማትም ከፈለገው ተመጣጣኝ ካሳ ይሰጠንና ሌላ ጋ ያስፍረን፣ እንዲሁም የተቃጠለው ቤታችን እና ንብረታችን ተገምቶና ተሰልቶ ካሳ ይሰጠን›› የሚል መልዕክት ያለው ሆኖ ይገኛል።

በህገመንግስቱ መነፅር ጉዳዩን ስንመረምረው ደግሞ የተፈናቃዮቹ ሰዎች የአማራ ብሄር ወይም የሌላ ብሄር መሆናቸው ትርጉም የለውም። ዋናው ነጥብና ጥያቄ ይህ አሁን በደቡብ ክልል የተወሰደው እርምጃ የዜጎችን በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የመኖር መብትን የሚነጥቅ ነውይ? ይህ አስተሳሰብ እንደ እሴት ሆኖ በማህበረሰባችን ውስጥ ከሰረፀ ዛሬ በእነዚህ ወገኖች የተጀመረ አካሄድ ወደ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤት ላለመንደርደሩ ማረጋገጫ አለ ወይ? ኢትዮጵያዊ በሁሉም ቦታ እንዳይኖር የመከልከል አካሄድ ህገመንግስቱን ከመጣሱም በላይ ለመጭው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ጥልቅነቀር ሳንፈ ጣሪ እሴት አይደለም ወይ? ለምሆኑስ የክልሉ መስተዳድር ዜጎችን ከክልሉ የማባረር ስልጣን አለው ወይ ? በዚህና መሰል ጉዳዮች የፍርድ ቤቶች ሽሽትና ዝምታን መምረጥስ አግባብ ነውይ? በኢትዮጵያ የህግ አስፈፃሚው፣ የህግ አውጭውና የህግ ተርጉዋሚው አካላት የስልጣን ክፍፍል፣ ሚዛን ጥበቃና የእርስ በእርስ ቁጥጥር በዚህና በመሰል ጉዳዮች ላይ በመንተራስ ሲመረመር ተጎትቶ የሚወጣው እውነት ምንድን ነው? የሚሉት ጥቄዎች በልዩ ልዩ የህግ፣ የስነልቦና፣ የሶሽዎሎጂ፣ የኢኮኖሚክስ፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የልማት ሳይንስ ወዘተ ምሁራን ትንታኔ እንዲቀርብባቸዉ ሀሳብ እያጫርኩ ፅሁፌን እዚህ ላይ እገታለሁ።

ኢትዮጵያን እግዚአብሄር ይባርክ !

# የፕ/ር ‹‹አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ››ን በጨረፍታ



በሙሉነህ አያሌው

muleayalew@yahoo.com

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ከዚህ ቀደም ከ13 በላይ የምርምር መጽሃፍትን አሳትመው ለንባብ ያበቁ ምሁር ናቸው:: በኢትዮጵያ ታሪክ ‹‹ምሁር›› ብለን ከምንጠራቸው የአገራችን ውድ ልጆች መካከል ብዙ መጽሐፍትን በማሳተም፣ ብዙ የምርምር ስራዎችን በማቅረብ፣ በተከታታይ በጋዜጦች ላይ በአምደኝነት ደረጃ በመሳተፍ እርሳቸውን የሚያክል ታላቅ ሰው አልገጠመኝም:: አሁን በዚህ ሳምንት ደግሞ ‹‹አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ›› በሚል ርዕስ ባለ 237 ገፅ መጽሐፍ ለንባብ አብቅተዋል:: መጽሐፉ በይዘቱም፣ በአይነቱም ከዚህ በፊት ለንባብ ካበቋቸው መጽሐፍቶች ለየት ያለ እና ለበለጠ ምርምርና ጥናት የሚጋብዙ ርዕሶችን በውስጡ አካቶ የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ ካርታዎችንም (ወደ 5 የሚጠጉ) በማስረጃነት ቀርበዋል::

በመፅሀፉ ውስጥ ከተካተቱት የተለያዩ ርዕሶች መካከል ለዛሬ ለጋዜጣው በሚመጥን መልኩ በተወሰኑት ርዕሶች ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ::

## የሶማሊያ ነገር

ፕ/ር መስፍን ሶማሊያን አስመልክተው በመጽሐፉ ውስጥ ሰፊ ትንታኔ አቅርበዋል:: በተለይ ሶማሊያ በእንግሊዝ እና ጣልያን ቅኝ ግዛት ከነበረችበት ጊዜ አንስቶ የተከፋፈሉት ግዛቶቿ ነፃ ወጥተው ውህደት እስከፈጠሩበት ያለውን ጊዜና ከዛም በኋላ በመካከላቸው ስለነበረው ፖለቲካዊ መስተጋብር፣ በጎረቤት አገራት ላይ የነበራቸውን የግዛት ይገባኛል ጥያቄን ጨምረው በስፋት አቅርበዋል::

ሶማልያ በዚያድ ባሬ ዘመን በኢትዮጵያ ላይ የወሰደችው እርምጃ እና በጊዜው ኃያላን የነበሩት አገራት (አሜሪካ እና ሩስያ) የነበራቸው ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ምን ያህል እንደነበረ በዝርዝር አሳይተዋል::

ሶማሊያ ከዚህ ጦርነት በኋላ የነበራት እብጠት ፈንድቶላታል ይላሉ ፕሮፌሰር:: ከዚህ በኋላም የቀድሞ የእንግሊዝ ሶማሊላንድ የቀድሞ ስሙን ይዞ እ.ኤ.አ. በ1991 ተገነጠለ፣ አንድ ሌላ ክፍል ደግሞ ፑንትላንድ የሚል ስም ይዞ እ.ኤ.አ. በ1998 ተገነጠለ፣ ከፊሉ የቀድሞ የኢጣልያ ሶማልያ በጣም በከፋና በሚያሳዝን ሁኔታ በጎሳ መሪዎች ተበታትኖ እስከአሁን አለ::

ሶማልያ እንዲህ የተከፋፈለች ብትሆንም ለወደፊቱም ቢሆን አካባቢውን ዳግም ሊያናጋ የሚችል እንደ ሕዝብና አገር የአንድነት መሰረት አላቸው:: የቋንቋ አንድነቱ፣ የሃይማኖት አንድነቱ እና የዜግነት አንድነቱ ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው:: የአሁኑ የሶማልያ መፈረካከስም ቢሆን ትኩረት ተሰጥቶት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አንፃር መታየት ይኖርበታል:: ሶማልያ ተፈረካክሳ ስትደክም በአንፃሩ ኢትዮጵያ አድጋና ተሻሽላ ዱሮ ከነበረችበት የላቀ ደረጃ ላይ ብትደርስ አንድ ነገር ነበር:: ግን ኢትዮጵያም ገና ባትፈረከስም ተከፋፍላለች፣ ተዳክማለች:: በመሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ እንደዚህ አድርገን ካየነው በሶማልያ መፈረካከስ ሳቢያ ለኢትዮጵያ አደጋን የሚጋብዙ በሮች እንደተከፈቱ እንረዳለን:: በንፅፅር እያንዳንዱ የሶማሌ ስብርባሪ ወደብ ያላቸው በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ይበልጣሉ:: ከዚህ በመለስም ሁሉም ከኦጋዴን ጋር ስለሚገናኙ በራሳቸው ፈቃድም ሆነ ለሌሎች ወኪል በመሆን የኢትዮጵያን ቁስል ለመጎርጎር ችሎታ አላቸው:: ኢትዮጵያ ወደደችም ጠላችም ከሁሉም ጋር በወዳጅነት መቆየቷ ይጠቅማታል::

ስለዚህ ይላሉ ፕሮፌሰር መስፍን ኢትዮጵያ በግድም ይሁን በውድ የውስጥም ሆነ የውጭ አመራር መለወጥ ግዴታዋ ይሆናል:: በውስጥ አመራር የኦጋዴን ክልል ፊቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ መልሶ የሚያረካው የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲኖረው ለማድረግ የፖለቲካው ስራ መጀመር አለበት::

## የአፍሪካ ቀንድ

በ21ኛው ክፍለ ዘመን አብዛኛው የአለማችን ክፍለ ዓለማት ከጦርነት ቀውስ ወጥተው ወደ ልማት ፊታቸው ባዞሩበት በአሁኑ ወቅት የአፍሪካ ቀንድ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ ግን ገና እንደ አዲስ እልም ያለ መከፋፈል እና ጦርነት ውስጥ በመዘፈቅ ላይ ይገኛል:: ይህንን አካባቢ በአሁኑ ወቅት እንደ አዲስ መረዳት እና ማወቅ ተገቢ ነው:: የፕ/ር መስፍን መጽሐፍም ከዚህ አንፃር ወሳኝ ነው ባይ ነኝ::

የአፍሪካ ቀንድ አገራት ተብለው ይጠራሉ በሚባሉት አገራት ዙሪያ እስከአሁን ድረስ የጋራ መግባቢያ ባይኖርም በመጽሐፉ ፕሮፌሰር የራሳቸውን ምልከታ አስቀምጠዋል:: በዚህም መሰረት የአፍሪካ ቀንድ የሚባሉት አገራትን በሁለት ክፍለን ልናየው እንችላለን:: በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ካሉት አገራት ሁሉ ጋር የጋራ የመሬት ድንበር ያላት አገር ኢትዮጵያ ነች:: ስለዚህ ኢትዮጵያ እንደ አፍሪካ ቀንድ እምብርት አድርገን ከወሰድን፤ ከኢትዮጵያ ጋር ድንበር ያላቸው አገሮች ሁሉ የአፍሪካ ቀንድ አገር አባላት ናቸው ማለት እንችላለን:: ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ የሶማሊያ አገሮች ከአፍሪካ ቀንድ ውጭ ከሌሎች አገሮች ጋር የመሬት ድንበር ስለሌላቸው በሙሉ ጉናቸው መስፈርቱን ሲያሟሉ፣ ኬንያ፣ ደቡብ ሱዳን እና ሰሜን ሱዳን ከአፍሪካ ቀንድ ካሉ አገሮች ውጭ የመሬት ድንበር ስለሚጋሩ የቀንዱ አባልነታቸው በግማሽ ይሆናል ማለት ነው::

የአፍሪካ ቀንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ከፋ መከፋፈል እና እርስ በርስ ጦርነት እያመራ ከመሆኑ አንፃር ወደፊት በአካባቢው ላይ ተስፋ እንዳንጥል ያደርገናል:: ለዚህም ማሳያ የሚሆነው አሁን በሶማልያ ያለው ትርምስ፣ በሱዳን ያለው የማይበርድ ጦርነት፣ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ መካከል ያለው ፍጥጫ ከብዙ በጥቂቱ መሆኑን በመፅሀፋቸው በስፋት አሳይተዋል::

የአፍሪካ ቀንድ አባል አገራት ባለፉት ሃያ አመታት ውስጥ ብቻ እንኳን ካየን ቁጥራቸው ከአምስት ወደ አስር ለማደግ ችሏል:: ይህ ክፍፍል በዚህ አያያዙ ወደፊትም የሚበርድ አይመስልም:: ለዚህ ቀውስ የተለያዩ ምክንያቶችን (ድንበር ዘለል ይሁን አገራዊ) ማቅረብ ቢቻልም በመሰረታዊ ደረጃ ሁለት ነገሮችን ማየት እንደምንችል ፕሮፌሰር መስፍን ይገልፃሉ:: የመጀመሪያው የጎሳ አስተሳሰብ የሙጢኝ ብለው አእምሮአቸውን ያፈኑና ወንበር ላይ የወጡ ሰዎች አሉ:: እነዚህ ግለሰቦች ስልጣኑን በጠባብ የጐሰኝነት አስተሳሰብ ያጠሩበት ምክንያት ዋናው የራሳቸውን የስልጣን ጥም ጠንካራ መሰረት የሚኖረው በራሳቸው ጎሳ ድጋፍ ብቻ ነው ብለው በማመናቸው ሲሆን ሌላኛው ምክንያታቸው አእምሮአቸውና ልባቸው በጎሳ ስሜት ስለታፈነ በራሳቸው በዜግነታቸው በሰውነታቸው ላይ መተማመን ያቅታቸዋል፣ ያለጎሳ ምርኩዝ መቆም አይችሉም:: በራሳቸው የችሎታ ማነስ ያጋጠማቸውን ነቀፌታ ሁሉ በጎሳ አባልነታቸው ያመካኙታል:: ጎሳቸውን መደበቂያ ዋሻ ያደርጉታል:: ስለዚህ ጉሳው ራሱን የቻለ ማህበረሰብ እንዲሆንለት ለመታገል ዓላማውን ያደርግና የበላይ የሚሆንበትን ስራ ያገኛል::

ሁለተኛው መሰረታዊ ምክንያት በአገሮቹ መካከል የሚፈጠረው ጠብ ነው:: የዚህ አይነት ግጭት ምክንያቱ የስልጣን ጥም ነው:: የየአገራቱ አገዛዞች በውስጥ የለመዱትን አፈና በውጭም ለማራመድ አገዛዞቹ ያላቸው የቆየና ብርቱ ልምድ ደጋግመው ወደ ግጭት እንዲገቡ ያስገድዳቸዋል:: አንዳንዴም ለጦርነት ይዳርጋቸዋል:: ጦርነቱ የአምባገነኖቹን ፍላጐት ከማሟላት ውጭ ምንም ፋይዳ የላቸውም:: ከዚህ በተጨማሪም ለእርስ በርስ ጦርነት የውጭ አገራት ጣልቃ ገብነት አስተዋፅኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም::

የፕ/ር መስፍን እይታ ከዚህ በፊት በተለምዶ ከምናየው ከባቢያዊ የፖለቲካ ቀውስ እይታ የተለየ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: አብዛኛው የግጭት ምክንያቶች ላይ ሳይሆን መፍትሄዎች ላይ የሚያዘነብለውን የፖለቲካ ትንተና በአንድ ደረጃ የቀየረ አካሄድ ይመስለኛል:: ችግሩንም እስከዛሬ መፍታት ያልተቻለው መሰረታዊው የግጭት ምክንያት ላይ ትኩረት ያለማግኘቱ ጉዳይ ነው:: አብዛኛው የመጽሐፉ ክፍል ከዚህ አንፃር መሰረታዊ ምክንያት (Root causes) የሚባሉት ላይ ያተኮረ በመሆኑ በአካባቢው ላይ ለሚደረጉ ሰላም የማስፈን ተልዕኮ አንድ ተጨማሪ ግብዓት ይመስለኛል:: በተለይ የቀጠናውን ዋነኛ መለያ ባህሪ ለማወቅ ለሚጥር ተመራማሪ መጽሐፉን እንደ መነሻ ለመውሰድ ከበቂ በላይ ነው::

በመፅሀፉ ውስጥ ለአገር ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባሉ የሚባሉትን ተለምዶአዊ ግብዓቶች የተለያዩ መረጃዎችን በማሳየት ወሳኝ እንዳልሆኑ ለማሳየት ተሞክሯል:: በተለምዶ በአገራት መካከል ላለው የኢኮኖሚ ልዩነት መሰረት ተደርገው በብዙ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ተንታኞች የሚቀርበው አገሪቷ ያላት የህዝብ ቁጥር እና የቆዳ ስፋት ናቸው:: ካላቸው ሰፊ የቆዳ ስፋት እና የህዝብ ቁጥር አንፃር በተደጋጋሚ ህንድ እና ቻይና የዚህ አይነት እድገት ተምሳሌት ተደርገው ይወሰዳሉ::

የፕሮፌሰር መስፍን መፅሐፍ ይህንን ትንተና ሁሌም ትክክል ሊሆን እንደማይችል አፍሪካ ቀንድን እንደ ማሳያ ተጠቅመው አሳይተዋል:: በአፍሪካ ቀንድ አባል አገሮች መሀከል በመሬት ስፋትና በሕዝብ ቁጥር ያለውን ያህል ልዩነት ባይሆንም መጠነኛ የጥራት ልዩነት አለ:: ኬንያ፣ኤርትራና ጂቡቲ በአንዳንድ ነገር የተሻሉ መሆናቸውን ማየት እንችላለን:: ለምሳሌ በእድሜ እርዝማኔ (Life expectancy)፣ በሕፃናት ሞት አነስተኛነትና በአጠቃላይ ሞት አነስተኛነት እነዚህ ሶስት አገሮች በቀጠናው ትልቅ የህዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት አላቸው ከሚባሉት ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ሶማልያ ጋር ሲነፃፀሩ የተሻሉ ሆነው እናገኛቸዋለን:: በተንቀሳቃሽ ስልክ አጠቃቀም ኢትዮጵያ ከጂቡቲም ከሶማልያም ታንሳለች:: ኬንያ ደግሞ ኢትዮጵያን አስር እጥፍ ትበልጣታለች:: የኬንያ የውጭ ንግድ ከኢትዮጵያ እጥፍ ይበልጣል::

በአጠቃላይ ፕሮፌሰር መስፍን የቀንዱ አካባቢ አገራትን የሚያምሱ መሰረታዊ የሚባሉ ምክንያቶችንም በዝርዝር አቅርበዋል:: የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በአካባቢው ባሉ አገራት ችግር ምክንያት ብቻ የሚታመስ አይደለም:: ከዚህ በተጨማሪም የአረቦችና የእስራኤል የማይሽር ጠብና ድብድብ ባህር ተሻግሮ በተለያየ መልኩ ወደ ቀንዱ አካባቢ ይመጣል:: በአክራሪ እስልምና ጋር የተዛመደውም የአካባቢው ውዝግብና ጠብ ወደ አፍሪካ ቀንድ ይደርሳል:: የአካባቢው ሀብታም አገሮች የተለያዩ ጫና በተለያየ መልኩ ቀዳዳዎችን እየፈለገ ይገባል:: ከዚህ በተጨማሪም የኃያላኑ የአሜሪካና የአውሮፓም ጫና ቀላል የሚባል እንዳልሆነ የተለያዩ መረጃዎችን ተጠቅመው መጽሐፉን አደርጅተውታል:: ፕሮፌሰር አሁን ያለውን ችግር የአካባቢው ቀውስ ከሌላ ኃይሎች ፍላጐት ጋር እንዴት ሊያያዙ እንደሚችልና መፍትሄውም አካባቢያዊ ብቻ ሳይሆን አለም አቀፋዊ ጥረት የሚሻ መሆኑን ነገሩን ውስብስብ አድርጐታል ይላሉ::

## ሽብርና ሽብርተኝነት

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት መጽሐፉ ከውጤት ይልቅ ምክንያት ላይ ማተኮሩ ለመፍትሄ መንገድ ጠቋሚ ያደርገዋል:: ከዚህ በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት አብዛኛው ትንታኔዎች ከዚህ በፊት አይተናቸው/ሰምተናቸው ከምናውቀው በተለየ መልኩ የራሳቸውን የፕሮፌሰሩ ወጥ ሃሳብ ብቻ ናቸው:: ለማጣቀሻነት እንኳን የሚጠቀሙት ከራሳቸው ተሞክሮ አልያም ከዚህ ቀደም ከፃፏቸው መፅሐፍቶቻቸው እና በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አገራት ባሉ ዩኒቨርስቲዎች እየተዘዋወሩ ካቀረቧቸው ጥናታዊ ፅሁፎች የተጨረፉ ናቸው:: ሽብር እና ሽብርተኝነት መጽሐፍ ውስጥ እንዴት እንደተነተነ እንመልከት::

በመሰረቱ በዘመናችን ሽብር የሚባለው ከጭቆና ተወልዶ በጭቆና ላይ የሚነሳ እምቢተኝነት የኃይል ተቃውሞ ነው ይላሉ ፕ/ር መስፍን:: በየዘመናቱ ለነፃነት፣ ለፍትሕ እና ለእኩልነት የተደረጉ ተጋድሎዎች ብዙውን ጊዜ በሌላኛው ወገን ‹‹ሽብር›› የሚል ስያሜ የተሰጣቸው መሆኑን የሚገልፁት ፕሮፌሰር ዛሬ በኢህአዴግ አመራሮች ላይ የተነሱትን አመፀኞች ሽብርተኞች ይሏቸዋል ይላሉ:: ሽብርተኞች የመንግስት ስልጣን ሲይዙ እነሱ በመጡበት መንገድና በተጠቀሙበት ዘዴ ሌሎች እንዳይጠቀሙ ነቅተው ይጠብቃሉ:: የ‹‹ሽብር›› ለየት ያለው ባህሪና (ለነፃነት በሚደረግ ትግል የሚተረጐም ሳይሆን) ከሌሎች ተጋድሎዎች ለየት የሚያደርገው ድንገተኛና ቁጥጥር የማይደረግበት መሆኑ ነው::

ሽብር ከጦርነት የተለየ ነው:: ጦርነት ግልፅ አላማ አለው:: ደንብና ስርዓትም አለው:: ሽብር ግልፅ አላማ ሳይኖረው ‹‹ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ›› በሚል የጭካኔ መመሪያ የሚፈፀም ነው:: ሽብር አመራርን የመለወጥ አላማ የለውም:: የቂም መወጫ ወይም በቀል ብቻ ይመስላል:: የሽብር ዓላማው ሕዝብን በማሸበርና በፍርሃትና በስጋት ኑሮ ውስጥ በመክተት ኑሮውን ማቃወስ ነው:: በዚህ ትንታኔ መሰረት የተደራጀ የፖለቲካ ፓርቲ መንግስትን ተክቶ ወደ ስልጣን መምጣት የሚፈልግ ማናቸውም የፖለቲካ ቡድን ለነፃነት፣ ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ እታገላለሁ የሚል ቡድን ስብስቡ በደምሳሳው ሽብርተኛ የሚል ማዕረግ ሊሰጠው እንደማይገባ የጠራ ትርጉም የያዘ ይመስለኛል:: በተለይ በአሁኑ ጊዜ ህገ-መንግስቱ ያጐናፀፈንን የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶች ሁሉ በአጠቃላይ ከሽብር ጋር እየተያያዘ ለተቸገርን ዜጐች፣ ትርጉሙ ግራ ለገባን እና ላጋባን ፀሐፊያን ጥርት ያለ መግባባት ላይ መድረስ እንችላለን የሚል እምነት አለኝ::

ፕ/ር መስፍን እንደተለመደው ሽብር ተግባሩን ብቻ ሳይሆን ምክንያቱንም ጭምር በሚገባ አሳይተዋል:: ስለዚህ ‹‹ሽብር›› እና ‹‹ሽብርተኛን›› ለማስወገድ አስቀድሞ ምንጩን ማድረቅ ያስፈልጋል::

የሽብር ዋነኛው መነሻ ጭቆና ነው:: አብዛኛውን ጊዜ በስልጣን ላይ ያሉት ወንበሩ እንዳይመቻቸው፤ የተጨቆኑትም ተስፋ ቢስ እንዳይሆኑ፣ የተስፋ ጭላንጭል ለማሳየት ይመስላል:: ከቂምና ከበቀል የተቀላቀለ በመሆኑ ሽብር ከአልሚነቱ አጥፊነቱ ያመዝናል:: ሽብር የሚያጠቃው በቀጥታ ሳይሆን ግፍ ፈፃሚን አልፎ ከግፍ ፈፃሚ አገር ጋር ንክኪ ያለውን ሁሉ ነው::

ከዚህ በተጨማሪም የሽብር ገፈት ቀማሽ የሚሆኑት አገራት ለአምባገነኖቹ የጭቆና መሳሪያ እና እርዳታ የሚለግሱ አገራትም ጭምር ናቸው::

## የአፍሪካ ቀንድ ግጭት ወይም ጦርነት

ፕ/ር መስፍን የግጭትን አይነቶች በሁለት ከፍለው ያሳዩናል:: አንደኛው ብዙውን ጊዜ የሚታየው በገዢዎች እና ተገዢዎች መካከል የሚነሳ ሲሆን ተገዢዎች በደልና ጥቃት እየከበዳቸው ሲሄዱ ተደራጅተውም ሆነ ሳይደራጁ በገዢዎች ላይ አምፀው የሚነሱበት ሲሆን አላማውም ገዢዎችን ለማውረድ ወይም የአገዛዛቸውን ዓይነት እንዲለውጡ ለማድረግ ሲሆን ሁለተኛው የግጭት አይነት ደግሞ በገዢዎች እና ተገዢዎች መካከል ሳይሆን ጎን ለጎን ባሉት የህዝብ ክፍሎች መሀከል የሚደረግ ነው:: መሰረቱ የጎሳ ልዩነት ወይም የሀይማኖት ልዩነት ይሆናል:: ሁለቱም አይነቶች በአንድ አገር ውስጥ ሲከሰቱ ለብዙ ዘመናት የሚቆይ ብጥብጥን ይፈጥራሉ:: ሱዳንና ሶማልያ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው::

በአገሮች መካከል የሚደረገው ግጭት ጦርነት ይባላል:: ጥፋቱም በአገር ውስጥ ከሚነሳው የግጭት ጥፋት የከፋ ነው:: በተለይ በአፍሪካ ቀንድ አገራት መካከል የሚነሱ ግጭቶች የውጭ እጅ ያለባቸው ናቸው:: የናይል ወንዝና ቀይ ባህር፣ የማዕድን ዘይት ማጓጓዣ መንገድ አቅርቦት፣ የአረብ አገሮች እና የእስራኤል ፍጥጫ እና የመሳሰሉት ምክንያቶች የአፍሪካ ቀንድን የግጭት አካባቢ አድርጎታል:: በዚህ መንገድ የሚነሱ ግጭቶች እና ጦርነቶች በየአገሩ ያለው ጭቆናና አበሳ ጋር ተዳምረው በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ዜጐች ከቀያቸው እና ከአገራቸው ለመፈናቀላቸው ምክንያት ይሆናሉ::

## ማጠቃለያ

ፕ/ር መስፍን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በተደጋጋሚ የሚከሰቱትን ግጭት፣ ጦርነት፣ ችጋርና በተመለከተ መንስዔያቸውን በጥልቀት ዳስሰዋል:: ችግሩ ከባቢያዊ ብቻም ሳይሆን የሌሎች አገራት እጅ እንዳለበት ከታሪክ በማስረጃነት ሁሉ እየጠቀሱ አቅርበዋል:: ከዚህ በተጨማሪም እንደ አንድ ምሁር ለችግሮቹ መውጫ መንገድም ጠቁመው አልፈዋል::

የአፍሪካ ቀንድ አገራት አዲስ የልማትና የእድገት አቅጣጫ ለመቀየስ ሁለት ነገሮችን ማሟላት ያስፈልጋቸዋል:: አንደኛው ሁሉም ከውስጥም ሆነ ከውጭ አመራራቸው በጉልበት ላይ መመካትን አስወግደው ህዝቦቻቸውን የስልጣን ባለቤት በማድረግ እርስ በርስ ምንም አይነት የጠላትነትና የጠብ ጫሪነት ዝንባሌ እንዳይኖራቸው ሙሉ በሙሉ የሚተማመኑበትን ዘዴ ሊቀይሱ ይገባል:: ሁለተኛ ጉልበትና ሀብት ላላቸው አገሮች በተለያዩ መንገዶች እየተገዙ ጉዳይ አስፈፃሚ መሆናቸውን ማቆም ያስፈልጋቸዋል::

በመፍትሄ የተቀመጡትን ዋና ዋና እሳቤዎች ዘርዝር አድርገው በራሳቸው አተያይ ፕሮፌሰር ያቀረቡ ሲሆን በተለይ እነዚህ ሁሉ ችግሮች መፍትሄ ሊያገኙ የሚችሉት የአካባቢው አገራት መሪዎች ትንሽ ማሰብና ቅን መንፈስ ከጨመሩበት አካባቢው አሁን ካለበት የግጭት፣ የውጊያና፣ የመጠላለፍ፣ የድህነትና የችጋር አዘቅት መውጣት ይችላል:: ይህንን ለማድረግ ከኢትዮጵያ የተሻለ አገር የለም:: ካልሆነ ግን ጦሱም በባሰ መልኩ ለኛ ነው የሚተርፈው::

በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት እያንዳንዱ ንዑስ-ርዕስ ለብቻቸው አንዳንድ መጽሐፍት ሊወጣቸው እንደሚችል አምናለሁ:: ይህንን መጽሐፍ በመነሻነት ተጠቅሞ ሌላ ሰፋ ያለ መጽሐፍ መስራትም ይቻላል:: የመጽሐፉ ሌላው ጠንካራ ጐኑ ሙሉ ለሙሉ የፕ/ር መስፍን እሳቤ ብቻ የተካተተበት በመሆኑ በሁሉም መልኩ አዳዲስ እና ወጥ የሆኑ መረጃዎችን ከነመፍትሄ ሀሳቦቻቸው ጭምር ይዟል::

መፅሐፉ ከዚህ በተጨማሪም በ1951 ዓ.ም. ለኦጋዴን በመንግስት ለጥናት ከተላከ ቡድን ጋር ለአንድ ወር ያህል ሄደው ከደረሱበት የጥናት ውጤት ለመንግስት ያቀረቡትን ሪፖርት እና በእንግሊዝኛ የዛሬ 41 አመት ግድም በጆርጅ ታውን ዩኒቨርስቲ የስትራቴጂና የዓለም-አቀፍ ግንኙነት ማዕከል በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገ ስብሰባ ላይ “Ethiopia and the Indian ocean”በሚል ርዕስ ያቀረቡትን ፅሁፍ በአባሪነት አያይዘው አቅርበዋል::መልካም ንባብ::

# ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

ታሪኩ መኮንን አምደማርያም
በኮከበ ዕፅባ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት
የፊዚክስ መምህር የነበረ

ከመምህራን የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በኩል በዜና የቀረበውን የተጋነነ መግለጫ ተከትሎ በተነሳው የመምህራን ተቃውሞ ምክንያት የስራ ስንብት ደብዳቤ (ወይም እርስዎ እንዳሉት ‹‹የማስወገድ እርምጃ››) ከደረሳቸው መምህራን አንዱ ነኝ። እርስዎ በተወካዮች ምክር ቤት የሰጡትን ማብራሪያ ማለትም የተጨመረ ደመወዝ እንደሌለና የእርከን ማስተካከያው ሲሰላ ሊኖር የሚችለውን አምስትም፣ ሃያም፣ ስልሳም፣ ሰባም ብር ለውጥ እንደጭማሪ በማየት ከፍተኛ ገቢ መምህሩ እንደሚያገኝ ያስመሰለውንና ከሸቀጦች ዋጋ መጨመርና ለቤት ኪራይ ባልተጠበቀ ሁኔታ መናር መንስኤ የሆነውን ዘገባ ፣በማህበረሰቡ ላይ ያሳደረውን የተሳሳተ ግንዛቤ ከታች ያሉት የትምህርት አስተዳደር አካላት አስቀድመው በማስተካከል ቢያቀርቡት ኖሮ አንድ ሳምንት አይደለም አንድም የትምህርት ክፍለ ጊዜ ባልባከነ ነበር። ችግሩ እንደተከሰተ በመገናኛ ብዙሃን ለምን ወዲያው ማብራሪያና መግለጫ እንዳልተሰጠበትም ግራ የሚያጋባ ቸልተኝነት ነው። መንግስት ራሱ ብጥብጡን የሚፈልገው እስኪመስል ድረስ ምንም የሚዲያ ሽፋን ሲሰጠውም አልታየም።

እኔ እስከማውቀው ድረስ የመምህራን ጥያቄ አጭርና ግልፅ፣ የሚመለከታቸው አካላትን አነስተኛ ማስተባበያና ማረጋጊያ ምላሽ የሚሻ የነበረ እንጂ እርስዎ እንደገለፁት የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብን የማሸበርና የማተራመስ እቅድ ካላቸው ሃይሎች የተወጠነ ሴራ ውስጥ ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ያመጡት እንዳልሆነ እኔ አንዱ ማረጋገጫ መሆን እችላለሁ።አጭሩና ግልፁ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ የነበረኝ አለመሆኑ ነው።ከማስተማር ብቃትና ክህሎት ጋር እንደማይያያዝም በተደረገው ከስራ ማስወገድ ርምጃ ሰለባ የሆንኩት ራሴው ህያው ማረጋገጫ መሆን እችላለሁ።ይህን ያልኩበት ምክንያት በማስተማር ብቃትም ሆነ በማስተምረው ትምህርት አይነት ክህሎት አንድም ቀን ጉድለት ኖሮብኝ እንደማያውቅ ማህደሬ የሚመሰክር በመሆኑ ነው።ይልቁንም ትምህርት በተቀላጠፈና ጥራት ባለው መልኩ የሚሰጥበትን መንገድ በማመቻቸት ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ እክሎችን ለማስወገድ ወይም ለመቅረፍ ከተቀጠርኩበት የማስተማር ስራ ውጪ ሌሎች ያካበትኳቸውን ተጨማሪ እውቀቶች ያለምንም ክፍያ ላስተማረኝ ህዝብና ሃገር፣ የዕረፍት ጊዜዬን ጭምር በመሰዋት ያገለገልሁና እያገለገልሁ የነበረ መሆኑን አሁንም ማህደሬና የስራ ባልደረቦቼ ይመሰክራሉ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እስከ ማክሰኞ 9/08/2004 ዓ.ም የተወካዮች ምክር ቤት ማብራሪያዎ ድረስ በየጊዜው እርስዎ ሃገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚያቀርቧቸውን ሪፖርቶች፣ክርክሮችና ማብራሪያዎች በአብዛኛው እከታተል ነበር።በሚያቀርቧቸው አንዳንድ መሰረታዊ የሆኑ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ምላሾች ላይ በሚሰጡዋቸው ምላሾች ከነባራዊ ሁኔታ የሚሸሹ ንግግሮችን፣ጥርጣሬን እንጂ ተጨባጭ መረጃ ላይ ያልተመረኮዙ ችኩል ውሳኔዎችን፣ወይም ስህተትን አምኖ ህዝብን ይቅርታ የሚያስጠይቁ ውሳኔዎች ችላ የማለት ሁኔታን አስተውያለሁ።ይሁንና ይህ ሁኔታ ሊያጋጥም እንደሚችልና ደሃ ሃገርን ማስተዳደር ትንሽ ሊከብድ እንደሚችል እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊስተካከሉ እንደሚችሉ ተስፋ ነበረኝ።በየጊዜው በወንጀለኝነት ተጠርጥረው ስለሚታሰሩ ግለሰቦች ወይም በአሸባሪነት ተጠርጥረው በፍትህ ሂደት ውስጥ ስለሚገኙ ግለሰቦች እርስዎ የሚሰጧቸውን ማብራሪያዎች ስሰማ ምናልባት እኔ የፖለቲካው ጨዋታ ያልገባኝ በመሆኑ ወይም የማላውቃቸውና ልረዳቸው የማልችላቸው የሃገር ደህንነት የመረጃ ስርዓቶች ይኖራሉ ብዬ በማሰቤ ሊሆን ይችላል፣ ከመንግስት ቁጥጥር አቅም በላይ ያልሆኑና መሳሪያ ያልታጠቁ የማህበረሰቡ አካላትን መንግስት እንዲሁ ያለምንም ወንጀል እየመረጠ የሚያስርበት ለየት ያለ ምክንያት የለውም እያልኩ እከራከር ነበር።ግለሰቦችን ለስቃይና ለእንግልት መዳረጉስ ለመንግስት ምን ይጠቅማል ነው የምለው። ምክንያቱም መንግስት እንደ አባት ነው።ልጆቹን ከአደጋ የሚጠብቅ እንጂ አደጋ ውስጥ የሚከት ተንኮል ያስባል የሚል እምነት አልነበረኝም።አሁንም ቢሆን መንግስት እንደዚህ መሆን አለበት የሚል እምነት ነው ያለኝ።መንግስት ብሎም የሃገር መሪ ሆደ-ሰፊ፣መካሪና አቅጣጫ ጠቋሚ እንዲሁም ህዝብ በማንኛውም ወቅት ሊደርስበት የሚችለውን የፖለቲካ፣የኢኮኖሚ፣የጤና ፣የማህበራዊና የስነ-ልቦና ደህንነት አደጋ የሚከላከልና የሚታደግ “አባት” መሆን አለበት ነው እምነቴ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የዚህች ሀገር የመጀመሪያው ተጠሪ እርስዎ እንደሆኑ ነው የማውቀው።ህዝቦች በየደረጃው በሚገኙ ባለስልጣናት በመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት ቢበደሉ፣ፍትህ ቢያጡና ቢንገላቱ የመጨረሻው አማራጫቸው የእርስዎ ቢሮ ማንኳኳት እንደሚሆን ነው የማምነው።እርስዎ ሌሎች ተራ ባለስልጣናትም ሆነ ተቋማት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በስህተት ለወሰኑት ውሳኔ በአደባባይ ድጋፍዎን ሲሰጡ ስሰማና በምስኪኑ መምህር ላይ ሲፈርዱ ስመለከት ግን እውነቴን ነው የምልዎት ወደ ፍትህ አካላት ለመሄድና የደረሰብኝን በደል አቤት ለማለት ያለኝ ተስፋ ሁሉ መነመነ።እንዴት እርስዎ እንደ አንድ መንግስት ተጠሪነትዎ የአንድ ወገን ውሳኔን ብቻ አድምጠውና ደግፌው በተወካዮች ምክር ቤት ለህዝብ በሚያቀርቡት ምላሽ ላይ ምንም አቅም የሌላቸውን፣ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን ከሌሎች የስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ያነሱና ባልተጠና አስተዳደራዊ እርምጃ ከስራቸው የተሰናበቱ፣መጠጊያና መሸሸጊያ የሌላቸውን መምህራንን ሞራል የሚነካና የሚወነጅል አድሎአዊ ምላሽ ለመስጠት እንዳነሳሳዎ አልገባኝም።ሲሆን ሲሆን እነዚህን ‹‹ያለወንጀላችን ነው የተባረርነውና ፍትህ ተጓድሏል›› በማለት በየአስተዳደርና የፍትህን አካላት ደጅ የሚጠኑ መምህራንን በማድመጥ፣ወንጀል ሰርተዋል ተብለው ተጠርጥረው ከሆነ የሚጣራበት ሁኔታ እንዲመቻች የማድረግና የማረጋጋት ተግባራትን ነው በእርስዎ ደረጃ የምጠብቀው።

የእርስዎ ምላሽ ከፍተኛ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል ዘንግተውት ነው? ኢትዮጵያ እንጂ ሌላ የምንኖርበት ሀገር እኮ የለንም! ሶስት አራት የሚሆኑ፣ ተቀጥረው፣ ሙያቸውን ሽጠው የለት ጉርሳቸውን የሚያገኙ ዜጎችን እንዲህ ባለ የማይገባቸውን ስም በመለጠፍ ከማህበረሰቡ እንዲነጠሉ ማድረግና በንግግርዎ ‘አፈር ድሜ ማስጋጥ’ስ ከእርስዎ ከአንድ ሃገር መሪ የሚጠበቅ ነው? እሺ የኛ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ይቅር፣ሌላ የግል መስሪያ ቤት ተቀጥረን እንዳንሰራ የእርስዎ የፓርላማው ውንጀላ ውርጅብኝ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያመጣ ሳይገነዘቡት ቀርተው ነው? ለዚህች ሀገር ዜጋ የሚያስቡት እንዲህ ባለ ሁኔታ ነው? ምን አደረግንዎ? መሳሪያ አላነሳን? ህገመንግስታዊ መብቶቻችንን በመጠቀም ቅሬታዎቻችንን በማሰማታችን ተገቢ ምላሽ ተነፈግን እንጂ።ወንጀል እንኳ ብንፈፅም በህግ የተቀመጠውን የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ ሂደት ተከትሎ መሆን አለበት እንጂ በማናለብኝነት አንድ ቀን እንኳ ስራ ገምግሞ በማያውቅ የበላይ አካል በቀጥታ የስንብት ደብዳቤ መድረስ ነበረበት?ወይስ እንዲህ አይነቶቹ ውሳኔዎች ከእርስዎ በቀጥታ የሚወርዱ ናቸው? የሚያደርጉት አይመስለኝም! ምክንያቱም እንዲህ ያለ ከተራ ግለሰቦች ጋር ግብ ግብ መፍጠር የርስዎን ስልጣን ይመጥናል ብዬ ስለማላስብ ነው። ለአንዳንድ የበታች ባለስልጣናት አቤቱታችንን ስናቀርብ፣ታዘን ነው።ካቅማችን በላይ ነው። የሚሉ መልሶች ያበዛሉና ነው ይህን ጥያቄ እንዳነሳ ያደረገኝ። እኛ መምህራን መብቶቻችንን የመጠየቅና ህገ መንግስቱንም ሆነ የሃገሪቱን ህጎች የማክበርም ሆነ የማስከበር ሃላፊነታችንን ካልተወጣን ሌሎች እኛ የምናስተምራቸው ዜጎች በምን አይነት ሁኔታ ሊያከብሩና ሊያስከብሩ ይችላሉ ብለው ነው የሚጠብቁት? ህገ መንግስቱ የማን ነው? ወዴትስ ሃገር ሄደን ያለስጋት በነፃነት እንኑር?

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አሁን አሁን ይብዛም ይነስ ለእርስዎም ሆነ ለመንግስትዎ የነበሩኝ ጥቂት በጎ አመለካከቶች በየጊዜው በማያቸው አሉታዊ እርምጃዎች ምክንያት ጭራሹኑ እየጠፉ ይመስለኛል።እኔ ብቻም እንዳይመስልዎ እንዲህ የሚሰማኝ።አያሌ ያገራችን ዜጎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመረራቸውና መቋቋም እየተሳናቸው ነው።ይህንን ስል ያለምክንያት አይደለም።በየጊዜው ከማያቸው የከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት መሳሪያ ባልታጠቀ ህዝብ ላይ ከሚሰሩት ሴራዎችና ጭፍን ውሳኔዎች ተነስቼ ነው።በዕውነት ነው የምልዎት

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# በቴዲ አፍሮ ‹‹ጥቁር ሰው›› የታለፈው የጥቁሩ ሰው የትንሳኤ በዓል

ዳንኤል ተፈራ

መቼም ሀገራችን በየሁለት ወሩ ታሪክ የሚወራባትና ትናንት ያሳለፍናቸው ነገሮች በጥቂት ሳምንታት ውስጥ እንደ ጥላ ‹‹ሽው!›› ብለው የሚያልፉባት ታሪካዊ ሀገር ሆናለች፡፡ እንደዘበት የምናውቃቸው፣ የምንዳስሳቸው፣ የምንጨብጣቸው ጉዳዮቻችን ሁሉ እንቆቅልሽ እየሆኑ የሚነግዱባት፤ ህዝቦቿ እና ኑሮ ያልተግባቡባት፤ የመንግስታት አድገናል ልፈፋና የድህነት ቀንሷል የቁጥር ጨዋታ ጠረጴዛ ላይ ዳቦ ሆኖ የማይታይባት፤ መጭው ጊዜ ምን ይሆን? የሚል አስጨናቂ ጥያቄ ሰንጉ የሚይዝባት ሀገር ሆናለች፡፡

ተስፋና ተስፋ ማጣት ድብብቆሽ የሚጫወቱባት፣ ኑሮን ‹‹ጨበጥኩህ›› ሲሉት እያፈተለከ የሚያስቸግርባት፤ እንጀት የሚያላውስ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ በርካቶች የከተሙባት፤ በአንፃሩ ደግሞ የሆሊውድ አክተሮችን የመሰለ ኑሮ የሚገፉ ጥቂት ቱጃሮች የሚንፈላሰሱባት ናት፡፡ እስቲ አዲስ አበባን እንዲሁ እዩዋት፡፡ በውስጧ የታመቀው ቁዘማ በቀላሉ የሚገለጥላችሁ አይደለም፡፡ ህይወት ተረት ተረት እንደሆነ የሚገባችሁ ጥቂት ቆይቶ ነው፡፡ ሀይማኖተኛ ከሆናችሁ ደግሞ የገበያውን መጦዝ አይታችሁ ይሄ ሁሉ ህዝብ እህል ቀምሶ ማደሩ አስደምሟችሁ የአምላክን ጥበብ መልሳችሁ ታደንቁ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያችን እንደዚህ ሚስጥር የሆነች ሀገር ናት፡፡

ኢትዮጵያዊነት ራሱ ሚስጥር ነው፡፡ የኢትዮጵያዊነት የቁጣ መንፈስ መቼ እንደሚነሳ መተንበይ አይቻልም፡፡ ጥልቀት ያለው ዝምውታም እንዲሁ ለመተንተን የሚቸግር ነው፡፡ እስቲ የኑሮ ክብደቱን የተሸከምንበት ጫንቃ ደንዳናነቱ ራሱ አያስደንቅም? ያስደንቃል እንጂ! የኢትዮጵያውያን የዘወትር ምግብ የሆነው ጤፍ ከአንድ ሺ ብር ድንገት ተወንጭፎ አንድ ሺ ስምንት መቶ ሲገባ ምን አልን? በገና እና ሁዳዴ መግቢያ በስምንት መቶ ይሸመት የነበረ ጠቦት ሁለት ሺ ሲገባ ምን ተናገርን? ከምግብነትም በላይ ወይዛዝርቶች ራሳቸው ላይ ተቀብተው ቀዝቀዝ ይሉበት የነበረው ቅቤ እንደዘበት ዋጋው እየተቆለለ ሲሄድ ምን ተነፈስን?… ይሄን ስሜት ነው መተንበይ የማይቻለው የኢትዮጵያዊነት ሚስጥር የምላችሁ፡፡

የዘንድሮው የትንሳኤ በዓልም ያው የተለመደውን የዋጋ ንረት መርዶ ይዞ ነበር ከተፍ ያለው፡፡ ዞርዞር ብዬ ባየኋቸው አካባቢዎች የሸማቹን ኩርፊያ አስተውያለሁ፡፡ በእርግጥ የገንዘብ ሚንስትሩ አቶ ሶፍያን አህመድም ይሄን አልደበቁም፡፡ ህዝቡ መኖር አቅቶታል፣ በትክክል አብልተን ማሳደርና ማስተዳደር አልቻልንም አላሉም እንጅ መንግስት በከተሞች አካባቢ ያለውን የዋጋ ንረት መቆጣጠር እንዳልቻለና ለትራንስፎርሜሽናቸው ፈተና እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ግን የድህነቱ መቀነስ እና የህዝቡ በዋጋ ንረቱ የተነሳ መኖር አለመቻል የሚታረቅ አስተሳሰብ አይመስልም፡፡ በባለሞያዎች እንደሚባለው ከሆነ የኢኮኖሚ እድገት ካለ ምርታማነት አለ ማለት ነው፡፡ ምርታማነት ካለ ደግሞ በአንፃራዊነት የተስተካከለ የሸቀጥ ዋጋ ይኖራል ማለት ነው፡፡ በእኛዋ እማማ ኢትዮጵያ ግን ያለው እንደዚያ አይደለም፡፡ እድገትና ምርታማነት እንዳለ የሚነገረን በቴሌቪዥን ነው፡፡ ማንም ደፍሮ ዳቦ የት እንዳለ የሚጠቁመን የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ህዝቡ ውስጥ የምናየውን ሀቅ ስንፅፍ እንደሚሮርተኛ የሚቆጥሩንና የሚያስፈራሩን ካድሬዎች እንኳን ‹‹ዳቦ የት አለ?›› ለሚለው የህዝብ ጥያቄ መልስ የላቸውም፡፡ ለዚህም ነው ቶሎ ብለው ወደ ዛቻ የሚሄዱት፡፡

ባለፈው እሁድ የተከበረው የትንሳኤ በዓል ያሳየን በርካታ ጉዳዮችን ነው፡፡ በእኛ ትንሽ እድሜ እንኳን ያለፈውን ደግ ዘመን በትዝታ እንድንቃኝ ሲጋብዘን፤ ዛሬ ላይ በሬ የመኪና ዋጋ እንደነበር በምናውቀው ሲጠራ በመደመም ፈገግ ያሰኛል፡፡ እንዲህ በየሁለት ወሩ ዋጋ እየተቆለለ የሚቀጥል ከሆነ መጪውን ጊዜ ማሰብ ይሰቀጥጣል፡፡

አንዱን በግ ሻጭ ጠጋ ብላችሁ መለስተኛ ጠቦት አገላብጣችሁ ‹‹ስንት ነው?›› ስትሉት ‹‹ሃያ አምስት!›› ይላችኋል፡፡ ሁለት ሺ አምስት መቶ ማለቱ ነው፡፡ መቼስ በደጉ ዘመን ክትፎ በስሙኒ በላን ለሚሉ አባቶቻችን መጥፎ ትዝታ ውስጥ የሚጥል ነው፡፡ አንዳንድ ደግ አዛውንቶች ሃያ አምስት ብር መስሏቸው አጉል ደስታ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ የዘንድሮ ትንሳኤያችን እንደዚህ ነበር፡፡ በቅርብ አመታት ውስጥ ያየናቸውና የበዓሉን መቃረብ የሚያበስሩ ትዕይንቶች አልነበሩም፡፡ ዶሮ ዘቅዝቀው ወደ ቤታቸው የሚሄዱ እናቶች አላየንም፡፡ የበግ ቀንድ ይዞ ወደ ቤቱ የሚገሰግስ አባወራም አይታይም ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ለመንግስት ቆም ብሎ ማሰቢያው ጊዜ አሁን ነው፡፡ ቁልቁል የሚንደረደረው የዋጋ ንረት ላይ ታኮ ማስቀመጥ አለበት፡፡ ህዝቡ ምን እንደሚል ጆሮ ሰጥቶ ቢያዳምጥ ለሁላችንም ይጠቅማል፡፡

‹‹ሳይደግስ አይጣላም›› እንደሚባለው እቤቱ ባሰረው የበግ ድምጽ በዓሉን ያከብር ለነበረው ኢትዮጵያዊ እንደ መጽናኛ ቴዲ አፍሮ ከተፍ ብሎለታል፡፡ ‹‹በቴዲ አፍሮ ‹‹ጥቁር ሰው›› አልበም ትንሳኤን ለመሸወድ እድል አግኝተናል›› ያሉኝ ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ በትንሳኤው ዋዜማ የወጣውን አልበም በዶሮ ፋንታ አንጠልጥለው ሲሄዱ የታዩ በርካታ ሰዎችም ነበሩ፡፡

ሚሊኒየሙን ተከትሎ ሰተት ብሎ የገባው የኑሮ ውድነት አሁን አሁን ዜጎችን በመኖርና ባለመኖር መካከል የሚከት የእለት ተዕለት ግብግብ ሆኗል፡፡ እዚህ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ግን ለብራችን የመግዛት አቅም ማነስ በርካታ ምክንያቶች ተቀምጠው ነበር፡፡ ከገዢው ፓርቲ ሰዎች እንደሰማነው ‹‹የዋጋ ግሽበቱ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተፈጠረ እና፤ ከውጭ የገባ ነው…›› የሚል መከራከሪያ ነበር፡፡ በመቀጠል ደግሞ ‹‹ስግብግብ ነጋዴዎች ናቸው፡፡›› የሚል በማስከተል ኪራይ ሰብሳቢዎችን ለማስቆምም ተብሎ የዋጋ ተመን ወጣ፡፡ የዋጋ ተመኑም ለሙስና ክፍት ሆኖ ለተሰራው ‹‹ሲስተም›› (Corrupted system) እድል የሚፈጥር ነበርና በወጣበት ፍጥነት ተመልሶ ገባ፡፡

እንደማስታውሰው አቶ መለስ የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ በሶስተኝነት ያስቀመጡት ገበያውን ለውጭ ሀገር ሰዎች ክፍት ማድረግ የሚል ነበር፡፡ ያልተሞከረውም ይሄው ነው፡፡ የቻይና ወይም የህንድ በግ ነጋዴ ማምጣት፤ የቻይናዊ የሽቀጣ ሸቀጥ ሱቅ መክፈት… የመሳሰሉት፡፡ ምንም ይሁን ምን ከሚያሰቀቀውና እስከፊ እየሆነ ከመጣው የኑሮ ውድነት ህዝቡን መገላገል የመንግስት ግዴታ ነው፡፡ የተስተካከለ ስርዓት መገንባት ወይም ስልጣን መልቀቅም ሌላው መፍትሔ ይመስለኛል፡፡

ወደ ዋናው የዕለቱ ርዕሴ ስመለስም በቴዲ አፍሮ ሙዚቃ የተከበረውን የትንሳኤ በዓል እናገኘዋለን፡፡ ከሁለት ሳምንት በፊት ስለቴዲ አፍሮ ጥቂት ነገር ፅፌ ነበር፡፡ ወደኋላ ተመልሼ የታሰረበትን ወቅት በማስታወስ የቀድሞው ቴዲ አለ ወይስ ሌላ ቴዲ ነው የምናገኘው የሚል አብይ ጥያቄ አንስቼ ነበር፡፡ በየቤቱ የፋሲካ በግ ሆኖ የዋለው አርቲስት በጃ ያስተሰርያል የ40 ዓመቱን የኢትዮጵያ ፖለቲካ በ7 ደቂቃ እንደነገረን ሁሉ፤ አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ እንዳልመጣ በቁጭት እንዳስታወሰን ሁሉ አሁንስ ምን ይለን ይሆን? ወደ ግለ-ሳንሱር ይወርድ ይሆን? የቀድሞውን ቴዲ እናጣው ይሆን? የሚለው ስጋት ታክሎበት የፋሲካው በግና ዶሮ መርሻ ቴዎድሮስ ካሳሁን ሆነ፡፡ ይሄ የእኔ አስተያየት አይደለም፡፡ ስለፋሲካው በዓል ያነጋገርኳቸው አንዳንድ ሰዎች የገለፁልኝ ነው፡፡

እናም ከፋሲካው በግ ምን አገኘን? በቃ ቁስላችንን ነካካው፡፡ እንደገና ሌላ ቁጭት ጫረብን፡፡ የአንዷን ዘፈኑን ግጥም መዝገቤ በማሳየት ፅሁፌን አሳርጋለሁ፡፡ ‹‹ስለፍቅር›› የምትለውን፡፡ የትንሳኤ በዓል እንድንጋፈጠው ግድ ያለንን እንቆቅልሽና የኑሮ ውድነት ቴዲም እንደኛው ጠየቀ እንጅ መልስ አልሰጠም፡፡

‹‹ስለፍቅር ሲባል ስለፀብ ካወራን
ተሳስተናል
አንድ ላይ ብንሆንም ተለያይተናል፡፡››

ብሎ የሚጀምረው ቴዲ አፍሮ በውብ ዜማ አጅቦ ማጣታችን እውነት እንደሆነና ብዙ ችግር እንዳየን፣ እንዲሁም የመጣንበት የችጋር መንገድ እንደሚያሳዝን ይገልፅልናል፡፡ አዎ ቴዲ እውነት ነው ያሳዝናል፡፡ ዛሬም በሀገራችን ያለው ጥያቄ በልቶ የማደርና ጠግቦ የማደር ነው፡፡ ደግሞ ከቀን ወደ ቀን እየቀነሰ ይሄዳል ብሎ በፋሲካ በግ ፋንታ በየቤቱ የገባው ቴዲ አፍሮም ጉዳዩ እንቆቅልሽ የሆነበት ይመስላል፡፡ እናም ስንኙን በጥያቄ ይደመድመዋል፡፡

‹‹… እግር ይዞ እንዴት አይሄድም
ሰው ወደፊት አይራመድም
አፈር ይዞ ውስጡ አረንጓዴ
ለምን ይሆን የራበው ሆዴ?››

እናመሰግናለን ቴዲ፡፡ የበርካቶችን ጥያቄ ጉልበት ባለው ዜማ አቀረበልን፡፡ የእኛም ጥያቄ ይሄው ይመስለኛል፡፡ መቼስ ኢትዮጵያችን በተፈጥሮ ሀብቷ የምትታማ አይደለችም፡፡ እግር ይዘን መሄድ ያልቻልነው፤ አረንጓዴ ሀገር ይዘን የሚርበን፤ በግ ሞልቶ ተርፎን አልቀመስ ያለን፤ ገበያችን እንደ ገበቴ ውሃ የሚዋልለው መልካም አስተዳደር ስለሌለን ነው፡፡ ከላይ ቴዲ እንዳለው አንድ ላይ ብንሆንም ስለተለያየን ነው፤ ስግብግብነት ኢትዮጵያዊ የሆነውን ይሉኝተኝነት አሸቀንጥሮ ስለጣለው ነው፤ ሙስናና ብልሹ አሰራር ሞልቶ ስለፈሰሰ ነው፤ በተጨማሪም ገዢው ፓርቲ ብቻውን ሮጦ ብቻውን ለማሸነፍ ባለው አጉል ህመም ነው፡፡

እና ቴዲ አፍሮ ያነሳው ‹‹…ለምን ይሆን የራበው ሆዴ?›› የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያለበት አገር አስተዳድራለሁ የሚለው አካል ነው፡፡ አርቲስቱ ግን በቀጣዩ ስንኙም ግሩም ምክር አንስቷል፡፡ ብራና ዘርግተው የቀድሞውን የኢትዮጵያ ስልጣኔ እንዲመለከቱ የሚማፀን ነው፡፡ የጥበባችንን መሰረት ወደኋላ ተመልሰን ካላገኘን፣ ወደፊት መሄድ አንችልም አይነት ነው፡፡ ያው እንደምናውቀው እኛ ሀገር ሁሉ ነገር የሚጀመረው በማፍረስ ነው፡፡ ፕ/ር መስፍን እንዳሉት ሁሉም እንደ እንስሳ የሚጀምሩት ከዜሮ ነው፡፡ ፕ/ር መስፍን ይሄን እንደ እንስሳ ከዜሮ መጀመር ሲያፍታቱት ለምሳሌ ድመት ይላሉ፡፡ ከሁለት ሺ ዓመት በፊት የነበረ ድመትና ዛሬ ያለ ድመት አንድ ነው፡፡ ሰው ግን በአንዱ ስራ ላይ አንዱ እየጨመረና እያሻሻለው መሄድ አለበት ይላሉ፡፡ ቴዲ አፍሮም ወደ ኋላ ሂዱና ብራና ግለጡ፣ ያኛውን ልምድ እዩ ይላል፡፡

የዋጋ ንረቱ ጣራ ባደረሰው የትንሳኤ በግና ዶሮ ፋንታ በየቤታችን የገባው ቴዲ አፍሮ በርካታ ጠንካራ መልእክቶችን ያስተላለፈ ይመስለኛል፡፡ አድናቂዎቹን በደረሰበት እስር ምክንያት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሀቆችን ከማንሳት ይቆጠብ ይሆን? ከሚለው ስጋታቸው ያላቀቃቸው ይመስለኛል፡፡ በእርግጥም በአንድ ነጠላ ዜማው ‹‹አንገት ከሚሰበር፤ ባይበላስ ቢቀር›› ብሎን ነበር፡፡ ስብዕና ለድርድር የሚቀርብ አይደለም፡፡ ሰው ራሱን ካጣ ምን ይቀረዋል?

‹‹ሰው ለመውደድ ካልኩኝ ደከመኝ
ያኔ ገና ውስጤን አመመኝ፡፡›› ይላችኋል፡፡

ሰውን አለመውደድና ጥላቻ የውስጥ በሽተኝነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ እናም መዋደድ ያስፈልገናል፣ መተሳሰብና ፍቅር ሊኖረን ይገባል፤ ከመለያየት መንገድ መራቅና አንድነታችንን ማጠናከር ቀዳሚው ስራ ነው፡፡ የካሳሁን ልጅ ቴዲ አፍሮ በጥቁር ሰው አልበምህ ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያኖች ትንሳኤን እንዲያከብሩ አድርገሃልና ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋር ብያለሁ፡፡

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል።

# ፅንስን ማቋረጥ የተፈቀደባቸው ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

አስታውሳለው ጥቂት ከማይባሉ ዓመታት በፊት በሰፈራችን ከሚኖሩ ወ/ሮ አረጋሽ ከተባሉ ሴትዮ ቤት ውስጥ ጕረቤት ተሰብስቧል። እግር በመተሳሰብ በሚዘረጋበት በዚህች ጠባብ ቤት ውስጥ በአንድ ጥግ አንድ የሽቦ አልጋ ይገኛል። በዚህ አልጋ ላይ ልጃቸው ሄለን ጠርዙ የተበጣጠቀ አዳፋ ብርድ ልብስ ለብሳ ኵርምት ብላ ተኟታለች። ሄለን ህመሟን ዋጥ አድርጋ ሊጠይቋት ከመጡት ጕረቤቶቿ የሚቀርብላትን ጥያቄዎች ‹‹በጕ ነኝ›› በሚል አጭር መልስ ትገላገላለች። ህመሟ ምን እንደሆነ አጥብቆ የሚጠይቅ ሰው ብዙም የለም። ለአንዳንድ አጥብቆ ጠያቂም እናቷ ኵላሊቷን እንዳመማት አስተዛዝነው ይመልሳሉ። አብዛኞቹ የሰፈር ሰዎች እንደሚሉት ግን ሄለን ፅንስ ስታስወርድ ከገጠማት ከፍተኛ አካላዊ ህመም ባልተናነሰ ከማህበረሰቡ የሚደርስባት ተፅዕኖ ስነ-ልቦናዋን በእጅጉ ጕድቶታል። በአይኗ ሙሉ አታይም። እርሷ ብቻ ሳትሆን ቤተሰቦቿም በአካባቢያቸው አንገታቸውን ቀና አድርገው እንዳይሄዱ ይሄው የሄለን ጉዳይ ምክንያት ሆኗል። በሀገራችን ውርጃ በግለሰቦች ላይ ከሚያደርሰው አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ችግር በተጨማሪ ማህበረሰቡ ለጉዳዩ የሚሰጠው የሞራል ደረጃ ዝቅተኛ እንደሆነ የሄለን ጉዳይ በተወሰነ መልኩ የሚያስረዳ ይመስለኛል። በህግም ደረጃ ውርጃን መፈፀም ከአስገዳጅ ሁኔታዎች በስተቀር /እነዚህ አስገዳጅ ሁኔታዎች በሕግ የተፈቀዱ ብቻ ናቸው/ ወንጀል እንደሆነ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ ተካቷል። ምንም እንኳ ፅንስን ማቋረጥ /ውርጃ/ በሕግ ደረጃ በመርህ የተከለከለ ቢሆንም አንዳንድ አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ወቅት ፍቃድ ባለው የህክምና ተቋም የሚደረግ ፅንስ ማቋረጥ ወንጀል ሊሆን እንደማይችል ሕጉ የደነገገ ሲሆን፣ እኛም ባለፈው ሳምንት ከእነዚህ ውስጥ በአስገድዶ መድፈር የመጣን ፅንስ ማስወረድ እንደ አስገዳጅ ሁኔታ ሊቆጠር ስለሚችል በሕጉ መሰረት ከተፈፀመ ወንጀል ሆኖ ሊቆጠር እንደማይችል አይተን ነበር። ዛሬም የተቀሩትን እናያለን።

በአንቀጽ 545 እንደተገለፀው በአንቀፅ 551 ውስጥ ከተጠቀሱት አስገዳጅ ሁኔታዎች በስተቀር ፅንስን ማቋረጥ ወንጀል እንደሆነና እንደ የአፈፃፀሙ የቅጣቱም መጠን ሊጨምር እና ሊቀንስ እንደሚችልም ህጉ ደንግጓል። በአንቀጽ 551 (1) (ለ) ውስጥ የተገለፀው እና ፅንስን ለማቋረጥ እንደ አስገዳጅ ሁኔታ የተቀመጠው ሌላው ጉዳይ የእርግዝናው መቀጠል የእናትየውን ወይንም የፅንሱን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ወይም የእናትየውን ጤና የሚጐዳ ከሆነ ወይም የፅንሱ መወለድ የእናትየውን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል የሆነ እንደሆነ ፍቃድ በተሰጠው የጤና ተቋም የሚደረግ ፅንስ ማቋረጥ እንደ ወንጀል ሊቆጠር አይችልም። በፅንሱ መቀጠል ምክንያት የእናትየው ጤና ወይም ህይወት እንዲሁም ፅንሱ ራሱ አደጋ ሊገጥመው የሚችሉበት የተለያዩ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ፅንሱን ባለበት ሁኔታ ይዞ መቀጠል ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚበልጥ እናትየው በጉዳዩ ተጐጂ እንዳትሆን እንዲሁም ፅንሱም ከተወለደ በኋላ የጤና ችግር ሊገጥመው ይችላል ተብሎ ሲታመን ፅንስን ለማስወረድ እንደ አስገዳጅ ሁኔታ ሊቆጠር ስለሚችል በወንጀል አያስቀጡም። ሌላው ከዚሁ ጋር በተያያዥነት የሚነሳው ፅንሱ ሲወለድ ምንም እንኳ ችግር የሌለበት ቢሆንና በወሊድ ወቅት በእናትየው ህይወት ላይ አደጋ ያደርሳል ተብሎ ከታመነ እና በጤና ባለሙያ ተረጋግጦ ሊወርድ የሚችል ከሆነ እንደ ሌላ አስገዳጅ ሁኔታ ሊታይ ይችላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው ችግር የፅንስ አለመርጋት፣ አለማደግ፣ የእናትየው ማህፀን ፅንሱን ለመሸከም በበቂ ሁኔታ ያደገ እና የተዘጋጀ አለመሆን፣ በወሊድ ወቅት የሚከሰቱ አደገኛ የጤና ችግሮች እና የመሳሰሉት በእናትየውም ሆነ በፅንሱ ላይ የእድሜ ልክ የጤና ችግር ወይም ሞት ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ሳይቃጠል በቅጠል እንደሚባለው ከወዲሁ መፍትሄ መስጠት ህጋዊ የሆነ ተግባር እንደሆነ ሕጉ ደንግጓል።

ሌላው በአንቀጽ 551 (1) (ሐ) ውስጥ የተጠቀሰው አስገዳጅ ምክንያት ፅንሱ የማይድን ወይም ከፍተኛ የአካል ወይም የጤና ችግር ያለበት ከሆነ እና ፍቃድ ባለው የጤና ተቋም ፅንስን ለማስወገድ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚደረግ ውርጃ (ፅንስን ማቋረጥ) በወንጀል አያስቀጣም። አንዳንድ ጊዜ ፅንሱ ሊድኑ የማይችሉ ወይም በሰው ሰራሽ የህክምና ዘዴ ሊቀየሩ የማይችሉ የአካል መዘበራረቅ ሊገጥመው ይችላል። ለምሳሌ የአይን አለመኖር ወይም በተገቢው ቦታቸው አለመቀመጥ፣ መንታ ሆነው አንድ የጋራ የሰውነት ክፍል የመጋራት ሁኔታ፣ ጆሮ፣ አፍንጫ ወይም ሌላ የሰውነት ክፍል አለመኖር ወይም ያልተገባ ቦታ ላይ መገኘት የመሳሰሉት በአንዳንድ ፅንሶች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተፈጥሮአዊ እና አካላዊ ጉድለቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚሁ ችግሮች በሚወለደው ህፃን ላይም ሆነ በእናትየው ወይም በቤተሰብ ላይ ተያያዥ ችግሮች ይዘው ሊመጡ ስለሚችሉ፣ በእናትየው ፍቃድ እነዚህ አካላዊ ችግሮች እንዳሉ ታውቆ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍቃድ ባለው የጤና ተቋም የሚደረግ ፅንስ ማቋረጥ እንደ ህገ-ወጥ ውርጃ ስለማይቆጠር አያስቀጣም።

አንቀጽ 551 (1) በውስጡ ከያዛቸው ፅንስን ለማቋረጥ አስገዳጅ ሁኔታዎች ተብለው ከተመደቡት ውስጥ በ551 (1) (መ) ውስጥ የተጠቀሰው እናትየው በአካላዊም ሆነ በስነ-ልቦናዊ ብቃት ማነስ ምክንያት ፅንሱን መውለድ የማትችል ከሆነ ፅንሱን ማቋረጥ ይፈቀድላታል። በንዑስ አንቀፁ መሰረት የጤና ሁኔታ እና የስነ-ልቦና ዝግጁነት መኖር እጅግ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ይህ ነገር ባልተሟላበት ሁኔታ ፅንስን እንዲቀጥል ማድረግ ለልጅም ሆነ ለእናትየው ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ፅንሱን ማቋረጥ ‹‹ህገ-ወጥነት የለውም›› በሚል ህጉ የአካልም ሆነ የስነ-ልቦና ችግር ላለባቸው እናቶች ፅንስን ማቋረጥ ይፈቅዳል። እናቶች በእድሜ፣ ሙሉ የአእምሮ ጤና አለመኖር እና በሌሎች የስነ-ልቦና ችግሮች ምክንያት ፅንሱን በበቂ ሁኔታ ለመንከባከብ እንዲሁም የራሳቸውን ጤና በበቂ ሁኔታ መከታተል አይችሉም የሚል የህግ ግምት ስላለ በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ካሉ ፅንስን ማቋረጥ ወንጀለኛ አያሰኛቸውም።

ነገር ግን ጉዳዩ በአንቀፅ 551 ንዑስ አንቀጽ አንድ እና ሁለት ውስጥ ከተቀመጡት አስገዳጅ ሁኔታዎች ውጭ የሚደረግ ፅንስ ማቋረጥ እንደ ወንጀል ስለሚቆጠር በጉዳዩ የተሳተፉ ማናቸውም ግለሰቦችም ሆነ ተቋማት እንደየጥፋታቸው ቅጣት ይጣልባቸዋል። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም በአንቀጽ 551 ውስጥ ለተጠቀሱት አስገዳጅ ሁኔታዎች ዝርዝር መግለጫ በማውጣት አስገዳጅ ሁኔታዎቹ በምን መንገድ መሄድ እንዳለባቸውና የእናትየውንም ፍላጐት በማይጐዳ መልኩ እንዲፈፀም ያደርጋል። ይህ ሁኔታ የሚያሳየው ምንም እንኳን በአንዳንድ አስገዳጅ ሁኔታዎች ፅንስን ማቋረጥ ክልክል ባይሆንም ህጉ ፅንስን ማስወረድ እንደማይቻል የያዘውን አቋም ያስረዳል። ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚያወጣቸውን ዝርዝር መግለጫዎች የማይፈፅም ግለሰብ ከአንድ ሺ ብር ባልበለጠ ቅጣት ወይም እስከ ሶስት ወር በሚደርስ እስራት ሊቀጣ ይችላል። ይሁንና በህግ ከተፈቀደው አስገዳጅ ሁኔታዎች ውጭ ፅንስ ያቋረጠች እናት በአንቀጽ 546 (1) ውስጥ በተጠቀሰው መሰረት ፍርድ ቤቱ በሚወስነው መሰረት በእስር ትቀጣለች። ከዚሁ ጋር በተያያዘ እናትየው ውርጃውን እንድትፈፅም መንገድን ያመቻቸ ወይም ውርጃውን እንድትፈፅም የረዳ፣ ያገዘ እና በውርጃው የተሳተፈ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው መሰረት በእስራት ሊቀጣ እንደሚችል አንቀጽ 546 (2) ደንግጓል። ከዚህ ሌላ እናትየው ውርጃን እንድትፈፅም መንገድ ያመቻቸ፣ ውርጃውን በሌላ ሰው ላይ ያደረገ ድርጊቱን የፈፀመው ከእርጉዟ ግለሰብ ፍቃድ ውጭ ከሆነ፣ ወይም እርጉዟ ፍቃዷን መስጠት በማትችልበት ሁኔታ ላይ ከሆነ፣ ወይንም እናትየው ፍቃዷን እንድትሰጥ በተለያዩ ማስገደጃ እና ማሳሳቻ መንገዶች በመጠቀም በነፃነት ፍላጐቷን ሳትሰጥ ፅንሱን እንድታቋርጥ ያደረገ ከሶስት እስከ አስር ዓመት ሊደርስ በሚችል እስር እንደሚቀጣ ህጉ ደንግጓል። ቸር እንሰንብት።

## የመድረክ ከየት ...

ከገፅ 2 የዞረ

በማዛመድ የብሔር የበላይነትን ማሳያ ትዕምርታዊ መተርጎሚያ አድርገው ያስቡታል። ይህ የልሂቃኑ አተረጓጎም ከዚህ ቀደም ከነበራቸው የብሄራቸውን ብቸኛ ወካይነት እምነት ጋር ሲዛመድ የህብረ-ብሔራዊውን ፓርቲ በአመራር ምስቅልቅሎሽ ውስጥ ይጥላዋል። መድረክ አመራሮቹን ለየፓርቲዎቹ በዙር እንዲዳረስ ለማድረግ መወሰኑም ይህን አደጋ ለመቀነስ እንደሆነ የፎረሙ የቅርብ ተከታታዮች ይናገራሉ።

የመቀናጀት ተግዳሮቶች

ከ1980ዎቹ መጀመሪያ ወዲህ ቁጥራቸው የበዛ የፖለቲካ ትብብሮች/ቅንጅቶች ተፈጥረው ከስመዋል። አሁን ያለውን መድረክን ጨምሮ እኒህን ጥምረቶች ያጠኑት ዶ/ር አስናቀ ክፍሌ ለትብብር መድረኮቹ መፈረካከስ ጥቂት ነጥቦችን በምክንያትነት ይደርድራሉ። የመጀመሪያው ፓርቲዎቹ ወደ ጥምረት ሲመጡ ይዘዋቸው ከሚገቡት መሰረታዊ ልዩነቶች ይነሳል። ዶ/ር አስናቀ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ወደ ጥምረት የሚሄዱት የጋራ መስማሚያ አላማዎችን ሳይቀርፁ ስርዓቱ ላይ ባላቸው ቅሬታ ብቻ እንደሆነ ያወሳሉ። ህብረቶቹ በዚህ መልክ መደራጀታቸው በተለይም የኢህአዴግ የበላይነትን ለመግራት እና ምርጫን ለማሸነፍ ቢጠቅማቸውም ያልተቻቻሉ ልዩነቶቻቸው ለመበታተን ይዳርጓቸዋል። ‹‹በፌደራሊዝም አመራረጥ እና በመሬት ጥያቄ ላይ ተፃራሪ አቋም ያላቸው ፓርቲዎች ይሰነብታሉ ብሎ መገመት አይቻልም›› ይላሉ ዶ/ር አስናቀ “The (UN) making of opposition coalitions and the challenge of democratization in Ethiopia, 1991-2011” በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናታቸው። ሌላኛው በዶ/ሩ የተጠቀሰው ነጥብ የውስጣዊ ዴሞክራሲ ዕጦት የኢትዮጵያ የተቃውሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በውስጣቸው የዲሞክራሲ ባህልን በሚጠበቀው ልክ አለማባጀታቸው ግለሰባዊ አምባገነንነትን ከማጎልበታቸው በተጨማሪ የአንጃ ፖለቲካን ለመግራት እንዳይቻላቸው አድርጓቸዋል። ዶ/ር ካሳሁን ብርሃኑ “Ethiopia; Beleaguered opposition under a dominant party system” በሚለው ፅሁፋቸው ፓርቲዎቹ ከአንድ ትውልድ በተነሱ ልሂቃን መመራታቸው ትውልዱ የሚታወቅበትን የሚስጢረኝነትን ባህርይ እንዲወርሱ እንዳደረጋቸው ያነሳሉ። እኒህን መሰል መገለጫዎች ያሏቸው ፓርቲዎች ወደ ጥምረት ሲሄዱ የሚወስኗቸው መሰረታዊ ውሳኔዎች በፓርቲዎቹ አመራሮች ብቻ የተሸበበ ይሆናል። በተለይም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ከባድ ተደርጎ የሚወሰደውን በሁለቱ የብሔርተኝነት ሙግቶች መሀከል የሚደረግ የማመቻመች ሙከራ የየፓርቲዎቹን አባላት ሀሳቦች ካላካተተ አደጋው ከባድ እንደሚሆን ዶ/ር አስናቀ ይናገራሉ። ዶ/ር አስናቀ ባለፉት ሃያ ዓመታት የተሞከሩትን ህብረቶች የተፈታተናቸው ብለው የሚጠቅሱት ሌላው ጭብጥ የመናፍቅነት የፖለቲካ ባህላችንን ነው። በብዙዎቹ ተመስርተው ባልሰነበቱ ቅንጅቶች መሪዎች መሀከል ሲከሰት የተስተዋለው ሌላውን በ‹‹ውስጥ አርበኝነት›› የመጠራጠር ስነ-ልቦና ለህብረቶቹ መድከምም ሆነ መፈራረስ ከፍተኛውን አስተዋፅኦ እንዳደረገ ዶ/ሩ በጥብቀት ይሟገታሉ።

የመድረኩ ነገዎች

ከወራት በፊት የመድረኩ አመራሮች ጥምረቱ ወደ ግንባር ፓርቲነት እንደተቀየረ ተናግረዋል። ነገር ግን ስብስቡን በግንባርነት እንዳይጠራ ያስቻላው ከምርጫ ቦርድ ዕውቅና ያለማግኘቱ ነው። ከጥምረቱ አባል ፓርቲዎች መሀከል በፕ/ር በየነ ጴጥሮስ እና በአቶ ጥላሁን እንዳሻው የሚመሩት ፓርቲዎች ራሳቸውን በግንባሩ ለማካተት አልወሰኑም። የፍትህ ምንጮች እንደሚሉት ሁለቱ ፓርቲዎች የገንዘብ እጥረትን በምክንያትነት በማቅረባቸው ባለፈው ሰኞ የተሰበሰበው የመድረኩ ስራ-አስፈፃሚ ጥምረቱ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው እና በአንድ ወር ውስጥ ውሳኔያቸውን እንዲያሳውቁ ወስኗል። ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የአንድነት የምክር ቤት አባል በበኩላቸው የእነዚህ ሁለት ፓርቲዎች በተለይም የፕ/ር በየነ መዘግየት መድረኩ ሲመሰረት እንደታሰበው ቀስ በቀስ ወደ አንድ ፓርቲነት የሚያመራ ከሆነ አንድነት በሚያቀነቅነው የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ትርክት ‹‹እንዋጣለን›› የሚል ስጋት እንደሆነ ይናገራሉ። ስለ ጉዳዩ ፕ/ር በየነ ለማናገር ባይፈቅዱም ፍትህ ያነጋገረቻቸው የወቅቱ የመድረኩ ፀሐፊ አቶ ጥላሁን እንዳሻው ስጋቱን ‹‹የተዛባ አመለካከት›› ሲሉ አጣጥለውታል። በሁለቱ የብሄርተኝነት ሀቲት አራማጆች መሀከል ይህን መሰል ግበረ-መልሶች ቢሰሙም ‹‹አንድነት በሚገባ እንዳይራመድ የሌሎቹ የመድረኩ አባላት መቀዛቀዝ አንዱ ምክንያት ነው›› ሲሉ አንድ ከፍተኛ የአንድነት አመራር ይወቅሳሉ። እርሳቸው ለዚህ በማሳያነት የሚጠቅሱት አሁን ፓርቲያቸው እየሞከረ ያለውን ህዝባዊ ስብሰባዎችን በማንሳት ነው። ‹‹እስከ አሁን ከተደረጉት ስብሰባዎች በበለጠ ቁጥር ቅስቀሳዎችን እንዳያኬሄድ ያገደው ከውስጣዊ ድርጅታዊ ችግራችን በተጨማሪ ሌሎቹ የመድረኩ አባላት ጉርምርምታ›› መሆኑን አመራሩ ያነሳሉ። ሌላኛው የፓርቲው የምክር ቤት አባል በበኩላቸው ‹‹አንድነት ‘Exit’ ስትራቴጂ ሊያስፈልገው እንደሚገባ›› እስከመናገር ሄደዋል።

የኢትዮጵያን የተቃውሞ ፖለቲካ የፈተሹ ፀሐፊዎች ‹‹ወደ ግንባር የሚሄድ ፎረም ወሳኝ ቅራኔ ያላቸውን ቡድኖች መሰብሰብ የለበትም›› ሲሉ ቢያስጠነቅቁም የመድረክ ልሂቃን ይህን መላምት በተግባር መሻር እንደሚችሉ ሲሟገቱ ተሰምተዋል። ለዚህ ፅሁፍ ፍትህ ያነጋገረቻቸው የተለያዩ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመድረኩ አባላት ግን ለመድረክ በሚገባ አለመንቀሳቀስ ከውጪያዊ ተግዳሮት በቀረበ ውስጣዊ ችግሮችም እንዳገቷቸው ይስማማሉ። So, are they strange bed fellows?

## ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ...

ከገፅ 9 የዞረ

የሽብርና የማተራመስ ስትራቴጂ አላቸው ተብለው ከተፈረጁት ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ወገን ጋር ንክኪ አለህ በሚል እወነጀላለሁ ብዬ አስቤውም አልሜውም አላውቅም። ነገር ግን መስመር በሳቱ ውሳኔዎች፣ሃቀኝነት በሌላቸው የደህንነት መረጃዎችና መሰረተ-ቢስ ውንጀላዎች ነው ግለሰቦች እየተያዙና እየታሰሩ የሚገኙት በሚል በተለያዩ ሚዲያዎች የምሰማቸው ዜናዎችና ትንታኔዎች እውነት ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚያረጋግጥልኝ ማስረጃ ለማግኘት ሩቅ መሄድ አላስፈለገኝም። በራሴና በሌሎች መምህራን ላይ የሚቀርቡ ሃሰተኛ ውንጀላዎች በቂ ናቸው።ችግሩ በራሴ ላይ ሲያነጣጥር አቤት ማለቴና ለምን ማለቴ አስከዛሬ በደል ደረሰብን የሚሉ ሌሎች ዜጎችን የነበሩበትን ሁኔታ ማስተዋልና መረዳት አለመቻልም ሆኖ ስለታየኝ ከፍተኛ የህሊና ፀፀትም እየተሰማኝ ነው።አሁንም ቢሆን ይህ የታሪክ አጋጣሚ እኔም እንዳየውና እንዲሰማኝ እድሉን ሰጠኝ እንጂ፤ የጉዳዩ ባለቤት ባልሆን ኖሮ ምናልባትም የመምህራንን ጥያቄ እርስዎ ለህዝብ ተወካዮች ባስቀመጧቸው መከራከሪያዎች መንገድ በመረዳት ብቻ ብቃት የሌላቸው መምህራንና ከሽብር ጋር ግንኙነት ያላቸው መምህራን ያነሱት ጥያቄ ነው የሚል የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ልደርስ እችል ነበር። ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ሆኖ ከስራ የተሰናበትኩት እኔው እጅግ ምርጥ ከሚባሉ፣በተማሪና በወላጅ ተወዳጅነት ካላቸው ታታሪ መምህራን አንዱ መሆኔና ለሃገሩ መልካም አሳቢ፣ ከመንግስት የሚያገኛትን ደመወዝ ሽራርፎና የዕረፍት ጊዜውን ሰውቶ ለትምህርት ቤት መሻሻል ስጥር የነበርሁ የትምህርት ቤታችን ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረትን(ወ.ተ.መ.ህ) ጨምሮ የቅርብ አለቆች የነበሩ የእርስዎ ፓርቲ አባላትን ጭምር በማስረጃነት ማቅረብ የምችል መሆኔን በድጋሚ ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ።የእርስዎ መረጃ ከወዴት እንደሆነ ግን ለመረዳት ይከብደኛል።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር እርስዎና ጥቂት ጓደኞችዎ በወጣትነት ዘመንዎ ጭቆናን፣ኢ-ፍትሃዊ አስተዳደርንና አምባገነንነትን ተቃውመው አልነበረም እንዴ ወደ ትጥቅ ትግል የገባችሁት?እርስዎና በአሁን ሰዓት በዙሪያዎ ያሉ ጥቂት አመራሮች በታሪክ አጋጣሚ የድልን ፅዋ ለማየት በቅታችሁ ይህቺን ሀገር ለመምራት ዕድሉን አገኛችሁ እንጂ ሌሎች ጀግኖች ጓደኞችዎ በረሃ ላይ ወድቀው የለም እንዴ? የተዋደቁትስ ለዜጎች ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ የሆነ የመንግስትና አስተዳደር ለማምጣት አልነበረምን? በነፃነት ሃሳብን የመግለፅና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችንን የማስከበር ነፃነት እንዳለን አልነበረም የነገራችሁንና ያስተማራችሁን? በአንድ ጀምበር ከስራ ማሰናበት ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ነው? መንግስት እንዲህ ፍትህን የሚያዛባና ውሃ በማይቋጥር ምክንያት የራሱን ሰራተኞች የስራ ደህንነት የሚያሳጣና አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ፤በሌሎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰራተኞችን በሚያስተዳድሩ የግል ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ዜጎችስ አያድርገውና በደል ቢደርስባቸው ለማን ነው አቤት የሚሉት?

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በሀገሪቱ ውስጥ ከለት ወደ እለት እየተባባሰ ከመጣው የኢኮኖሚና የገበያ አለመረጋጋት ችግር ጋር መጋፈጡ ሳያንሰው በየጊዜው በመንግስት መልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት ፍዳውን የሚያየው የሃገራችን ዜጋ ይብዛም ይነስም ቁጣውንና ኩርፊያውን በተለያየ አጋጣሚ ሲገልፅ ይታያል።ሆኖም የእርስዎ አስተዳደርም ሆነ ማንኛውም አስተዳደር መቶ በመቶ ለማርካት እንደማይችል በአንደበትዎ ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ለማርካት ባይቻል እንኳ ቢያንስ ተስፋ ሰጭና ቁጣን የሚያረግብ አስተዳደራዊ ምላሽ መንፈግ ተገቢ አይደለም። በምናገኘው ገቢ ህይወታችንን መምራት፣መኖርና ማስተማር አልቻልንም ብለው አቤቱታቸውን ያሰሙ መምህራንን ‹‹ብቃት የሌላቸው፣ ከነውጥ ፈላጊ ጎራ የተሰለፉ አሸባሪዎች ናቸው›› ብሎ በደፈናው መወንጀሉ ከእርስዎ የሃገር መሪነት ፤ክብርና ስልጣን ጋር የሚመጣጠን ተግባርም አይደለም፡፡እርስዎ የመምህራንን ጥያቄ እንዲህ ከተረጎሙት ከታች ያሉ ባለስልጣናት፣ የቢሮና የፅ/ቤት ሃላፊዎች የተሰጣቸውን ስልጣንና ሃላፊነት ባግባቡ ባይጠቀሙት የሚያስደንቅ አይሆንም።ለምሳሌ እኔ አድልዎ ተፈጽሞብኛል፣ባልዋልኩበት ነው ያዋላችሁኝ በሚል ከበታችዎ ያሉትን ሃላፊዎች ለመክሰስ እየተዘጋጀሁ ባለሁበት ወቅት ነው እርስዎ በተወካዮች ምክር ቤት ስማችንን ሲያጠፉ የዋሉት።ቢያንስ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣናት በዜጎች ላይ እንዲህ ያለ የህግ ጥሰት ሲፈጸም ዝም ብለው አያዩም በሚል እምነት ነበር በደሉኝ የምላቸውን የቅረብ አለቆች በፍርድ ቤት ላቆማቸውና ልከራከር ቆርጬ የነበረው። የኢህአዴግ ቁንጮ ከሆኑት ከእርስዎ አንደበት በጊዜ ቁርጤን አወቅሁኝ እንጂ።በአንድ በኩል የ‹‹መንግስት ሌቦች›› እንዳሉ ይነግሩናል፤ እየተዋጓቸው መሆኑንም ጭምር። በሌላ በኩል በዜጎች ላይ አድልዎና በደል የሚያደርሱና እያደረሱ ያሉ ባለስልጣናትን ውሳኔዎች ትክክለኛነት ሳያጣሩ መጠጊያ የሌለውን ደሃ መምህር ተባብረው ሲወርዱበት ይደመጣሉ።እኔን በመሳሰሉ ተመጣጣኝ የሆነ የመወሰንና የመቃወም አቅም የሌላቸውን ዜጎች ከሽብርተኝነት ጋር ማነካካቱ፣ ማስፈራራቱና በተፈጠሩበት ምድር ላይ በድህነትም ቢሆን ያለስጋት የመኖር መብታቸውን ከራሳቸው ሀገር መንግስት መነፈጋቸው ተገቢ አይደለም። ማንንም የሚጠቅም አይደለም።ለሃገር የሚጠቅሙ በርካታ ዜጎች ተስፋ ቆርጠው ባላሰቡትና ባላቀዱት ድንገተኛ የህይወት መንገድ እንዲጓዙ የተሳሳተ አቅጣጫ ማሳየት አይሆንም ብለው ያስባሉ? መቼም ምላሽዎ ‹‹መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው›› እንደማይሆን አስባለሁ።

# በአማኑኤል ጥላ ስር

ከቆዘመው እስከሚለፈልፈው፤ ፍዝዝ ካለው ያዙኝ ልቀቁኝ እስከሚለው፣ ከሚሳደበው አዬ ኃይለ ስላሴ ነኝ እስከሚለው ጊቢ ውስጥ ይታያል። ስልጣን ላይ ያለውን መንግስትን ከሚተቸው፣ የወደቀውን መንግስት መሪ እስከሚያወድሰው፣ ከሃይማኖት ስብከት እስከታሪክ ትንተና፣ ከማህበራዊ ህፀፅ ነቀፋ እስከ ፖለቲካዊ ትችት ይደመጣል። እዚህ የማይታይ የማይደመጥ ነገር የለም። ምክንያቱም ይህ አማኑኤል ነው።

### አንድ ለእናቱ

በ1930 ዓ.ም. የተመሰረተው አማኑኤል እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ህመምተኞችን ተቀብሎ ሲያክም ከሰባ ዓመታት በላይ ቆይቷል። ሆስፒታሉ አእምሮ ጤና ላይ ትኩረት በማድረግ ህክምና በመስጠት ብቸኛ ነው። ይህም ጫና እንዳበዛበት ይነገራል። በቀን በአማካይ 417 ህመምተኞች በሀኪም የሚታዩ ሲሆን ለታማሚዎችና አስታማሚዎች ስለህመሙ ግንዛቤ ለማስጨበጥም ሆነ ማብራሪያ ለመስጠት የስራው ውጥረት ለሀኪሞቹ እድል እንደማይሰጣቸው በአማኑኤል ሆፒታል በረነርነት ሚሰራው ተስፋዬ ጥራዝ ይናገራል። ከእንክብካቤና ግንዛቤ ከማስጨበጥ ይልቅ ሀኪሙ ሁሉንም ህመምተኞች ለማየትና ለማዳረስ እንደሚጥር ይገልፃል።

ከአዕምሮ ህመሞች አንዱ በሆነው Schizophrenia በአማካይ ከ100 ሰዎች አንዱ እንደሚታመም የሚገልፁት በአማኑኤል ሆስፒታል የአእምሮ ሀኪም ዶክተር ሉሉ በቃና ‹‹በአዲስ አበባ ውስጥ 3 ሚሊዮን ሰው አለ ብንል 1 በመቶው 300ሺ ነው አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ በSchizophrenia የተጠቃ 300ሺ ሰው አለማለት ነው። እዚህ ተኝተው የሚታከሙት ግን 200 ህመምተኞች ብቻ ናቸው።›› ይላሉ።

ያለው ሆስፒታል አንድ ብቻ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ህዝብ 15 በመቶ ማለትም 12 ሚሊዮን ህዝብ በአእምሮ ህመም እንደሚሰቃይ የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ ይገልፃል።

መረጃው እንደሚነግረን ቁጥሩ ቀላል የሚባል አይደለም። ከቁጥሩ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ስራ እየተሰራ ነው ለማለት ግን በጣም አዳጋች ነው። ሌሎች ሆስፒታሎችም የአእምሮ ህክምና መስጠት መጀመራቸው አንድ ለውጥ ቢሆንም ገና በሰፊው ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል።

ዶ/ር ሉሉ የህክምና አሰጣጡን እስካሁን ከነበረው አማኑኤልን ማዕከላዊ ከሚያደርግ አሰራር በማውጣት ወደሌሎች ሆስፒታሎች አገልግሎቱን ለማስፋፋት እየተሰራ መሆኑን ይናገራሉ። ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ ተማሪዎችን ማስተማርና በማስተርስ ዲግሪ ማስመረቅ መጀመራቸውን የገለፁ ሲሆን ‹‹በዲፕሎማም ትምህርት ለመስጠት ዝግጅት ጨርሰናል›› ይላሉ።

### ቤተሰብና ህመምተኛው

ያሬድ ወንድሙ ከመታመሙ በፊት ስለአእምሮ ጤና ምንም ግንዛቤ አልነበረውም። ከአእምሮ ህመሞች አንዱ በሆነው Schizophrenia በተሰኘ ህመም ወንድሙ ሲጠቃ ያደርጋቸው የነበሩት ነገሮች ከባህሪው መበላሸት የመጡ እንጂ የህመሙ ምልክቶች መሆናቸውን አልተረዳም ነበር። ወንድሙ ‹‹አባቴ ሰው ቀጥሮ ሊያስደበድበኝ ነው፣ ዱርዬዎች ገዝቶብኛል›› በማለት አባቱን በጠላትነት ያይ እንደነበር የሚናገረው ያሬድ፤ ይህን የሚለው ቤተሰቡን ለመረበሽ ሲል እንደሆነ ይገምት እንደነበር ይገልፃል። የአእምሮ ህመም ይሆናል ብሎ የገመተ አንድም የቤተሰብ አባል እንዳልነበረ ይናገራል። በኋላ ሲረጋገጥ ግን ወንድምየው የአእምሮ ህመምተኛ ሆኖ ተገኘ።

እንደያሬድ ዓይነት ሰዎች ጥቂት አይደሉም። ብዙ ሰዎች ስለአእምሮ ጤና ይሄ ነው የሚባል ግንዛቤ የላቸውም። በዚህ ግንዛቤ ማጣት ምክንያት ህመምተኞቹን ለመረዳትም ሆነ የተጠቂው ድርጊቶች የህመሙ ምልክቶች መሆናቸውን ለማወቅ ይቸገራሉ። የአእምሮ ጤና ጉዳይ ውስብስብ ከመሆኑ አንፃር ህመም መሆኑን ካወቁም በኋላ በርካቶች የህመምተኞቹን እውነታ መገንዘብ ያቅታቸዋል። ያሬድ የሚለውም ይህንኑ ነው።

‹‹የአእምሮ ህመም ታማሚ መሆኑን ካወቅንም በኋላ ያለበትን ሁኔታ እያየን አውቆ የሚያደርገው የሚመስለን ጊዜ ብዙ ነበር››

ወንድምየው በጣም ይጠራጠርና ሰው የሚያጠቃው ይመስለው እንደነበር የሚናገረው ያሬድ ሳይቀድሙኝ ልቅደም በሚል ስሌት ሰው ለማጥቃት ይሄድ እንደነበር ያስረዳል፤ አባቱን ለመውጋት ያደረገው ሙከራ ለጥቂት እንደከሸፈበት በመግለጽ ጭምር።

‹‹ይሄ ሁሉ ሆኖ፤ እሱ ያለበትን ትክክለኛ ሁኔታና ዓለም ልንረዳለት አልቻልንም ነበር›› ይላል።

### የአእምሮ ህመምና ህብረተሰቡ

አብዛኛውን የአእምሮ ህመም በመድኃኒት ኃይል መቆጣጠርና ማዳን ይቻላል። በብዙ ሰዎች ዘንድ ግን የአእምሮ ህመም መፍትሄ እንደሌለው ተደርጐ ይቆጠራል። ህክምና ከማግኘት በላይ በርካቶች መንፈሳዊ ‹ህክምና› ወደመሻት እንደሚሄዱ ዶ/ር ሉሉ ይናገራሉ። አንዳንዶች ከዓመት በላይ ፀበልና የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ህክምናዎችን ሲከታተሉ ቆይተው እንደሚመጡ የሚገልፁት ዶክተሩ መንፈሳዊ ህክምናን መከታተሉ በ‹ራሱ ችግር ባይሆንም ከህክምና መራቅ ችግር እንደሆነ ይናገራሉ። መድኃኒት መውሰድና የህክምና ክትትል ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነም ያስረዳሉ። የአእምሮ ህመም እንደማንኛውም ህመም በመድሀኒት መፍትሄ የሚገኝለት ነው ሲሉ ያስረግጣሉ።

የህብረተሰቡ አቀባበል ሌላው ከአእምሮ ጤና ጋር ተያይዞ የሚነሳ ችግር ነው። ህብረተሰቡ የአእምሮ ህመምተኞችን የሚቀበልበት መንገድ የተለየ ነው። የአእምሮ ህመምተኞች በህበረተሰቡ ከፍተኛ የሆነ መገለል ይደርስባቸዋል። ዶ/ር ሉሉ የአእምሮ ህመም ‹‹የሚያስፈራም፣ በሩቁ የሚሸሽም ነገር አይደለም›› ይላሉ። ‹‹የአእምሮ ህመም ምንም አይደለም ሌላኛው የሰውነት ገፅታ ነው›› የሚሉት ዶክተሩ በህክምና ለውጥ ሊመጣ እንደሚችልና በዓለም ላይ የአእምሮ ህመምተኞች ሆነው ከፍተኛ ቦታ ላይ የደረሱ ታዋቂ ሰዎች መኖራቸውን ያብራራሉ። አንዳንድ የአእምሮ ህመሞች የአእምሮን የማሰብ አቅም የማይነኩና የማስታወስ ችሎታንም የማይጐዱ በመሆናቸው ምሁራዊ ማንነት እንዳይኖር አያደርጉም። ትክክለኛ እንክብካቤና የመድሀኒት ክትትል ካለ የአእምሮ ህመምተኞች ስኬታማ የማይሆኑበት ምንም ምክንያት የለም።

አሁንም ግን የህብረተሰቡ ተፅዕኖ ቀላል አይሆንም። አንዴ ህመምተኛ ነው የሚል ስም ከወጣ በኋላ ወደጤንነት ቢመለሱም ህብረተሰቡ እንደጤነኛ ሊቀበላቸው አይደፍርም። በዛው በወጣላቸው ስም መጥራቱን ይቀጥላል። ይህም ያላቸውን ተቀባይነትና ተሰሚነት እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪነት የሚጎዳው ይሆናል።

ለዚህ ችግር መፍትሄው ህብረተሰቡን ማስተማርና ያለውን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ እንደሆነ ዶክተር ሉሉ ይገልጻሉ። በድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው በየቤቱ በድንገቴ ምርጫ የሚደረግ ትምህርት የመስጠት ፕሮግራም መጀመሩንም ይናገራሉ።

### ማንም ነፃ አይደለም

ማንም ከአእምሮ ህመም ነፃ ነኝ ብሎ መፎከር እንደማይችል ዶክተር ሉሉ ያስረዳሉ። ማንም ነፃ አይደለም። ሁሉም የመታመም አደጋ አለበት። ዶክተር ሉሉ ‹‹ማንኛችንም በማንኛውም ሰዓት ለአእምሮ ህመም ልንጋለጥ እንችላለን›› ይላሉ። አብዛኞቹ በዘር የሚተላለፉ ቢሆንም የአእምሮ ህመም መምጫ ምክንያቶች ግን በህክምናው አይታወቁም። የተለየ ክስተትና ማንኛውም ጫና ግን ለአእምሮ ህመም ሊያጋልጥ ይችላል። ስለዚህ እኔ ከአደጋው ክልል ውጪ ነኝ ማለት አይቻልም። በእርግጥ የአእምሮ ህመም ይህን ያህል የሚጋነን አደጋም አይደለም። እንደጉንፋንና እንደማንኛውም በሽታ ሁሉ አንድ ህመም ነው። የህክምና ባለሙያዎቹ እንደሚያስረዱት ከሆነ ህክምና በመከታተል ቁጥጥር ስር ሊውል ወይም ሊድን የሚችልም ነው።

ዶክተሩ ማግለሉ እንዲቆም የሚጠይቁትም ‹‹የአእምሮ ህመም ተለይቶ የተወሰኑ ሰዎች ጉዳይ አይደለም፤ ማንኛውም ሰው የአእምሮ ህመም ሊያጋጥመው ይችላል›› በማለት ነው።

### የለውጥ መንገድ

አሁን ካለው ሁኔታ የተሻለ ነገር እንዲታይ ግንዛቤ መፍጠሩ ላይ ተግቶ መስራት እንደሚያስፈልግ ግልፅ ነው። ዶክተር ሉሉ ‹‹HIV ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቶ ማግለሉ ላይ ለውጥ እንደታየው ሁሉ የአእምሮ ህመም ላይም መሰራት አለበት›› ይላሉ። ሚዲያው ትኩረት እንዲሰጠውም ይጠይቃሉ። ይህንኑ ግንዛቤ የመፍጠር ጉዳይ በተመለከተም እንደተቋም ያሰቡትን ሲናገሩ፤

‹‹ታላላቅ ሰዎችንና አርቲስቶችን ያካተተ የአእምሮ ጤና ክለብ ለማቋቋም አስበናል›› ይላሉ።

የአእምሮ ጤና በእርግጥም ትኩረትን የሚሻና ተባብሮ መስራትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል።

---

## ኪነጥበብ

# አታሚ፣ አሳታሚ፣ ታታሚ!

የአንድ ማነበረሰብ ስልጣኔ ሊለካም ሊያድግም የሚችለው ለራሱ ባህልና ሥነ-ፅሁፍ በሚሰጠው የክብር ቦታ መጠን ነው። ተረት እየተነገረው ያደገ ትውልድ ሳይነገረው ካደገው በተሻለ ስለማንነቱ ሊያውቅ ይችላል። ግብረ ገብነቱም ያን ያክል አስመስጋኝ ይሆናል። ቃል ህይወት ነው እንዲል ጸጋዬ ገ/መድህን ኑሮውን በቃል የመሰረተ ግለሰብ ማንበብን የመውደዱን ያክል የሚያነብ ጀግና ደግሞ ኑሮውን በጥበብ ይመራል። ጠቢብ ደግሞ ለሁሉም የሚመች ብልህ ነው።

ዘመናዊው ዓለም መምጣት ሲጀምር በአፍ የሚሰረጩ ወሬዎች እና መረጃዎች ወደ ህትመት ተሸጋገሩ። ይህ በዘመነው ዓለም ይሁን እንጅ ኢትዮጵያዊያንን በመሰሉ ጥንተ ስልጡን ህዝብና ሀገሮች በብራና ላይ የሚጻፉ ድርሰቶች የቀደመ ታሪክን አስቆጥረዋል።

በእርግጥ ስልጣኔ የሚገኘው ከመጻፍ አይደለም ከማንበብ ነው። ሲጽፍ የኖረ ትውልድ በጽህፈት ስራ ለመራቀቁ እንጅ እውቀት ጠገብ ሰልጣኝ ስለመሆኑ ልንመሰክርለት አንችልም ። እንግዲህ ቀድሞ በበግና በፍየል ቆዳ ላይ ፊደልን ስትከትብ የኖረች ሀገር የስነጽሁፍ እና ህትመት እንቅስቃሴዋ ምን ህይወትን አሳልፎ ስንት ዘመን ተንኳተተ? እንደጥናትም ባይሆን እንደጥናት መነሻ ወፍ በረራዊ ቅኝት እናደርግ ዘንድ ስንነሳ የአንባቢነት ፈቃዳችሁን በመለመን ነው።

ከጅምሩ የክህነት ቋንቋ እና የቤተመንግስት ቋንቋ ተብሎ እተመረጠ ጭዋ ከሊቁ በተገለለባት ሀገር የፊደል ትምህርት ቤቶች ለተመረጡ /ለተቀቡ/ ብቻ የተፈቀደ መስሎ በኖረባት ሀገር ከሀገሪቱ ስንቱ ክልል ከክልሎች ስንቱ መናገሻ ከዚያም ስንቱ ደብር የሊቃውንት መብቀያ እንደነበረ መናገር ብንጀምር ጎዳናችን በአጭር ያልቃል። የተመራማሪነቱ የጥበብ ፍለጋው የሊቅናው የፈላስፋነቱን ጉዞ የደፈሩት የቀደሙ ዘመዶችን ማመስገናችን ግዴታ ቢሆንም ጥቂቱ በተነጠቁበት የጥበብ መንፈስ ብዙሃኑ ተሳታፊ አለመሆናቸው ሳይቆጨን የሚቀር ርእስ ዐይደለም ።

ይህም ሆኖ ስነጽሁፋችን መንፈሳዊነት ላይ ያተኮረ ብጽዕና ፤ ቅድስና ፤ በዓል ማክበር፤ መመንኮስ፤ መመነን ፤ ላይ ያተኮሩ እንደመሆኑ ለስጋዊ ዓለምና ግለሰብ እንዲገባ ሆኖ ተወዳጅነትን ሳያገኝ እድሜውን ጠግቧል ። ከዚህ አልፈው ቤተመንግስት ነክ የሆኑ ሙዋለ ዜናዎች ደግሞ ምድራዊያን ነገስታትን በወርቅ የታነጹ፤ ከመላዕክት አጥንት የተፈለጡ ፤ ከእግዚአብሔር መንበር ጋር የሚያስተካክሉ፤ ከቅድስናቸው የተነሳ ወዛቸው ቅብኣ ቅዱስ የሆኑ በድምጽ ብቻ ዓለምን የሚያንቀጠቅጡ በመዳበስ ብቻ በረከትን እና ጤናን የሚያድሉ እየተደረጉ የተጻፉበት ዘመን ተወደደም ተጠላ ሀገሪቱ የሥነጽሑፍ ብቻ ሳይሆን የህትመትም ታሪክ አካል ናቸው። በእርግጥ ከባህል ከቅርስ ከእምነት እና መሰል ጉዳዮች ተነስተን እነዚህን ነገሮች ከተመለከትን ሀገሪቱን የሚያኮሩ ነባር ታሪክ መሆናቸውን አንክድም ።

እንደጥበብ ሥነጽሁፍ ፍልስፍና ሳይንስ ነክ ስልጣኔ መስፋፋት ያስተዋልነው እንደሆነ ግን ያን መሰል እሳቤ ወደ አንድ ጎን ያዘነበለ የጥበብ መዝራት እና ማጨድ እርሻ ወቅት እንደነበር መናገር እንገደዳለን። ዕውቀት ጥበብ ፍልስፍና ዕምነት ነክ ሆነው የሃይማኖት መሠረት ይዘው ይነሱ ነበርና ከዚህ እንኳ ልቆ የሚወጣ ወይም የወጣ ‹‹የዘመነ መባነን›› አሳቢ መናፍቅ የሚባል ቃላት ይለጠፍለታል።

ይህ አይነቱ አካሄድ ዘመናችን በሽቁጥቁጥነት ፤ በግብዝነት፤ በፈሪነት እና ባድር ባይነት መሰል ስሜቶች ተክነን እንድናድግ አስገድዶናል። በአደባባይ የቀደመ የስነጽፍ ዘይቤአችንን የእሳቤ አድማሳችንን የኑሮ ቅኝታችንን ለመናገር መሞከር ‹‹ ይቅሰፍህ ›› ለመባል አለዚያም በአፈ ሙዝ ለመቀሰፍ ወይም ለጅራፍ ግርፋት ሲዳርግን ኖሯል።

ይህ በጸሐፊዎች በአንባቢዎች እንዲሁም በልሂቃኑ ዘንድ ሲፈራ የኖረ እውነት ነው። የደፈሩ ሊቃውንት በሰም ለበስ ቅኔ መናገራቸው የታመነ ቢሆንም በስነጽሁፋችን ነባራዊ እውነት ከስነመለኮታዊ አለዚያም ስነመለኮት ነክ ከሆኑ እሳቤዎች ውጭ አለማቀንቀኑ የሃገሪቱ ሥልጣኔ አንድም የተቀላጠፈ እንዳይሆን ሁለትም ዘመነኛ ሀቆችን በጥርጣሬ እና በፍራቻ የማየት ተሰጥኦን እንዳናዳብር አድርጎናል።

ዘመናዊ ቴክኖሎጅ መጥቶ የብራና ጽህፈትን የሚደፍር ብርቱ በጠፋበት ዘመን እንኳ ብዙሃኑ ጸሐፊዎች ታሪክ ቢመሰርቱ ከቤተክህነት፤ ልብወለድ ቢጽፉ ከክርስትና ግብረገብ ከቆሎ ትምህርት ወዘተ ብቻ ስለሚሆን የተለየ ዕይታ የተስተናገደበት የሃገራችን ስነጽሑፋዊ ድጉስ ሳይታይ ዘመናት ተስከንትረዋል።

መጽሐፍት በብዛት እየተጻፉ እና እየተተረጎሙ መታተም ከመጀመራቸው በፊት የንጉሱን ፎቶ ይዞ መውጣት በጽህፈት ሰጥ ለጥ ብሎ እጅ መንሳት የተለመደ እውነት ሆኖ ቆየቷል። አላሰለቸም ያስደስታል ተገቢ ነው የሚል የአንባቢ አስተያየት እንደነበራቸው ልመሰክር ግን እቸገራለሁ።

በዚህ ሁሉ መኻል ስንጠቀምበት በኖርነው ቋንቋና ፊደላችን መጻፍ ይቻላል አይቻልም እየተባለ ዘመናዊ ፊደልን በቆጠሩ ጭሮ አዳሪዎች መካከል የተነሳው ሽኩቻ ጽድት ብሎ እስኪለይ ድረስ የነበረው እንቅስቃሴ የሚያረካ አልነበረም ፡ ፡ በኋላም የድርሰትና የህትመት ብሎም የንባብ አብዮት እንደተነሳ በሚነገርበት ሰባዎቹ ውስጥ ብዙዎች መታተማቸው የታመነ ቢሆንም የማጠንጠኛ ርእሳቸው ብዙ ፈቀቅ ያላለ የምልከታ መንገዳቸው ብዙ የማያስደነግጥ /የማያስገርም/ የቋንቋ ዐጠቃቀማቸው የተንዛዙ በብዙ መቶ ገጾች ጥራዝ ውስጥ ጥቂት ብቻ ምርጥ ሀሳብና ቃላት የሚነበብባቸው ባዘቶዎች እየታተሙ ወጥተዋል።

በዘመኑ የሚያስደስቱ እንቅስቃሴዎች ቢኖሩ የአሳታሚዎች ብርታት የመጽሐፍት ሽያጭ መጧጧፍ እና የአንባቢዎች ተነሳሽነት ነበር። ከዚህ ባለፈ ‹ወርቃማ› ተብሎ ከሚሞካሸው የሥነጽሑፍ ዘመናችን ወንዝ የተሻገረ ጠንካራ ድርስት ለመጥቀስ ይቸግረናል። ብርቱ ደራሲዎች ብለን የምናመሰግናቸው የራሳችንን ህይወት የራሳችንን እውነት የራሳችንን እምነት ለራሳችን ስለነገሩን እንጅ ወንዝ ተሻግሮ የተጠራልን ደራሲ ማን እንደሆነ በአንድ ድምጽ የምጠራው የለንም። ዛሬ መናገር የፈለግሁት ግን ከዚህ ወርቃማ ዘመን ወጥተን የመጽሐፍት እንቅልፍ ዘመን መጣበት እስከተባለው ሰማኒያ እና ዘጠናዎቹ እስካሁን አሳታሚ አታሚ እና ታታሚዎች ላይ ነው።

በሃገራችን የአታሚ ታሪክ መቼ ተጀመረ እንዴት መጣ የእኔ የዲስኩር አጀንዳ እንዳይደለ እየተረዳሁ ፤ ከደራሲያን ጋር በጋራ የሚሰሩ፣ በጥራት የሚሰሩ፣ ቀጠሮ አክብረው የሚሰሩ፣ ሚስጥር ጠብቀው የሚሰሩ ቢበረቱ እወዳለሁና ነው።

አባዛኛዎቹ ማለት ይቻላል አታሚዎች ከፈጣን ቴክኖሎጅ ጋር ሩቅ ይመስላሉ። ዓለም አቀፍ የህትመት ጥራት በደረሰበት ደረጃ የሚሰሩ ስንት ይሆናሉ? ሚስጥር ጠብቀው፣ ቀጠሮ ጠብቀው፣ ጥራት ጠብቀው የሚሰሩትስ? ከደራሲዎች ጋር ተግባብተው የሚሰሩትስ ስንት ይሆናሉ? ይችን ይችን እንዲመልሱ ያህል ነው። በቀጠሮ የማያስረክቡ ብዙ ናቸው። ከተሠጣቸው ቀለም ውጭ ሌላ ቀለም የሚያትሙ ጥቂት አይደሉም። የእገሌን ሥራ እያተምኩ ነው ብለው የሚያወሩ ከሚገባቸው በላይ ትርፍ የሚጭኑ በርካታ እንደሆኑ እናውቃለን።

በዚች ሀገር ብዙ የሚጠቀስ ታሪክ ያለው አሳታሚ ስንት ነው? እርሱስ ስንት መጽሐፍትን አሳተመ? ካሳተማቸውስ ምን ያህሉን በሰላማዊ እና በህጋዊ መንገድ አስፈጸመ? ከደራሲዎች ጋር የሚጋጩ የሚነጫነጩ ፤ የረቂቅ ሚስጥሮችን እስከመሸጥ የሚደርሱ ለደራሲው ክፍያ በጊዜው የማይከፍሉ የአሳታሚነትን ሃላፊነት በቅጡ የማያውቁ ወዘተ አሉ።

በዘመናችን በርካታ አሳታሚዎች የሉንም ፡ ፡ ቢኖሩም እንኳ መጽሔት እና ጋዜጣ የሚያሳትሙ እንጅ ተደራጅተው የደራሲያንን ስራ የሚያሳትሙ ስለመኖራቸው እርግጠኛ አይደለንም። ቢኖሩም እንኳ የትምህርት አጋዥ ከማሳተም ባለፈ የጥበብ መጽሀፍትን ማሳተም ላይ የተጨበጨበላቸው አይደሉም። ይሕ ጭቆና የተጫናቸው ደራሲዎች ራሳቸው አሳታሚ ራሳቸው አከፋፋይ ራሳቸው ሻጭ ሆነው የሀገሪቱን ስነጽሑፍ ሊታደጉ ይኳትናሉ።

ታታሚ ፊደል ሁሉ ይታተማል እንዴ? ከነበረው የተለየ ምን አመጣን ከተጻፈው የተለየ ምን ጻፍን? ዘመናችንን የሚዋጅ ምን ሥራ ሠራን? መጭውን ጊዜ የሚተነብይ ምን አደረግን? ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ እንቅፋቶቻችን የሚታገሉ መጽሀፍት ስንት አሳተምን? ከራሳችን ቅዠት ውጭ እንዲታተም ያልነው ታታሚ ምንድን ነው?

# የካድሬው የፍቅር ደብዳቤ 3



**አቤ ቶኪቻው**
abeto2007@yahoo.com

*ሰላም ወዳጄ... እንዴት ሰነበቱልኝ ልበል ወይስ እንዴት ከረሙልኝ? እኔ እንደምንም አለሁልዎት:: ለዛሬ ፍትህ ጋዜጣ በሰጠችን ቦታ የካድሬውን የፍቅር ደብዳቤ ይዤ መጥቻለሁ:: ይህ ታታሪ ሰራተኛ እና አፍቃሪ ካድሬ ከዛሬ በፊት ሁለት የፍቅር ደብዳቤዎቹ በአውራምባ ታይምስ መፅሄት እና ጋዜጣ ተስተናግዶለታል:: የዛሬውን ቁጥር ሶስት ደብዳቤ ደግሞ እነሆ በፍትህ ጋዜጣ ወጣ:: ከአፍቃሪው ፍትሀዊ ምላሽ እንዲገጥመው እንመኝለት...*

ይድረስ እንደ ሰማህታት ሀውልት በልቤ ውስጥ ለተተከልሽ፣ እንደ መደበኛ ግምገማ ሁሌ ለምታስጨንቂኝ፣ እንደ ድርጅታችን አርማ ዘወትር ለምትታይኝ፣ እንደ ውሎ አበል ለምትናፍቂኝ ውድ ፍቅሬ፤ ለጤናሽ እንደምን አለሽ? መቼም የተዘረጋው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እያለ በጤናሽ ላይ እንከን ያጋጥምሻል ብዬ አላስብም!

የኔ እመቤት እኔ ከድርጅታዊ ስራዬ ጎን ለጎን፤ ዘወትር አንቺን ማሰብ እና ስለ አንቺ መጨነቅ ኦቨር ታይም የማልጠይቅበት በራስ ተነሳሽነት የማከናውነው የየዕለት ተግባሬ ሆኗል::

በተለይ ይሄን ሰሞን ለምን እንደሁ እንጃልኝ ከእጄ የምታመልጪኝ እየመሰለኝ ስጨነቅ እና ስጠበብ ከርሜልሻለሁ::

ያስያዝሽኝ ፍቅር ህዝባዊ መሰረት እንዳለው ፓርቲያችን የጠነከረ ነው:: ቢሆንም ከአንቺ ዘንድ ያለውን ቁርጠኝነት እስከ አሁን ባለማወቁ የተነሳ እሰጋለሁ:: ከአሁን አሁን የኪራይ ሰብሳቢነት ባህርይ የተጠናወታቸው ግለሰቦች ወስደው ለግላቸው ያደርጓት ይሆን? ብዬ እጨነቃለሁ::

ያው አንቺም እንደምታውቂው በአሁኑ ግዜ የሁላችንም ዋነኛ ችግር ሙሰኝነት፣ ግለኝነት እና ኪራይ ሰብሳቢነት ነው:: ለሰዎች ያለማሰብ ለህብረተሰቡ ያለመጨነቅ የዘቀጠ አሰራር በየቦታው ተንሰራፍቷል:: ታድያ ምድረ ኪራይ ሰብሳቢ ሰብስቦ ሊይዝሽ የሞት ሽረት ትግል ሲያደርግ እየታየኝ ከአሁን አሁን አጣት ይሆን ብዬ እጨነቃለሁ::

የኔ እመቤት ነጋ ጠባ በስስት ነው የምመለከትሽ:: በሀገሪቱ ላይ የሚነሳ ማንኛውም ጉምጉምታ አንቺን የሚያሳጣኝ እየመሰለኝ ስጨነቅ ብትመለከቺኝ ታዝኚልኝ ነበር:: ጋዜጠኞች የሚያስቡት፣ ፖለቲከኞች የሚናገሩት፣ መምህራን የሚጠይቁት ሁላ እኔ እና አንቺን ለማለያየት ታስቦ ነው ስል እጨነቃለሁ:: የኔ ቆንጆ የአወሊያው ሶላት፣ የዋልድባው ሱባኤ ሳይቀር እኔን ከአንቺ ለመነጠል ሆን ተብሎ የሚጠነሰስ ሴራ እየመሰለኝ ስጋቴ እንደ ዋጋ ግሽበቱ ከእለት እለት እየጨመረብኝ ነው::

እውነቱን ለመናገር አንዳንድ ግዜ ሰዉን በሙሉ በአሸባሪነት ክስ ዘብጥያ አውርጄ እኔ እና አንቺ ብቻችንን የምንኖርባት ምድር ለመፍጠር እመኛለሁ::

አበዛሽው አትበይኝና ማንም እንዲጠጋሽ አልፈልግም:: እንኳንስ ሌላ ቀርቶ ጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበራት፣ የወጣቶች እና ሴቶች ሊግ፣ እንኳን አንቺን በነፃነት እንዲያቅፉብኝ አልፈልግም:: እኔው ማህበር ልሁንሽ የኔ ቆንጆ፣ እኔው ላደራጅሽ የኔ እመቤት፤ እኔው ልቀፍሽ የኔ ሸጋ:: እመኚኝ እሺ ካልሽኝ፤ በአጭር ግዜ መካከለኛ ፍቅር ካላቸው ግለሰቦች ተርታ እንሰለፋለን::

እሳሳልሻለሁ::

ለዚህም ነው፤ ተሳክቶልኝ ከአንቺ ጋር ግንባር ፈጥረን አብረን መኖር እስክንጀምር ድረስ ማንም እንዳያይብኝ፣ ማንም እንዳይረብሽብኝ፤ ብድር እና ቁጠባ ተቋም ውስጥ ላስቀምጣት ይሆን...? ብዬ የማስበው::

እውነቴ ነው የኔ ቆንጆ እንደምታውቂው፤ ከለበስኳት ሱፍ እና ከጥቂት መፅሀፎቼ ውጪ የሚቆጠብ ገንዘብ የለኝም:: ሀብቴ አንቺ ነሽ:: አንቺኑ ልንከባከብ፤ አንቺኑ ለዘላለም እንድትቆይ ክፉም እንዳይነካሽ፤ በቁጠባ ባንክ ላስቀምጥሽ:: እናም ከጫጫታውም ከግርግሩም የፀዳሽ ሁኚልኝ::

አረ የኔስ ስስት ለጉድ ነው፤ ሰሞኑን ያ ቴውድሮስ ካሳሁን ያወጣው አዲስ ዘፈን ተለቆ፤ ከተማዋን የግሉ ጭፈራ ቤት አስመስሏት የለ? እናልሽ ፍቅሬን በሙዚቃ ሊበጠብጡብኝ ነው እንዴ? ብዬ ለመላው የከተማ ነዋሪ ሙዚቃውን እንዲቀንሱ መመሪያ መስጠት ሲያሰኘኝ ሰንብቶልሻል:: እውነቴን ነው የኔ ቆንጆ አንቺ ካልሽኝ አደርገዋለሁ:: አንቺን ለመጠበቅ እንኳንስ ሙዚቃ ወንዝ እገድባለሁ::

አረ ሳልነግርሽ በቅርቡ ጓደኞቼ የዳቦ ስም አውጣላት ብለው አበሳዬን ሲያሳዩኝ ነበር:: እንደ አቅጣጫ፤ ሳንጋባ የዳቦ ስም ሊኖር እንደማይችል ግንዛቤው አለኝ:: ነገር ግን እውነትም ከወዲሁ ቅደመ ዝግጅት ባደርግ አይከፋም ብዬ አንዳንድ ስሞችን መርጨልሻለሁ::

ሚሊኒየም አበባ

ልክ አንቺን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር እንዳዋልኩ ያኔ ለእኔ አዲስ ጊዜ፤ አዲስ ዘመን እንደመጣልኝ እቆጥረዋለሁ:: ያ ግዜ ግን መቼ ይሆን...? በአስተማማኝ ሁኔታ እጄ ላይ ሆነሽ ለሚቀጥሉት አርባ እና ሃምሳ... አረ ያንሳል መቶ አመታት አብረን እንድንኖር እፈልጋለሁ::

ቦንድ አለሜ

ይህንን ስም የመረጥኩልሽ ልማት ላይ ያለሽን ቁርጠኝነት አሳምሬ ስለማውቅ ነው:: "እኔ ለአባይ በገንዘቤም በጉልበቴም ዘራፍ እላለሁ!" ያልሽ የልማት አርበኛ መሆንሽን መቼ አጣሁት? ከዛም በላይ ግን አንቺ ማለት ዛሬ በቁጠባ ባንኬ ያስቀመጥኩሽ እና ነገ የምመነዝርሽ ሀብቴ መሆንሽን ለማመላከት "ቦንድ አለም" ብዬሻለሁ::

ህዳሴ ወርቅ

አንቺ ለእኔ አዲስ ህይወት ነሽ:: ባለፉት ጨቋኝ ሴቶች ከፍቅር ልማት ርቆ ለቆየው ልቤ በአንቺ እንደሚያገግም አዲስ ራዕይ ይታየኛል:: እንግዲህ መቶ ፐርሰንት የእኔ ከሆንሽ ከዚህ በላይ ህዳሴ ከየት ይመጣል?

የኔ እመቤት ይሄ ብቻ አይምሰልሽ በርካታ ስሞችን አዘጋጅቼልሻለሁ:: "ግድብ ነሽ፤ ሽብር ይራቅ፣ ልማቴ፣ ሊዝ አዋጄ..." ምን ያላልኩሽ አለ! የአንቺን ይሁንታ ብቻ ላግኝ እንጂ ያዘጋጀኋቸውን ስሞች በሙሉ ከነ ምክንያቶቼ ዘርዝሬ እነግርሽ እና አሳታፊ በሆነ መልኩ ተወያይተንበት አንዱን እናፀድቃለን:: በአካሄዬ እንደምትደሰቺ ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ::

እመቤቴ፤

በየ አቅጣጫው የተነሱ ፀረ ፍቅር ሃይሎች በተቀነባበረ መልኩ ሊያለያዩን እንደሚያሴሩ አውቃለሁ:: አንቺም ይህንን ግንዛቤ ልትወስጂ ይገባል:: ማንም ወዳጅ መሳይ መጥቶ ጥገኛ እንዳይሆንብሽ ጥንቃቄ አድርጊ ዘንድሮ ማንም የማይታመንበት ሁኔታ ነው ያለው::

ውዴ

እንደምንም ብዬ አውራ ፓርቲሽ ሆኜ ለዘለቄታው አብሬሽ መኖር እስክንጀምር ድረስ ራስሽን ከኒዮ ሊብራል ሀይሎች ጠብቀሽ እና በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሀይማኖትሽ ፀንተሽ እንደምትጠብቂኝ ዘጠና ዘጠኝ ነጥብ ስድስት በመቶ እርግጠኛ ነኝ!

ከሰላምታ ጋር!

በመጨረሻም

እኔ አማን ያገናኘን! እላለሁ::

# የመለስ ዲስኩር ግዝፈትና ግድፈት



**አክመል ነጋሽ**
**(የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት ሲኒየር ኤዲተር)**
(akemelnegash@yahoo.com)

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በየጊዜው እየቀረቡ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸውን ማብራሪያዎች ሳደምጥ ቆይቻለሁ:: ከቀናት በፊት ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የመብት ንቅናቄ አስመልክቶ የእሳቸው ግላዊ አቋም ምን ሊሆን ይችላል?›› ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ ከእሳቸው አንደበት ምላሽ ማግኘት ችለናል:: በዚሁ የማክሰኞ የፓርላማ ውሎ እና ዲስኩር ብዙዎቻችን የቀድሞን ብቃታቸው (performance) እያሽቆለቆለ መሄዱን ታዝበናል:: በተለይ በሃይማኖት ጉዳይ የሰጡት ‹‹ትንታኔ›› እውነታዎችን ለጥጦ በማግዘፍና በማግደፍ የተሞላ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: በዚህ ጽሑፌ የእሳቸውን ሕጸጾች ከግላዊ ምልከታዬ በመነሣትም ለመጥቀስ እሞክራለሁ::

በቀዳሚነት ለጠቅላይ ሚኒስተሩ ጥያቄውን ያቀረቡት ‹‹የአጋር ፓርቲ አባል›› ጥያቄያቸውን ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ የተመራ (leading question) ማድረጋቸው መለስ ምላሹን አድበስብሰው እንዲያልፉት አጋዥ ሆኗቸዋል:: ጠያቂው ‹‹የአክራሪነት አዝማሚያዎች... መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል በሚል ሰበብ... በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት...›› የሚሉ ሐረጎችን በማከል ጥያቄውን እጅግ አቅልለውላቸዋል:: ምናልባትም ጥያቄው ከተፎካካሪ ፓርቲ አባል ተጠይቆ ቢሆን ኖሮ አብነቶችን በመጥቀስ ጥያቄው ከተግዳሮት ጋር ሊቀርብ ይችል የነበረ በመሆኑ የምላሻቸውም ይዘት ሊቀየር ይችል ነበር:: ሆኖም ያ ባለመሆኑ የጥያቄውን ዐውድ እንዳሻቸው እንዲቀያይሩት ምክንያት ሆኗል::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የመብት ንቅናቄ አስመልክቶ ምላሽ ሲሰጡ የተንደረደሩት ከሕገ-መንግሥቱ አንቀጾች ነው፤ በተለይም ስለ መንግሥትና ሃይማኖት መለያየት የሚደነግጉትን አናቅጽት:: በተደጋጋሚ ጊዜ እንዳስተዋልነውም ‹‹መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል›› ለሚለው ውንጀላ የገገሩው ፓርቲ ሰዎችም ሆኑ ልሳኖቻቸው የሚጠቅሱት የሕገ-መንግሥቱን የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት ድንጋጌ ነው:: ‹‹መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ በመሆናቸው ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ አንገባም›› የሚል ነው የብዙዎቹ መልስ:: የእሳቸውም መልስ ይኸው ነበር::

በመሠረቱ የአንድ ሕግ መደንገግ በራሱ ወንጀልን ከነአካቴው ሊያስቀም አይችልም:: አሁን ባለው ሁናቴ መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ መግባቱን የሚጠቁሙ የቪዲዮ፣ የድምጽ እና የሠነድ ማስረጃዎች በገፍ እየቀረቡ ሳለ እሳቸው እና መንግሥታቸው የቀረቡትን ማስረጃዎች የሚቀለብስ ሌላ ማስረጃ ከማቅረብ ይልቅ ‹‹ሕገ-መንግሥቱ ስለከለከለን አናደርገውም›› የሚል ሾላ በድፍን መልስ መስጠታቸው አግባብ አይደለም:: ምክንያቱም የሕግ መኖር ወንጀል ላለመፈጸሙ ዋስትና አይሆንም:: በአገሪቱ ሙስናን፣ ሥርቆትን፣ ጾታዊ ጥቃትን ወዘተ. የሚከለክሉ የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሕግጋት አሉ:: የእነዚህ ሕግጋት መኖር ግን ከላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎች ሊገታቸው አልቻለም:: እንደውም በተቃራኒው የወንጀሎቹ ቁጥር አሻቅቦ ነው የታየው:: የአቶ መለስም አሥተዳደር ዳር ዳር ከማለት ይልቅ ወዳጄ ተመስገን ከሳምንታት በፊት ያቀረባቸውን የመንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ማስረጃዎች ቢመልሱ ይሻላቸው ነበር:: ነገሩ ከየት አምጥተው ይመልሱታል?

የመለስ ‹‹ነባሩ›› እስልምና

ከሰሞኑ የገገሩው ፓርቲ ሰዎች ‹‹ነባሩ እስልምና›› የሚል ቃል አለቅጥ አብዝተዋል:: ከቀናት በፊት ያገኘሁትና ፓርቲው አባላቱን ሊያወያይበት ያዘጋጀው ባለ 25 ገጽ ሠነድ ‹‹ነባሩ እስልምና›› የሚል ቃል ደጋግሞ ሲጠቅስ አስተውያለሁ:: ቃሏ ልክ እንደ ‹‹ውሃ ማቆር››፣ ‹‹ውጤት ተኮር››፣ ‹‹ኪራይ ሰብሳቢ›› ዓይነት ቃላት አዲስና ልማታዊ ሳትሆን አይቀርም:: የሆነ ሆኖ መለስም በመልሳቸው ‹‹ነባሩ እስልምና›› የሚል ሐረግ ደጋግመው ጠቅሰዋል:: መለስ ሲያስረዱ ‹‹በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የነበረው ነባሩ እስልምና ሱፊይ የሚባለው ነው›› ብለውናል::

ይህ የአቶ መለስ አካሄድ አሁን መንግሥታቸው እያካሄደ ያለውን በ‹‹አሕባሽ›› አስተምህሮ የማጥመቅ ስትራቴጂ ትክክለኝነት ለማሳየትም ያለመ ይመስላል:: አቶ መለስ ‹‹የሃይማኖቱ አዋቂዎች እንደነገሩን›› የሚለውን ቃል በመደጋገም ‹‹አሕባሽ›› የነባሩ ሱፊይ አስተሳሰብ አካል እንደሆነ አስረድተዋል:: ‹‹ለመለስ ያስረዷቸው የትኞቹ የሃይማኖት አዋቂዎች ናቸው?›› ከተባለ አሁን ሕዝበ ሙስሊሙ ‹‹ሳንመርጣቸው በመንፈሳዊ ተቋማችን ተቀመጡብን፤ ስለማንፈልጋቸውም ይነሡልን›› ያላቸው ጠምጣሚ ካድሬዎች ናቸው:: ‹‹የ‹አሕባሽ›ን ሥልጠናም ሆነ ትምህርት እየሰጠ ያለው የሙስሊሞች መንፈሳዊ መሪ ድርጅት በመሆኑ ምንም አይመለከተንም›› የሚል ስሜት ነበረው መልሳቸው:: ሕዝቡ ‹‹መሪ ድርጅቱ ውስጥ የተሰገሰጉት ግለሰቦች ያልተመረጡ ናቸው፤ ምርጫ ይካሄድልን›› ብሎ፣ አቤቱታ አቅርቦ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴርም ምርጫ እንደሚደረግ ተስማምቶ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ቢያንስ በመርህ ደረጃ ከሥልጣን የወረዱ ሰዎችን አቶ መለስ ‹‹መሪዎቹ›› እያሉ መጥራታቸው በጣም ያሳዝናል::

በእርግጥ እሳቸው እንዳሉት ‹‹የሃይማኖት አዋቂ›› ካሏቸው ሰዎች ምክሩን አግኝተው ከሆነ ድምዳሜ ላይ የደረሱት፣ የመከሯቸው ሰዎች ተሳስተው አሳስተዋቸዋል:: ይህን በእርግጠኝነት ለመናገር ደግሞ ነብይ መሆን አይጠይቅም:: በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ የአስተሳሰብ መስመር (school of thought) የሚባል ጽንሰ ሐሳብ አለ:: የዚህ ጽንሰ ሐሳብ ዓይነተኛ ባሕሪ ከአንድ ልዩ ሥርዓት ጋር በልዩ ሁኔታ መቆራኘትን (specialization) አመልካች ነው:: ለምሳሌ ሱፊይ (ተሰዉፍ) ማለት መንፈሳዊ (spiritual) ነገሮች ላይ በጣም የሚያተኩር መስመር እንደማለት ነው:: ይህ የአስተሳሰብ መስመር በተገለጸው ሁኔታ ራሱን ከመንፈሳዊነት ጋር ያስተሳሰረ እንጂ ከሌላው ሙስሊም ተለይቶ ‹‹የተለየ ሙስሊም›› የሚባልበት ቀመር የለም::

ወደ መሠረታዊው ነጥብ ስንመጣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹‹አሕባሽ›› የነባሩ እስልምና አስተምህሮ ወይም ሱፊይ እንደሆነ ነግረውናል:: በመሠረቱ አሕባሽ ራሱን ‹‹ሱፊይ›› ብሎ ይጥራ እንጂ ‹‹ሱፊይ›› አይደለም:: ለዚህ ደግሞ የእሳቸው ንግግር በራሱ መልስ ይሰጠናል:: ‹‹ነባሩ እስልምና ነው›› ያሉት የአሕባሽ እንቅስቃሴ የተጀመረው ዐብደላህ አል ሐረሪ በተባለ የሐረር ሰው መሆኑን ነግረውናል:: ዐብደላህ አል ሐረሪ ደግሞ የሞተው ከዛሬ ሰባት እና ስምንት ዓመታት በፊት ነው:: እስልምና ግን በኢትዮጵያ ላለፉት 1400 ዓመታት ቆይቷል:: ታድያ መለስ ‹‹ነባር›› የሚሉት ከ 20 ዓመታት በፊት የተፈበረከን አንጃ ነው?

እንደ አቶ መለስ ንግግር ዐብደላህ አልሐረሪ በተወለዱበት ሐረር አካባቢ በ1930ዎቹ ትምህርታቸውን ማስተማር ስላልቻሉ ኢትዮጵያን ለቀቀው በሌሎች አገሮች አስተምህሮታቸውን አስፋፍተዋል:: ይህም ከቀዳሚው ንግግር ጋር ፊት ለፊት የሚላተም ነው:: ምክንያቱም ዐብደላህ አል ሐረሪ ትምህርቱን ማስተማር ሳይችል የቀረውና የተገፋው አቶ መለስ ‹‹ሱፊይ›› ያሉት ነባር ማኅበረሰብ የሰውየውን ትምህርት ሊቀበለው ስላልፈለገ እና ስለተጠየፈው ነው:: ወይም በመለስ መዝገበ ቃላት ‹‹ከ 20 እና 30 ዓመታት በፊት የገባው›› ሠለፊያ ገፍቶት አይደለም:: ይህ መከራከሪያ ‹‹አሕባሽ›› የነባሩም ሆነ የ‹‹ሱፊይ›› መስመር አካል እንዳልሆነ ያሳየናል::

ከሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮች አንጻር ስናየውም ‹‹አሕባሽ›› መንግስትም ሆነ እነሱ ራሳቸው እንደሚሉት ‹‹ሱፊይ›› አይደለም:: በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እውቅና ያለውና ሥርዓተ ትምህርቱን በሱፊይ የአስተሳሰብ መስመር የቀረጸው የግብጽ አል-አዝሐር ዩኒቨርሲተ የ‹‹አሕባሽ›› አንጃ የሱፊያን የአስተሳሰብ መስመር እንደማይከተል ሃይማኖታዊ ብያኔ ሰጥቷል:: በ‹‹ሱፊይ›› የአስተሳሰብ መስመር ልሂቅ የሆኑትና እንደ ዓለም አቀፍ ማጣቀሻ የሚወሰዱት ኢማም ወሕበቱ ዙሐይሊም እንዲሁ አንጃው የ‹‹ሱፊያ››ን የአስተሳሰብ መስመር በጭራሽ የማይከተል ስለመሆኑ በተመሳሳይ መልኩ ብያኔ ሰጥተዋል:: የ‹‹አሕባሽ›› አንጃ መሥራች ዐብደላ አል-ሐረሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ አሉ የተባሉ የ‹‹ሱፊያ›› ልሂቃንን ማክፈራቸው (ከእስልምና ወጥተዋል ብለው ብይን መስጠታቸው) ግለሰቡም ሆነ አንጃቸው ሱፊያ አለመሆኑን አስረጂ ነው::

ሸኽ ሐቢብ ዐሊ ጀፍሪ፣ ሸኽ ሙሐመድ ሰዒድ ረመዷን አል ቡጢ፣ ሸኽ ሸዐራዊ እና ሌሎችም በርካታ የሱፊያ ልሂቃን ሁሉ ‹‹ሙስሊም አይደሉም›› ተብሎ በ‹‹አሕባሽ›› አንጃ ብይን ተሰጥቶባቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ነጥቦች መለስም ሆኑ መካሪዎቻቸው ‹‹አሕባሽ›› ሱፊይ አለመሆኑን፣ የነባሩን እስልምና አስተምህሮም ያልተከተለ መሆኑን የሚያስገነዝቧቸው ይመስለኛል::

‹‹ሠለፊይ›› መጤው እስልምና?

አቶ መለስ በንግግራቸው ከ 30 እና 20 ዓመታት በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የእስልምና ዓይነት ‹‹ሠለፊይ›› የሚባለው እንደሆነ ነግረውናል:: ስለዚህ ቡድንም ትንታኔ ሲሰጡ ‹‹የሃይማኖት አዋቂዎቹ ነገሩኝ›› ማለትን አልመረጡም:: የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች ጥቂቶቹ የአልቃይዳ አባላት እንደሆኑና በብዙ የሽብር ተግባሮች ላይ እንደሚሳተፉም ነግረውናል:: ስለ‹‹አሕባሽ››

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

አለም አቀፍ

# ሱዳን-ዳግም ወደማይበርደው ጦርነት

ካሳሁን አ.

ሁሌም ግጭትና ጦርነት በማይርቀው የቀንዱ አካባቢ አገራት ዙሪያ ከጊዜ ወደ ጊዜ ችግሮች በመባባስ ላይ ይገኛሉ፡፡የአካባቢው አገራት እርስ በርስ ከሚያደርጓቸው ጦርነቶች በተጨማሪም በየአገራቸው ያለባቸውን ውስጣዊ ችግር መቅረፍ አለመቻላቸው ለበለጠ መለያየት እና መከፋፈል እየዳረጋቸው ይገኛል፡፡ ለዚህ አንዱና ዋነኛ ማሳያ የሚሆነው ትልቋ ሱዳን ነች፡፡ በሱዳን በቅርቡ የተካሄደው ህዝበ ውሳኔ ሁለቱን አገራት ከመከፋፈል እና በቀንዱ አካባቢ የነበረውን የአገር ብዛት ከማሳደግ ውጭ የታሰበውን ሰላምና መረጋጋት ማምጣት አልቻለም፡፡

በቅርቡ ደቡብ ሱዳን ሉዓላዊ አገር ከሆነች ወዲህ እንኳን አንስቶ በሁለቱ አገራት መካከል ‹‹ጠብ የለሽ በዳቦ››አይነት ተደጋጋሚ ግጭቶችን አስተናግደዋል፡፡ በተለይ በሁለቱ አገራት መካከል የሚገኙ በነዳጅ የበለፀጉ የድንበር አካባቢ ክልሎች ላይ ግጭቱን የከፋ አድርጎታል፡፡ በደቡብ ሱዳን እና ሱዳን መካከል ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች እስከ ዛሬ ድረስ ኃላፊነቱን የሚወስድ ወገን ባይኖርም ለግጭቱ አንዱ ሌላውን ተጠያቂ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

### መሰረታዊ ጥያቄዎች

በሁለቱ ሱዳናውያን መካከል ለበርካታ አመታት የዘለቀውን የእርስ በርስ ጦርነት እልባት ሊሰጥ የሚችል አንዳችም የመፍትሄ ሃሳብ እስከ አሁን ማግኘት አልተቻለም፡፡ የራስ ገዥ አስተዳደር ለረጅም ጊዜ ለዘለቀውን የእርስ በርስ ጦርነት እልባት ይሰጣል ቢባልም የአገራቱን የድንበርን ይገባኛል ውዝግብ ከማጉላት ውጭ አንዳችም መፍትሄ ማምጣት አልቻለም፡፡

በሁለቱ አገራት መካከል ላለው መካረር የሃይማኖት እና የጎሳ ልዩነት ትልቁን ድርሻ ቢወስድም ይህንን ተከትሎ የተወሰደው እርምጃ በራሱ መፍትሄ መሆን በቻለ ነበር፡፡ ደቡብ-ሱዳን እንደ አገር ስትመሰረት አብዛኛውን የነዳጅ ማውጫ አካባቢዎች በቁጥጥር ስር ያደረጉ ቢሆንም ይህንን ነዳጅ ለተቀሩት አገራት የሚያስተላልፉበት የነዳጅ ቱቦ ግን የላቸውም፡፡አገራቱ በመከፋፈላቸው፤ አስቀድሞ በሰሜን ሱዳን የነበረውን ደቡቦቹ ይጠቀሙበት የነበረው የነዳጅ ማስተላለፊያ ቱቦ አሁን አጥተውታል፡፡ ሰሜን ሱዳን ይህንን ማስተላለፊያ ቱቦ ደቡብ ሱዳን እንድትጠቀምበት ብትፈቅድም ደቡቦቹ ግን በሁለት ምክንያቶች ይሁንታውን አልተቀበሉትም፡፡ የመጀመሪያው ለነዳጅ ማስተላለፊያ ቱቦው ሰሜኖቹ የጠየቁት የኪራይ ሂሳብ ከፍተኛ መሆኑ አንዱ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ደቡብ-ሱዳን ሰሜን ሱዳንን አቋርጦ በሚያልፈው ነዳጅ ላይ የአልበሽር መንግስት ስርቆት ሊፈፅም ይችላል የሚል ስጋት አላት፡፡ በተጨማሪም ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ቀጥላ በአፍሪካ ቀንድ ሁለተኛዋ ወደብ አልባ አገር በመሆኗ ችግሩን የበለጠ ውስብስብ አድርጎታል፡፡

በሁለቱ አገራት መካከል በተለይ ገና ውሳኔ ያላገኘችው በነዳጅ የበለፀገችው ‹‹አቢዬ››ግዛት ለጊዜውም ቢሆን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አስተባባሪነት የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት የሰላም ማስከበሩን ተልዕኮ በኃላፊነት ወስዶ ማስተዳደሩ ለአካባቢው በአንፃራዊነት የተሻለ ሰላም እና መረጋጋት አጎናፅፎታል፡፡ ምንም እንኳን ግዛቲቱ ለወደፊቱ የለየለት የጦርነት ቀጠና ይሆናል የሚል ፍራቻ ከመኖሩ አንፃር፡፡

### ሄግሊግ-ቀጣዩ አቢዬ

በሱዳን የተጀመረው የ‹‹አዲስ አገር›› ምስረታ ፕሮግራም አንዱ ተያዘ ሲባል በሌላ በኩል ያለው ቀዳዳ እያፈሰሰ በየጊዜው አዳዲስ ዜና መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡ በተለይ ግጭቱ እንዳይበርድ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ከጀርባ ለጥቅማቸው የተሰለፉት የውጭ አገራት ኃይሎች ናቸው፡፡ በተለይ በአካባቢው የፈለቀውን እምቅ የነዳጅ ሀብት በበላይነት ለመቆጣጠር ሲባል እና አካባቢው ካለው ጂኦ-ፖለቲካዊ ስትራቴጂ አንፃር ተመራጭ ያደርገዋል ይላሉ በአፍሪካ ቀንድ ላይ ፖለቲካዊ ትንታኔ የሚያቀርቡ ሰዎች፡፡

የዚህ ሳምንቱ ግጭት ዋነኛው መንስኤ እ.ኤ.አ. በ2005 ዓ.ም. ሱዳን የራሷ ግዛት ያደረገቻትን የሄግሌግ ግዛት ደቡብ ሱዳናውያን በሃይል መውረራቸው ሲሆን ይህም ሱዳን ለቃጣችባቸው ጥቃት አፀፋዊ ምላሽ መሆኑ ብቻ የጁባ ባለስልጣናት አሳውቀዋል፡፡

‹‹በቅርቡ ድንበር አቋርጠው ሁለቱ አገራት እያደረጉት ያለው የአየር ድብደባ የተጀመረውን የሰላም ስምምነት ወደኋላ የሚመልስ ነው›› ሲሉ በአውሮፓ ህብረት የውጭ ግንኙነት ዋና ኃላፊ የሆኑት ካትሪን አሽተን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ጠቁመዋል፡፡ ይህንን ስጋት የአፍሪካ ህብረት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ አሜሪካም እንደሚጋሩት አስታውቀዋል፡፡

የአፍሪካ ህብረት የደቡብ ሱዳን ጦር ሰራዊት ግዛቲቱን የያዘበት አካሄድ ህገ-ወጥ ነው ሲል የኮነነው ሲሆን የደቡብ ሱዳን መንግስት በበኩሉ ከዚህ በኋላ ከግዛቲቷ ከወጣን ፊታችንን ወደ አቢዬ ግዛት እናደርጋለን ማለታቸውን ሮይተርስ በዚህ ሳምንት ዘግቧል፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ሁለቱ አገራት ዳግም ወደ ጦርነት የሚያመሩ ከሆነ ማዕቀብ እንደሚጠብቃቸው አስጠንቅቀዋል፡፡

የአለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይ ደቡብ ሱዳንን ‹‹ወራሪ›› አድርጎ የኮነነ ሲሆን ጦሯንም በተቻለው ፍጥነት እንድታስወጣ እና ሱዳንም እያካሄደች ያለውን የአየር ድብደባ እንድታቆም በይፋ ጠይቀዋል፡፡

እስካሁንም ለግጭቱ ጥርት ያለ መነሻ ምክንያት ማግኘት ባይቻልም አንዱ ሌላውን ከመውቀስ ግን አልቦዘኑም፡፡ የደቡብ ሱዳን ኢንፎርሜሽን ሚኒስትር የሆኑት በርናባ ቤንጃሚን ለሮይተርስ የዜና ወኪል እንደገለፁት ከሆነ ‹‹የሱዳን አየር ኃይል በግዛታችን ውስጥ ገብተው የነዳጅ ማውጫ ክልል በሆነችው ‹‹ዩኒቲ ግዛት›› ላይ ጥቃት ፈፅመዋል›› ሲሉ የአልበሽርን መንግስት ይኮንናሉ፡፡ ስለዚህ ይላሉ ሚኒስትሩ ለዚህ አፀፋ ይሆን ዘንድ ሌላኛዋን በነዳጅ የበለፀገችውን ሄግሊግ ግዛት መቆጣጠራቸውን ገልፀዋል፡፡ በተለይ ደቡብ ሱዳኖች ሱዳን ለምታደርስባቸው ጥቃቶች የሄግሊግን ግዛት እንደ መነሻ እየተጠቀመችበት ነው ለሚለው ክሳቸው አካባቢውን በመቆጣጠር ቅድመ ጥቃቶችን ማክሸፍ ይቻላል ብላ ታምናለች፡፡

ደቡብ ሱዳን ባለፈው ሐምሌ ስትገነጠል የአገሪቷን 75 በመቶ የሚሸፍነውን የነዳጅ ሃብት ጠቅልላ ወስዳለች፡፡ ይህም ከሰሜኑ በተሻለ ከነዳጅ ምርት ተጠቃሚ የሚያደርጋት ከመሆኑም በተጨማሪ ለመበልፀግ አቋራጩን መንገድ የያዘች አስመስሏታል፡፡ ይህንን ማድረግ እንዳትችል ግን ከፊቷ ብዙ እክሎች ተደቅነውባታል፡፡ ነዳጁን ማውጫ፣ ማጣሪያ እና ወደ ተለያዩ አገራት ለመላክ የምትጠቀምበት የማስተላለፊያ ቱቦ ሁሉም ያሉት በሰሜኑ ግዛት መሆኑ የተፈጥሮ ሀብቱ ብቻ መኖር ጥቅም አልባ አድርጎባታል ይላሉ ተንታኞቹ፡፡

በነዳጅ ማስተላለፊያ ቱቦ ክፍያ ዙሪያ፣ በድንበር ማካለል እና በሁለቱ አገራት ውስጥ ተበታትነው ስለሚኖሩ ዜጎቻቸው ጉዳይ ገና መግባባት ላይ አልደረሱም፡፡ ይሄ አንገብጋቢ ጉዳይ በቋፍ እያለ ነው እንግዲህ ሁለቱም አገራት በጥቂት ነገር መቆራቆዝ የቀጠሉት፡፡

### ቀጣዩ ፈተና

ሁለቱ አገራት በተቋጨውም ይሁን ባልተቋጨው የመከፋፈል ሂደት ላይ ብዙዎቹ መተማመኛ የላቸውም፡፡ በተለይ ደቡብ ሱዳናውያን ለረጅም አመታት ራሳቸውን ከጦርነት ጋር አላምደው መቆየታቸውና በውስጣቸው ያለው የተማረ የሰው ኃይል ውስን ከመሆኑ አንፃር በቶሎ ለማገገም ጊዜ ይፈጅባቸዋል፡፡ ስለዚህ አፋጣኝ እርምጃ ሊሆን የሚችለው ያላቸውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ መጠቀም ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ተፈላጊውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም፡፡ ለረጅም አመታት የቆየው የእርስ በርስ ጦርነት መገንጠልን እውን ቢያደርግም በተመሳሳይ መልኩ የግዛት ይገባኛል እና የድንበር ማካለልን ጥያቄ እንደ አዲስ ይዞ ብቅ ብሏል፡፡ ቀጠናው ለተወሰነም ጊዜ ቢሆን አንድ ሽክም ቀለለለት ሲባል ሌላ መዘዝ ይዞ ብቅ ብሏል፡፡ ከዚህ በኋላ በሁለቱ አገራት (የውጭው ጣልቃ ገብነት ሳይረሳ) መካከል የሚደረገው ጦርነት እንደ ከዚህ ቀደሙ በመንግስት እና በአማፅያን መካከል የሚደረግ ሳይሆን በመንግስታት መካከል የሚደረግ በመሆኑ ጥፋቱን እጥፍ ያደርገዋል፡፡ ከዳግም ጦርነቱ በፊት ቤጂንግ እና ዋሽንግተን እጃቸውን ማስገባት ካልቻሉ ቀጠናው ዳግም በከፋ መልኩ በጦርነት፣ በችጋር፣ በስደተኞች፣ ሊጥለቀለቁ ይችላል፡፡ እንዲህ አይነት ግጭቶች ድንበር ዘለል በመሆናቸው ለመፍትሄውም የሁሉንም አገራት የጋራ ጥረት ይጠይቃል፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ በሁለት መልኩ ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከታል፡፡ አንደኛው አብዛኛው ወታደሯን አደገኛ በሚባለው የአቢዬ ግዛት በብቸኝነት በማስፈሯ እና ዜጎቿ በብዛት ስራ ፍለጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ጁባ (የደቡብ ሱዳን ዋና ከተማ) የሚያደርጉት ፍልሰት ምክንያት የጦርነቱ መነሳት አይቀሬ ከሆነ ቀጥተኛ ተጨፍላቂ የሚሆኑት ዜጎቻችን ስለሚሆኑ አስቀድሞ የማምለጫ ስትራቴጂ መንደፍ እና ጉዳዩን በቅርበት መከታተል ያሻል፡፡

# ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ለውሳኔ ተቀጠረ

## - አቃቤ ሕግ በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ተጨማሪ አቤቱታ አቀረበ

በከሳሽ አቃቤ ሕግና በተከሳሾ እነ አንዷለም አራጌ መካከል በችሎት እየታየ ያለውን የወንጀል ክስ አስመልክቶ ‹‹በፍትሕ እና ነጋድራስ ጋዜጦች ላይ የተዛባ የችሎት ዘገባ እየወጣ ነው በሚል በአቃቤ ሕግ›› የቀረበውን አቤቱታና አዘጋጆቹ በፅሁፍ ያቀረቡትን መልስ መርምሮ መልስ ለመስጠት ፍ/ቤቱ ለማክሰኞ ሚያዚያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ቀጠረ፡፡

የፍትሕ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የአቃቤ ሕግ አቤቱታ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ከመጥሪያ ጋር ተያይዞ የቀረበው ሶስት የአቃቤ ህግ ቅሬታዎች ለዝግጅት ክፍሉ የደረሰው ማክሰኞ እለት ነበር፡፡ እናም ፍርድ ቤቱ በአዘዘው መሰረት አስተያየቱን ይዞ በትላንትናው ዕለት ከጠዋቱ 3፡30 በከፍተኛው ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት የተገኘ ቢሆንም፤ በችሎቱ አዳራሽ የተሰበሰበው ህዝብ ከአዳራሹ አቅም በላይ በመሆኑ ሰፊ አዳራሽ ወደሆነው 15ኛ ወንጀል ችሎት ዞሮ ጉዳዩ ታይቷል፡፡

ዓቃቢ ህግ ያቀረበው ቅሬታ ‹‹በተለያየ ጊዜ ከዚህ እንደከሚከተለው የተዘረዘሩትንና በኛ እምነት ለችሎቱ ህጋዊነት፣ የክሱን አቅራቢ ተቋማዊም ሆነ ሙያዊ ብቃትና ነፃነት የሚሸረሽር፣ እንዲሁም በማስረጃ ምዘና ረገድ የፍ/ቤቱን ዋነኛ ተግባር የሚያሳጡ /የሚያጎድፍ/ እንዲሁም በአጠቃላይ ሕዝቡ በፍትሕ ስርዓቱ ላይ እምነት እንዲያጣና ኢ-ሕጋዊነት እንዲሰፍን የሚያደርጉ ፅሁፎችን እያወጣ ስልሆነ…›› የሚል ነው፡፡

አንደኛው የአቃቤ ሕግ አቤቱታ ጋዜጣዋ በቁጥር 178 የካቲት 30/2004 ዓ.ም. የአንዷለም አራጌ ቃል ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት በሚል ርዕስ ውስጥ ‹‹..ይህ ውሳኔ ቀደም ሲል መከሰስ እንዳለብኝ ከወሰኑት አሳሪዎቼ እንደተላለፈ መገመት የሚከብድ አይደለም›› ያለውን እና ‹‹እውነቱን ለመናገር የእኔ ጉዳይ በአሳሪዎች በእነ አቶ መለስ እንጂ በወህኒ ቤቱ አሊያም በፍርድ ቤቱ እጅ ነው የሚል አንዳች ብኸርታ ኑሮኝ አያውቅም›› የሚለውን ነበር፡፡

የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ ለዚህ ለፍ/ቤቱ በፅሁፍ በገለፀው መልስ ላይ እነዚህ ቃላቶች ብቻ ሳይሆኑ ሙሉ ፅሁፍ እንኳን ቢቀርብ አቃቤ ሕግ ከያዘው ክስ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ሊገባው አለመቻሉን ጠቅሷል፡፡

እንዲሁም የአቶ አንዷለም ፅሁፍ በቀጥታ የሚገናኘው በየካቲት 23/2004 ዓ.ም. በቁጥር 177 በታተመው ጋዜጣ ላይ የፌዴራል ማረሚያ ቤት ‹‹የአቶ አንዷለም አራጌ ደህንነት አደጋ ላይ አይደለም›› በሚል ከወጣው ፅሁፍ ጋር መሆኑን ጠቅሶ ‹‹ማረሚያ ቤቱ በፍትህ ጋዜጣ ላወጣው ፅሁፍ ምላሽ ነው›› ብሏል፡፡

ይህ የአቶ አንዷለም ምላሽ በጋዜጣው ላይ መስተናገዱ የፕሬስ አዋጅ ‹‹በመገናኛ ብዙሃን በቀረበ የፍሬ ነገር ዘገባ መልካም ስሙና ክብሩ የተጎዳበት ማንኛውም ሰው ዘገባው በቀረበበት መገናኛ ብዙሃን ላይ ያለክፍያ መልስ የመስጠት መብት አለው›› በሚለው መሰረት መሆኑን የጋዜጠኛ ተመስገን ምላሽ ያስረዳል፡፡

ሁለተኛው አቤቱታም በጋዜጣዋ ቁጥር 181 መጋቢት 21/2004 ዓ.ም. በወጣው እትም ተከሳሽ ናትናኤል መኮንን ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት ‹‹ይድረስ ለክቡር ፍ/ቤት፤ ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ›› በሚለው ርዕስ ሙሉ በሙሉ ክሱን የሚያጣጥልና የሀገሪቱን መሪዎች ስም በመጥቀስ በእነርሱ እንደተሰራ በመግለፅ በሚል ነበር፡፡

ጋዜጠኛ ተመስገንም ‹‹መቼም የተከበረው ፍርድ ቤት እንደሚያስታውሰው አቶ ናትናኤል በችሎት የተከራከሩት ክሱን ክደው እንጂ አምነው አይደለም፡፡ ስለዚህ በዚህ ሁኔታ እየተከራከረ ያለ ተጨማሪ የተከሰሰበትን ክስን የማጣጣል መብት አለው›› በማለት የፅሁፍ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም የፍትህ ዋና አዘጋጁ አቃቤ ሕግ ምን ብለው እንዳጣጣሉ የገለፀው ነገር አለመኖሩን በመጥቀስ ‹‹የሀገሪቱ መሪዎችን ስም በመጥቀስ የሚለውም ቢሆን ግራ አጋቢ ነው፡፡ አንድ ሀገር ስንት መሪ ነው ያላት? የሆነ ሆኖ ይህ ጉዳይ ጥፋት ቢሆን እንኳን የሚመለከተው ተከሳሹን እንጂ ጋዜጣውን አይደለም›› ብሏል፡፡ እንዲሁም ተከሳሽ ‹‹ፅሁፉ የእኔ አይደለም›› ቢል ኖሮ የአቃቤ ሕግም ተቃውሞ ቦታ ይኖረው እንደነበር ጠቅሷል፡፡

በጋዜጣዋ ቁጥር 181 መጋቢት 21/2004 ዓ.ም. ‹‹የእስክንድር ነጋ ቃል›› በሚል ርዕስ ውስጥ የተመሰረተባቸው ክስ በሀሰት የተቀነባበረና የበቀል ግብ እንዳለው የተጠቀሰውን አቃቤ ሕግ ባቀረበው አቤቱታ ውስጥ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ፅሁፍ ውስጥ ‹‹ይጠርጠር ከተባለ የዐቃቤ ሕግ የሞያ ብቃት ጥያቄ ውስጥ የሚከት ከመሆን አያልፍም፣ ችግሩ ግን በዐቃቤ ሕግ የሞያ ብቃት ሳይሆን የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት…›› በባዶ እጅ ክስ እንዲመሰርቱ ሲገደዱ የሌለን ያለ አስመስሎ ከማቅረብ ውጭ አማራጭ የላቸውም የሚለውም ሌላኛው አቤቱታ ነበር፡፡ ዋና አዘጋጁም በአቃቤ ህግ ተመዞ የቀረበው ቃል ጋዜጠኛ እስክንድር በመጋቢት 19/2004 ዓ.ም. በዚሁ ችሎት ቀርበው ከሰጡት ቃል ውስጥ መሆኑን ለተከበረው ፍ/ቤት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

በችሎቱ ተከሳሾች ያቀረቡትን ቃል ጋዜጣ ላይ ሲታተም ልክ እንደ አዲስ እና ሌላ አስመስሎ ማቅረብ በእጅጉ የሚያሳዝን በመሆኑ መታረም አለበት ብሎ እንደሚያምን በመልስ ፅሁፉ ገልጿል፡፡

አቃቤ ሕግ በፍትህ ላይ ባቀረበው አቤቱታ ተከሳሾች ‹‹…የሰጡትን ቃል ብቻ መሰረት በማድረግ የነፃ ሚዲያ ስነ-ምግባር ምሰሶ የሆነውን ገለልተኛ ሆኖ የመዘገብን መርህ ወደ ጎን በመተው…›› የሚል ይገኝበታል፡፡

ጋዜጠኛ ተመስገንም ‹‹እውነታው ዐቃቤ ሕግ እንዳለው በተቋማችን የተዘጋጀ ዘገባ ሳይሆን በጋዜጠኝነት እና በመገናኛ ብዙሃን መርህ መሰረት ‹‹ለድምፅ የለሾች ድምጽ መሆን›› (Voice to voiceless) እድል በመስጠታችን ተከሳሾች ለፍርድ ቤቱ በገሃድ ያቀረቡትን የተከሳሽነት ቃላቸውን በመላካቸው ከላይ እንደተገለው በጋዜጠኝነት ሙያ መርህ መሰረት መስተናገድ የሚችል ሆኖ በመገኘቱ ለህትመት የበቃ ነው›› በማለት ክቡር ፍ/ቤቱ እንዲገነዘብለት ጠይቋል፡፡

‹‹ዐቃቤ ሕግ የተከሳሾችን ቃል ማውጣት የአንድ ወገን ስለሆነ ሚዛን አልጠበቀም ያለውም ቢሆን የዝግጅታችን ክፍል (ፍትሕ) ከሳሽም የሚፈልገው ካለና አዘጋጅቶ ካመጣ ልናወጣ ፈቃደኛ ነን›› ያለው ጋዜጠኛ ተመስገን አቃቤ ሕግ በፍ/ቤቱ ሽፋን ሞያዊ ስብዕናችንን ለመጋፋት የሚያደርገው ጥረት ተገቢ አለመሆኑን ታውቆ ጥያቄያቸው ውድቅ እንዲደረግ በምላሹ አካትቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የተመስገን ደሳለኝን እና የነጋድራስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሱራፌል ግርማ የፅሁፍ ምላሽ ተቀብሎ ካነበበና ለአቃቤ ሕግ እንዲደርሳቸው ካደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ሁኔታ አገናዝቦና መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት ለማክሰኞ ሚያዚያ 16ቀን 2004 ዓ.ም. 2፡30 ተለዋጭ ጊዜ ቀጠሮ ሰጥቶ ነበር፡፡ ሆኖም አቃቤ ሕግ ባለፈው ሳምንት በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ክንፈ ሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) ከቃሊቲ ወህኒ ቤት ‹‹ማቆሚያና ገደብ ያጣው የምስኪኗ እናቴ እንባ!›› በሚል ርዕስ የወጣው ፅሁፍን ጠቅሶ ተመሳሳይ አቤቱታ በማቅረብ ‹‹ፍ/ቤቱ ፍትህ ጋዜጣን በተለይ ያስጠንቅቅልን›› ሲል ፍርድ ቤቱን ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጋዜጠኛ ተመስገን በቀረበው አቤቱታ ላይ ምላሽ እንዲሰጥ ሲጠይቀው ‹‹ዐቃቤ ሕግ አሁን ያነሳው አቤቱታ ቀደም ሲል ባቀረበው አቤቱታ ላይ ስላልተያያዘ አሁን ምላሽ ለመስጠት ይቸግረኛል፡፡ በሚቀጥለው ቀጠሮ ላይ ከድርጅቱ ጠበቃ ጋር ተመካክሬ ምላሽ እንዳቀርብ እጠይቃለሁ፤ አሁን ገና በሰማሁት አቤቱታ ግን ምላሽ ለመስጠት አልችልም›› ብለዋል፡፡

የችሎቱ ዳኞችም ከተወያዩ በኋላ አዲስ ለቀረበው የአቃቤ ሕግ አቤቱታ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ከቀጠሮ በፊት በሬጂስትራል በኩል እንዲያስገባ በመግለፅ በመጀመሪያ በሰጠው ቀጠሮ አዘጋጆቹ በችሎት እንዲገኙ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተወዳጇን አዲስ ታይምስ መፅሔት
የፊታችን ማክሰኞ
ከበርካታ ወቅታዊ መረጃዎች ጋር
ይጠብቋት

# አርበኞች መሞትን ማን አስተማራቸው? ታላቁ ጴጥሮስ ነው ባርኮ የሰጣቸው



ከታዴዎስ ታንቱ

ትኩሱን ደማቸውን ውሾች ልሰዋል:: አሁን ቀዝቅዟል:: ከአፈር ተዋህዷል:: ጉንዳኖች ደግሞ ሰፍረውበታል:: በተራቸው የቅዱሱን ደም ይዋኙታል:: መስቀላቸው ከቀኝ እጃቸው አጠገብ ወድቋል:: ግራ እጃቸው ከአምባር መዋያ መልስ በጭቃ ተለውሷል:: ጥፍሩ እንኳን አይታይም! ልብሳቸውም በጭቃ ተለውሷል:: ራሳቸው በጥይት ተፈረካክሷል:: አንድ አሞራ እየበረረ መጥቶ በሬሳቸው ላይ ሊያርፍ ሲል በሰዎች ተባርሯል:: መላ አካላቸው ደቅቋል:: ዓይኖቻቸው ወደ አረንጓዴነት ተቀይረዋል:: አፋቸው በመጠኑ ተከፍቷል:: ሕዝበ ክርስቲያን በውስጡ ለውስጡ ያለቅሳል:: ማን ሬሳቸውን ደፍሮ ያንሳ? የፋሽስቶች ውሳኔ በቅፅበት ተፈፃሚ ይሆንበታል:: ሬሳቸው ተዘርሮ ውሏል:: ለብዙ ሰዓታት ተኝቷል:: የጨው ተራ አፈር በሐምሌ ዝናብ ቦክቷል:: ሰዎች የጀግናውን ሐዋርያ ሬሳ ላለመርገጥ ሲጠነቀቁ ይስተዋላል:: አንዳንዶች ግን በጉዳያቸው የህሊና ስሌት ተመስጠው ሲገሰግሱ ጭቃ በእጅጉ ያፈናጥሩበታል:: ከመንገድ ዞር ለማድረግ እንኳን የፋሽስቶች ፈቃድ ሊወርድ ይገባል:: ይህ ሳይደረግ ማን ይደፍራል? በገዛ ስሜቱ ስሜቱን ያስተናገደ ይገደላል! ሬሳው ውሎ ቢያድርም በዚያው ይቀጥላል!

በድንገት ግን ለውጥ ተስተውሏል:: የጀግናው ሐዋርያ ሬሳ ተነስቷል:: በቦታው አልነበረም:: ማን ወሰደው? ሲያልፉ ያዩት ሲመለሱ አጥተውታል:: ወስዶ የደበቀው ይታወቅ:: የሁሉም ጥያቄ ሆኗል:: የፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ዳኛ ደግሞ በጣም ተናድዷል:: የሚቀበርበትን ቦታ መወሰን ፈልጓል:: ምን ጉድ ነው እናንተዬ? ዳኛው ከመኻል ወንበር ተቀምጦ ቅጣቱን አፅድቋል:: አገዳደሉም በትእዛዙ ተፈፅሟል:: አሁን ደግሞ የቀብር ቦታ ምርጫ እንዴት የዳኛ ኃላፊነት ሊሆን ይችላል? የእኚህ ሐዋርያ ግፍ አልበዛም ትላላችሁ? ሬሳቸው ከተቀበረበት ከጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ተቆፍሮ እንዲወጣ ተደርጓል:: የዳኛውን ትእዛዝ ዳኛው ራሱ ካልቀለበሰው ማን ይቀለብሰዋል? ከከተማ ዳር ተወስዶ በምስጢር ስፍራ እንዲቀበር ለለማዳ አገልጋይ ባንዳዎች ትእዛዝ ወርዷል:: በምክንያቱ ምክንያት በምስጢር ተወስዶ በድብቅ ከአፈር ውስጥ ገብቷል:: አቡኑ በአደባባይ ተገድለዋል:: ነፍስ አልባ ተክለ አካላቸው ግን በበድን ይዘቱ ተሰውሯል::

አርበኛውና ሐዋርያው ብፁዕ ቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መገደላቸው በታሪክ ዓይን በቦግታ ይስተዋላል:: ጥያቄ አይታሰብም! የባንዳዎች ሎሌያዊ ሚና ግን በደረጃው ዘወትር አለመታሰቡ ለምንድን ነው? ተገቢም አላስፈላጊም ጥያቄ መሆኑን አንጣ! በታሪክ ሐቅ ላይ ከመጋረጃ በስተጀርባ ወግ የለም:: እውነት እንደ ወረደ ለትውልድ ይውረድ! ባንዳ ከባዕዳን ወራሪ ባላነሰ ደረጃ ኢትዮጵያን ጎድቷታል:: ታሪካችን ደግሞ ከባንዳና ከከሐዲ ነፃ ሆኖ አያውቅም:: ይህ ትውልድ የታሪካችንን ታሪካዊ ፍሰት አይጣ! ጀግኖች ሀገራችንን ጠብቀው ያቆዩት በየዘመኑ ባዕዳንና ባንዳዎችን ከትቢያ ጋር በማዋሐድ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: ይህ እውነት ነው! እውነትም ይህ ነው! ሌላ እውነት የለም!

ባሁኑ ሰዓት ዳኞች ከአንዲት ጥቁር አውቶሞቢል ወርደዋል:: ከችሎት አዳራሽ አጠገብ ደርሰዋል:: የመሐል ዳኛው ኢጣሊያዊው ኮንቴ ዴላ ፓርቶ ከፊት ሆኖ ሁለት ለማዳ አገልጋይ ባንዳ ኢትዮጵያውያን ተከትለውታል:: ወደ አዳራሽ እየገቡ ነው! አሁን ሶስቱም ዳኞች ገብተዋል:: ህዝቡ ለክብራቸው ከመቀመጫው ተነስቷል:: አዳራሹ በጆሮ ጠቢዎች ተሞልቷል:: ጆሮ ጠቢዎቹ ለማዳ አገልጋይ ወዶ ገባ ሆድ አደር ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ታውቋል:: ጥቂት የውስጥ አርበኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በአሳማኝ የቋንቋ ቃና አቡነ ጴጥሮስን እያወገዙ ተሰምተዋል:: ከጆሮ ጠቢዎች መካከል ኢጣልያኛ የሚናገሩ ከሁለት እንደማይበልጡ ለማወቅ ተችሏል:: በችሎቱ ላይ ከፍተኛ የሐዘን ድባብ ይነበባል:: ይነበባል! ይነበባል!

ኢጣሊያዊው የመሓል ዳኛ ፈገግ በማለት ህዝቡ እንዲቀመጥ ለወለሉ ትእዛዝ አወረደ:: ወዲያው እሱም ተቀመጠ:: ቀጥሎ የግራ ዳኛ ወንበር ይዟል:: ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ ይባላል:: ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ የክፍሌ ወዳጆ አባት መሆኑ ይመዝገብልን! የቀኝ ዳኛው በቀኝ ተቀምጧል! ብላታ አየለ ገብሬ ይባላል! የመኻል ዳኛውን ስሜት ይከታተላል! ባንዳ በጌታው ሳንባ ይተነፍሳል! ሕሊናውን በሊሬ የሸጠ ምን ሊሆን ይችላል? ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ በተፈጥሮአዊ ሞት ከዚህ ዓለም ተለይቷል:: ብላታ አየለ ገብሬን ግን ታህሳስ 7 ቀን 1953 ዓ.ም. ብርጋዲዬር ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ ገድሎታል:: እርግጥ ነው! በዕለቱ አርበኞችም ተገድለዋል:: ለነጥያን የመጣ ለጻድቃን ይተርፋል:: የነዋይ ወንድማማቾች የግድያ የሒሳብ ስሌት ግን በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር አይስማማም! የአምስት ዓመት አርበኞች የሃያ ዓመት ቀማኞች እንደ ነበሩ በሰንጠረዥ አስቀምጧል:: ገዳዮቹ በግልፅ ናቡቴ መኳንንትን ከህዝብ ጫንቃ ላይ ማውረድ የሀገር ባለውልታ ጀግና አርበኞችን መጻረር እንዳልነበረ ተናግረዋል:: ይህ የነዋይ ወንድማማቾች ድምፅ ነው! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! ይህ የነዋይ ወንድማማቾች ድምፅ ነው! ከአረንጓዴው ሣሎን!

አቡነ ጴጥሮስ ከወንበዴዎች ጋር በማበር ወንጀል ተከስሰዋል:: ፍርዱ ምን ሊሆን ይችላል? አቡኑ ውጭ ተቀምጠዋል:: እጆቻቸውን በረጅም ሰንሰለት ታስረዋል:: ሁለት ለማዳ አገልጋይ ባንዳዎች በአጠገባቸው ቆመዋል:: አንዱ ባንዳ ኢጣሊያንኛ ይናገራል:: ሁለተኛው ጆሮውን ቢቆርጡትም አይሰማም:: ዳኞቹ ለጥቂት ደቂቃዎች ሲወያዩ ቆይተዋል:: የመኻል ዳኛው ሰዓቱን ተመለከተ:: በመቀጠል ወደ ተቀመጠው ህዝብ አየ:: ብዙም አልቆየም:: ከቆሙት ኢጣሊያውያን ወታደሮች አንዱን ጠራው:: ወታደሩ ቀረብ በማለት ወታደራዊ ሰላምታ ሰጠው:: አቡነ ጴጥሮስ እንዲገቡ እንዲያደርግ ታዘዘ:: ወታደሩ በታዛዥነት አቋም ለሁለተኛ ጊዜ ለዳኛው ሰላምታ አበረከተ:: ትእዛዙ ለአቡኑ ጠባቂዎች ከመቅፅበት ደርሷል:: ጠባቂዎቹ አቡነ ጴጥሮስን ይዘው ተንቀሳቅሰዋል::

ትርጁማኖች ተነስተው ቦታቸውን ይዘዋል:: ሁለት ናቸው:: አንደኛው ደጃዝማች አርአያ ዋሴ የተባለ ሰው እንደነበር መረጃ ይዘናል:: ሁለተኛው ደግሞ ፊታውራሪ ሮዛርዮ ተብሎ ይታወቃል:: ሁለቱም ከማስተርጎም የዘለለ ሚና አልነበራቸውም:: አሁን አቡነ ጴጥሮስ ከችሎት አዳራሽ ገብተዋል:: ታዳሚው ህዝብ ከንፈሩን ይመጥጣል:: የመኻል ዳኛው በኢጣሊያንኛ የተደራጀውን የክስ ዝርዝር በደጃዝማች አርአያ ዋሴ አማካይነት ለአቡኑ ጴጥሮስ አሳውቋል:: አቡነ ጴጥሮስ በደንብ ሰምተዋል:: አቡኑ ምንም ነገር ቢመጣ በፀጋ ለመቀበል ወስነዋል:: ለሀገራቸው ነፃነት፣ አንድነትና ሉዓላዊነት እንደማያቅማሙ ፍርጥም ባለ ቋንቋ መልስ ሰጥተዋል:: እሳቸውም በአስተርጓሚ አንፀባርቀዋል:: በዚህ የድፍረት መልስ የመኻል ዳኛው ተናድዷል:: ወዲያው ሶስቱም ዳኞች አቡነ ጴጥሮስ በአደባባይ በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ በመወሰን መዝገቡን ተመላሽ አድርገዋል:: በፈጣን ችሎት አስቸኳይ ውሳኔ ተሰጥቷል:: አለቀ!

ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. አቡነ ጴጥሮስ በጥይት ይደበድባሉ:: ወሬው በመላው አዲስ አበባ ተሰምቷል:: ቁርጥ ቀን ሆኗል:: በዚያን ጊዜ ጨው ተራ ተብሎ ይታወቃል:: ዛሬ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ሕንፃ ዝቅ ብሎ የሚገኝ ስፍራ መሆኑን እንወቅ! ከጧቱ ሶስት ሰዓት አንስቶ ጨው ተራ በሰው ተጨናንቋል:: ጆሮ ጠቢው በበኩሉ ይርመሰመሳል:: አራት ሰዓት ሲሆን አቡነ ጴጥሮስ በበርካታ ለማዳ አገልጋይ ባንዳዎችና በጥቂት ኢጣሊያውያን ወታደሮች ታጅበው ከጨው ተራ ደረሱ:: ከፊታቸው ድፍረት ይነበባል:: ዘለዓለማዊ መንፈሳቸውን ለሟች ስጋ ላለማስገዛት ፀንተዋል:: እንደ አብርሃም በግ ተነድተዋል:: አሁን ከተመረጠላቸው ነጥብ ስፍራ ደርሰዋል:: ጥያቄ አልተነፈጉም:: ዓይንዎት በጨርቅ እንዲሸፈን ይፈቅዳሉ? መልስ ለመስጠት አላቅማሙም:: ፊታቸው ባይሸፈን ደስተኛ መሆናቸውን አረጋገጡ:: ተኳሽ ጓድ ተዘጋጅቷል:: አቡነ ጴጥሮስ ፊታቸውን ወደ መርካቶ አቅጣጫ እንዲያዞሩ ተደረጉ:: ዓይኖቻቸው እንዳልተሸፈኑ ልብ በሉ! ስምንት ተኳሾች አንድ ላይ አነጣጠሩባቸው:: አዛዡ ከጥቂት ጊዜአት በኋላ ትእዛዝ ይሰጣል:: አቡነ ጴጥሮስ በልባቸው ፀሎት ላይ ናቸው:: ‹‹አምላኬ ሆይ! ግፈኞች እኔን ባርያህን ሊገድሉኝ ተዘጋጅተዋል:: ለሀገሬና ለሃይማኖቴ እሞታለሁ:: ወዳንተ እመጣለሁ:: ነፍሴን ተቀበላት:: ሀገራችንን ጠብቃት::››

አዛዡ አሁን ጮኽ ባለ ድምፅ ትእዛዝ ሰጠ:: ስምንቱም ነፍሰ ገዳዮች ተኰሱባቸው:: አቡነ ጴጥሮስ ወደቁ:: የሕክምና ክፍል አዛዥ በወደቁበት ገልብጦ ተመለከታቸው ነፍሳቸው ገና ከስጋቸው እንዳልተለየች አስተዋለ:: ወዲያው ሽጉጡን መዝዞ በሶስት ጥይት ራሳቸውን አከታትሎ መታቸው:: ሞተዋል::

አርበኛውና ሐዋርያው ብፁዕ ቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ የኢጣሊያን ገናናነት አምነው እንዲቀበሉ ብዙ ተለምነዋል:: ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪቃ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መሆኗን አምነው ከተቀበሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መሪ እንደሚሆኑ ተነግሯቸዋል:: ግን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም:: ባንዳ መነኩሴ! ከመባል በላይ ምን ሞት አለ? የቪክቶሪ አማኑኤልን ንጉስነትና የቤኒቶ ሙሶሎኒን ቻንስለርነት ከዕውቅና እርከን አላሳደጉም:: ከሮማ ውድ ዋጋ ያለው ሽልማት እንደሚጠብቃቸው ተገልጾላቸዋል:: አቡኑ ግን በንቀት መልስ አልፈዋል:: ውብ አውቶሞቢል በትእዛዝ ከኢጣሊያን ሀገር እንደሚመጣቸው ቃል ተገብቶላቸዋል:: መልሳቸው ግን የተለመደ እምቢታ ሆነ:: በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሊሬ እንደሚሰጣቸው ተነግሯቸዋል:: አቡነ ጴጥሮስ ግን ምንም ዓይነት ቁሳዊ ሀብት አልለወጣቸውም:: በአማላጅ ጋጋታ አልተበገሩም:: ይልቁንም ምድሪቱም ጭምር ለጣሊያን እንዳትገዛ አወገዟት:: የኢትዮጵያ ነፃነት አይገሠሥም! የኢትዮጵያ ሕዝብ ሐይማኖት አይረክስም! ይህ የአቡነ ጴጥሮስ ድምፅ ነው!!

ሰማዕትነትን በድፍረት የተቀበሉት አርበኛውና ሐዋርያው ብፁዕ ቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ

## ለአቡነ ጴጥሮስ ከተቀኘው የተወሰደ

በመስከረም ወር 1868 ዓ.ም. በሰላሌ ዋና ከተማ በፍቼ ተወለዱ:: በሕፃንነታቸው በጎሓ ፅዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መጀመራቸው ታውቋል:: በመቀጠልም በደብረ ሊባኖስ ትምህርታቸውን በስፋት ተከታትለዋል:: ከዋሸራ በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል::

አርበኛውና ሐዋርያው አቡነ ጴጥሮስ እስከ 1921 ዓ.ም. ድረስ በየቦታው እየተዘዋወሩ አስተምረዋል:: የአድባራት አለቃም ሆነው አገልግለዋል:: በ1921 ዓ.ም. ወደ ግብፅ ሔደው ተሹመው መመለሳቸውም በህይወት ታሪካቸው ውስጥ ተወስቷል:: ከግብፅ ሲመለሱ የመንዝና ወሎ ጳጳስ ሆነው ሰርተዋል:: በ1928 ዓ.ም. ደግሞ ማይጨው ዘምተዋል:: የወገን ጦር ወደ ኋላ ሲመለስ እሳቸውም ተመልሰዋል:: ነገር ግን ትግላቸውን አላቋረጡም:: ይልቁንም በግንደ በረትና በሰላሌ የተጠናከረ የአርበኝነት እንቅስቃሴ ያደርጉ ገቡ:: በእርግጥ እሳቸው ራሳቸው ጠብመንጃ ይዘው ጥይት አጉርሰው በፋሽስቶች ላይ የተኩሱበት ወቅት አልነበረም:: ነገር ግን ህዝቡን በማረጋጋትና አርበኞችን በማስተባበር በኩል ትልቅ ተግባር አከናውነዋል:: መጠባበቂያ ጠብመንጃ ባለበት አካባቢ ደግሞ የመሳሪያ አጠባበቅ አመራር መስጠታቸው ታውቋል:: አቡነ ጴጥሮስ የጀግናው የደጃች ባልቻ አባነፍሶ የንስሓ አባት እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል::

ፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ወቅት አንስቶ በተከታታይ ጳጳሳትን ቀሳውስትንና መነኰሳትን እንደ ገደለ ታሪክ በቂ ማስረጃ ይሰጠናል:: በዚህም መሰረት በኢሊባቡር ውስጥ በጎሬ ከተማ አቡነ ሚካኤል ተገድለዋል:: እንዲሁም አለቃ መርሻ ወልደማርያም ሶስት ጣሊያኖችን ደምስሰው ራሳቸውም መስዋዕት ሆነዋል:: በደብረ ሊባኖስ ውስጥ ደግሞ 229 መነኩሳት ተገድለዋል:: እንዲሁም 129ዲያቆናትና መዘምራን በዚሁ በደብረ ሊባኖስ ውስጥ በግፍ ተረሽነዋል:: ጄኔራል ግራዚያኒ ራሱ አረጋግጧል:: ታሪክ ይናገራል::

በእውነት ስለእውነት እንናገር! አርበኛውና ሐዋርያው አቡነ ጴጥሮስ ንፁሕ የሐይማኖት አባት ነበሩ:: የህይወት ታሪካቸው ይመሰክራል:: ተምረውና አገልግለው በታላቅ ሰማዕትነት ወድቀዋል:: ወንጀል አልሰሩም:: ከባለስልጣናት ተመሳጥረው ጳጳስ ገልብጠው በትእዛዝ ጳጳስ አልተደረጉም:: በውጭ ሀገር አልኖሩም:: ሀብት ንብረት አልነበራቸውም:: ለሆዳቸው ኖረው የሞቱ አድር ባዮችን እየመረጡ ፍትሐተ ፀሎት አላደረጉም:: በሐይማኖት ፀንተው ከኖሩ አልተለዩም:: አቡነ ጴጥሮስ በሕይወት ዘመናቸው እሳቸውን ወክላ መግለጫ የምትሰጥ የስጋ ዘመዳቸው የሆነች ሴት አላዘጋጁም:: ለሟች ተክለ አካል መታሰቢያ በምዕመናን ገንዘብ የተሰራ ሐውልት አልነበራቸውም:: ማንም የፈለገውን ሐይማኖት መከተል እንደሚችል በመስበክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐይማኖት ምዕመናንን ሐይማኖታዊ ሞራል አልተፈታተኑም:: አቡነ ጴጥሮስ ለሐይማኖታቸው ኖሩ! ለሀገራችን ሰማዕት ሆኑ!

አቡነ ጴጥሮስ ታላቅ ሐዋርያ ነበሩ:: ታላቅ ተግባር ፈፀሙ:: በታላቅ ሰማዕትነት ወደቁ:: እውነተኛ የሐይማኖት አባቶች በታላቁ ሐዋርያ በአቡነ ጴጥሮስ መንፈሳዊ ኩራት ይሰማችሁ! ኢትዮጵያ እናታችንም ትኩራ!

አርበኞች መሞትን ማን አስተማራቸው?
ታላቁ ጴጥሮስ ነው ባርኮ የሰጣቸው::

## የመለስ ዲስኩር ... ከገፅ 12 የዞረ

ሱፊይነት ‹‹ዑለማዎቹ ነገሩኝ›› ያሉት አቶ መለስ ስለ ‹‹ሠለፊይ›› ብዙ ደስ የማይሉ ነገሮችን ሲናገሩ ‹‹አዋቂ›› አለመጥቀሳቸው በጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን በመረጃ ያልተደገፈ እና ወገንተኛ ዕይታ ያሳያል:: በመሠረቱ ለጠቅላይ ሚንስትሩ ‹‹ይሄ ሱፊይ ነው፤ ይሄ ሠለፊይ ነው›› የማለት ሥልጣን ማን ሰጣቸው? ይህን ክፍፍል ሲሠሩስ መነሻቸው ምንድን ነው? የሃይማኖቱ ሰዎች የራሳቸው የቁርኣን እና የሐዲስ መመዘኛዎች አሏቸውና::

አቶ መለስ ‹‹አንተ ሱፊይ ነህ:: አንተ ሠለፊይ ነህ›› የሚል ምደባ ማስቀመጣቸው አሁን የኢትዮጵያ ሙስሊም ልዩነቶቹን ትቶ በአንድ ላይ ለአንድ ዓላማ መቆሙ ስላላስደሰታቸው ይመስላል:: ወይስ የትናንቱን የልዩነት ጊዜ መመለስ ተመኝተው?

አቶ መለስ አንድ ቦታ ‹‹ሙስሊም›› ማለቱን ትተው ‹‹ክርስትያኑ እና ሱፊው በሰላም ይኖር ነበር›› ብለዋል:: ተመለከታችሁት!? ‹‹ክርስትያኑና ሱፊው…››! ይህ ምን ማለት ነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር?

እንደ አቶ መለስ እምነት የሱፊይ እስልምና በኢትዮጵያ ከሌላው ሃይማኖት ጋር ተቻችሎ ለዘመናት ኖሯል:: ምንም እንኳ አቶ መለስ ሱፊያን ‹‹ሰላማዊና ተቻችሎ የኖረ›› ብለው ቢጠቅሱትም እንቅስቃሴውን ግን ትኙ (passive) አድርገው ከመግለጽ አልተቆጠቡም:: ይህ ምናልባትም የኢትዮጵያን ‹‹ሱፊያ›› ካለማወቅና ካለመገንዘብ ይመስለኛል:: አቶ መለስ እንዳሉት የቀድሞዎቹ ሥርዓቶች አድሎአዊ አሥተዳደሮች ነበሯቸው:: እነዚህን አድሎአዊ አሥተዳደሮች በነፍጥ ጭምር ታግለው ሃይማኖቱ ለዚህ ትውልድ እንዲደርስ ያደረጉት ቀደምት ‹‹ሱፊይ›› አባቶቻችን ናቸው::

በኢትዮጵያ ታሪክ በርካታ እስላማዊ ሡልጣኔቶች (መንግሥታት) እንደነበሩ ይታወቃል:: እነዚህ ሁሉ ሡልጣኔቶች ምሥረታቸውን ያገኙትም ሆነ ይተዳደሩ የነበሩት በቱባ ሱፊዮች ነው:: በሊቢያ አረመኔውን ፋሽስት የጣልያን ቅኝ ገዥ ሲታገሉ የነበሩት ዑመር ሙክታር ‹‹ሱፊይ›› ናቸው:: ታሪካዊቷን እየሩሳሌም ከመስቀል ጦረኞች አላቅቆ በሙስሊሞች እጅ ያገባው ጦረኛ ሶላሐዲን አል አዩቢም ‹‹ሱፊይ›› ነበር:: ይህ ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስን የመከሯቸው ሰዎች (በእርግጥም መክረዋቸው ከነበር) መሳሳታቸውን ያሳያል::

ጠቅላይ ሚኒስተሩ ስለ ‹‹ሠለፊይ›› የገለጹት ባሕሪ በብዙ መልኩ እውነቱን ያገናዘበ አይደለም:: ስለ ‹‹ሠለፊይ›› ሲያወሩ በስፋት የሄዱበት ‹‹እስላማዊ መንግሥት›› የሚለውን ቃል ነው:: ‹‹ሠለፊይ›› በሌላው ዓለም እንዳደረገው ኢትዮጵያ ውስጥም እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት እንቅስቃሴ ያደረገ መሆኑን ቢጠቅሱም አስረጂ አድርገው ሊያቀርቡት የሚችሉት የምሳሌ እንኳ ማስረጃ ማጣታቸው የነገሩን ትክክል ያለመሆን ያሳብቃል:: አቶ መለስ የሚሏቸው ሰዎች በኢትዮጵያ እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት ጥረት እያደረጉ ከሆነ ማስረጃ የሚመስል ነገር ለምን ለፓርላማው አባላት አላቀረቡም?

በቁጥር የማነስም ጉዳይ በአቶ መለስ ንግግር ተዳስሷል:: ሠለፊዮች ‹‹መንግሥት ቁጥራችንን አሳነሰብን›› የሚል ዘመቻ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል:: ይህ ምኑ ከወንጀል ጋር እንደሚገናኝ አይገባኝም:: ከጥቂት ዓመታት በፊት የአማራ ሕዝብ ቁጥር ከተጠበቀው በላይ ማነሱን ተከትሎ አንድ የገዢው ፓርቲ የፓርላማ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ ‹‹ቁጥራችንን አሳነሳችሁብን›› በሚል ሙግት አስነስተው እንደነበር ትዝ ይለኛል:: የሕዝብ ቁጥር በብዙ መልኩ ብዙ ትርጉም በሚያስጥበት አገር የቁጥር ማነስ አለማነስ ጥያቄ ለምን በጠቅላይ ሚኒስተሩ መዝገበ ቃላት ከእስላማዊ መንግሥት ምሥረታ ጋር ይያያዛል?

ለጥያቄዎቻችንስ ምላሽ የሎትም?

በማክሰኞው የአቶ መለስ ንግግር አሁን እየተነሣ ያለውን የመብት ጥያቄ ‹‹ሠለፊይ›› ብለው ካሰቡት ወገን የመጣ ብቻ ተደርጎ ነው የቀረበው:: የመብት ጥያቄው ግን የትኛውንም የአስተሳሰብ መስመር ሳይለይ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ሙስሊም እየተንጸባረቀ መሆኑ አይጠፋቸውም:: በሚሊዮን የሚቀጠሩ ሰዎችን ጥያቄም ‹‹የጥቂቶች›› ብለው መግለጻቸው ተገቢ አይደለም::

ንቅናቄውንም አሁን በጎረቤት አገራት በግብጽ፣ በሊቢያ፣ በቱኒዚያ እየተካሄደ ካለው ማዕበል ጋር አቆራኝተውታል:: ሕዝቡ ያነሣው ከመንግሥት ሥልጣን ጋር ያልተነካካ ንጹህ አገራዊ የመብት ጥያቄ ቢሆንም ከሌላ አገር፣ በተለይም ከዐረብ አገራት አጀንዳዎች ጋር ተሳስሮ ቀርቧል:: ይህ የሚመነጨው ምናልባትም የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ኢትዮጵያዊነት ካለመቀበል ይሆናል::

ይህ ሁሉ ሆኖም ግን አቶ መለስ መሠረታዊውን የሕዝብ ጥያቄ መመለስ አልተቻላቸውም:: መንግሥት ‹‹ሕገ-መንግሥትን በማስከበር ሽፋን ሃይማኖት ውስጥ ገብቶ የሚፈጽመውን ተግባር ሊያቆም ይገባል›› የሚለው ጥያቄ ከእሳቸው ምላሽ አላገኘም:: ጠቅላይ ሚንስትሩ የ‹‹አሕባሽ››ን የግዳጅ ሥልጠናዎች በተመለከተ መንፈሳዊ ተቋሙ (መጅሊስ) በሥልጠናዎቹ ላይ ‹‹ብትመጡ ጥሩ ነው› ስላለን ብቻ ተገኝተን ስለ ሕገ-መንግሥቱ አስተምረናል›› ቢሉም ሕዝቡ የሚያውቀው ግን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና የፍትሕ ቢሮ ኃላፊዎች በነበሩበት መጅሊሱ ሥልጠናዎቹን በግዳጅ ጭምር ሲሰጥ እንደነበር ነው::

የመብት እና የነጻ መሪ ድርጅት ጥያቄውን አቶ መለስ ‹‹የጥቂቶች›› በሚል ሽፋን የእስላማዊ መንግሥት ምሥረታ ሩጫ አድርገውታል:: ‹‹ጥያቄ እያቀረበ ያለው›› የሚሉት የ‹‹ሠለፊያ›› ቡድን ብዙ እየሠራ መሆኑን ነግረውናል:: አቶ መለስ በመደምደሚያቸው ይሄ እንቅስቃሴ ‹‹በእንጭጩ መቀጨት አለበት›› ብለዋል:: በአቶ መለስ ኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም የዴሞክራሲ እና መብት ጥያቄ ማንሳት በሽብር ተግባር አስፈርጇል::

ዋይ ኢትዮጵያ::

# በጉራፈርዳ ወረዳ የተፈናቃይ ቤቶች በካድሬዎች መቃጠላቸውን መኢአድ ገለፀ - አንድ ተፈናቃይም ታርዶ ተገኝቷል

‹‹በደቡብ ኢትዮጵያ በቤንቺ ማጂ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ ሚያዚያ 6/2004 ዓ.ም. ለሚያዚያ 7 አጥቢያ ከጉራፈርዳ ተፈናቅለው ከአካባቢው የተሰደዱ ሰባት የአማራ ብሄር ተወላጅ ቤቶች በካድሬ ተቃጥለዋል›› ሲል መኢአድ ለፍትህ ገለፀ፡፡

መኢአድ በጉራፈርዳ ወረዳ አዲስ ዓለም ማርያም ሰፈር በስተጀርባ ገርጂ ከሚባለው አካባቢ ተፈናቅለው የተሰደዱ የአማራ ተወላጆች የሆኑ ሰባት ቤቶች ከነሙሉ ዕቃዎቻቸው በካድሬዎች በእሳት መጋየታቸውን የዓይን እማኞች ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ መግለጻቸውን ተናግሯል፡፡

ቤታቸው የተቃጠለባቸው አባወራዎች ብዙዎቹ ተሰደው አዲስ አበባ የሚገኙ እንደሆኑና ቤተሰቦቻቸው ግን እዛው ጉራፈርዳ ወረዳ ውስጥ በየዘመድ ቤቱ በጥገኝነት እንደሚኖሩ ፓርቲው አስረድቷል፡፡

መኢአድ የአካባቢው ተወላጆች የሆኑት ምኒጦች አሁንም ለአማራ ተወላጆች ፍቅር ያላቸው መሆኑንና ጥላቻው፣ በደሉና ግፉ እየተፈፀመ ያለው በካድሬዎች መሆኑን የመረጃ ምንጮቹ መናገራቸውን ገልጿል፡፡

የወረዳው ባለስልጣናት ግን መጋቢት 29/2004 ዓ.ም. የአማራ ተወላጆ የሆኑ ነዋሪዎችን ሰብስበው ‹‹እስከአሁን ከአካባቢያችን እንዲወጡ ያደረግነው 3000 ሰዎችን ብቻ ነው፡፡ በዕቅዳችን መሰረት 22000 ሰዎችን እናስወጣለን፣ እስካሁን የሰራነው ግን ከአቀድነው በጣም በጣም ትንሹን ብቻ ነው፡፡›› በማለት እንደነገሯቸው ምንጮቹ መግለጻቸውን መኢአድ ጠቅሷል፡፡

በተያያዘ ዜናም ኢድሪስ ዓለሙ የተባለ ወጣት ከጉራፈርዳ በቅርብ ርቀት ላይ በምትገኘው ኮይ በምትባል ቀበሌ ተገድሎ መገኘቱን መኢአድ ገልጿል፡፡ ወጣቱ ተገድሎ የተገኘው ሚያዚያ 8/2004 ዓ.ም. ጥዋት ሲሆን በገጀራ ታርዶ ማንነቱ እንዳይታወቅም ተቃጥሎ ሳር ተርከፍክፎበት እንደነበረ ፓርቲው አስታውቋል፡፡ ወጣቱ ከጉራፈርዳ ወረዳ ተፈናቅሎ በሬዎቹን በመያዝ ወደ ኮይ ሄዶ ከዘመድ ጋር ይኖር እንደነበረና የቀብር ሥነ-ስርዓቱ በኡቶዋ ቀበሌ ቁጥር አንድ መስጊድ ውስጥ እንደተፈፀመ መኢአድ ጨምሮ ገልጿል፡፡

# መዐሕድና ኢአዴድ የአርሶ አደሮችን መፈናቀል ተቃወሙ

የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ) እና የኢትዮጵያውያን አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢአዴድ) በጋራ ባወጡት መግለጫ የአማራ ተወላጅ አርሶ አደሮች ከደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ መፈናቀላቸውን ተቃወሙ፡፡

ፓርቲዎቹ ሚያዚያ 11/2004 ዓ.ም. ለፍትህ ጋዜጣ በላኩት መግለጫ ‹‹በደቡብ የክልል ባለስልጣን ትእዛዝ የተፈናቀሉት የአማራ ብሔር ተወላጆች ፍትሃዊ ያልሆነና ሰብዓዊነት የጐደለው ድርጊት ተፈጽሞባቸው አደጋ ላይ የሚገኙ ተፈናቃዮች በአስቸኳይ ቀደም ብለው ወደነበሩበት ቀዬ እንዲመለሱ እንጠይቃለን›› ብለዋል፡፡ እንዲሁም ‹‹በአሁኑ ሰዓት ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ለተፈናቀሉት አማሮች ወደነበሩበት ደቡብ ክልል እስከሚመለሱ ድረስ የፌዴራል መንግሥቱ አስቸኳይ የመጠለያ እርዳታና የካሳ ክፍያ እንዲሰጥ›› ጠይቀዋል፡፡

# አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ 5 ሚሊዮን ብር ተዘረፈ

የአንበሳ ኢንተርሽናል ባንክ ጉርድ ሾላ ቅርንጫፍ ሰራተኞች ቅዳሜ ዕለት ስራ ጨርሰው ከወጡ በኂላ ሰኞ ጠዋት ወደስራ ገበታቸው ሲመለሱ 5 ሚሊዮን 500 ሺ የሚጠጋ ገንዘብ ተዘርፎ መገኘቱን ምንጮች ለፍትህ ገለፁ፡፡

ባንኩን በዕለቱ ሲጠብቁ የነበሩት የጥበቃ ሰራተኛ የተሰወሩ ሲሆን የተቀሩት የጥበቃ አባላት ዝርፊያውን በተመለከተ ረቡዕ ሚያዚያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቀርበው ቃል ሰጥተዋል፡፡

ምንጮቻችን ባንኩ የተዘረፈው የፋሲካ በዓል ዕለት እሁድ ሚያዚያ 7 ቀን 2004 ዓ.ም ሳይሆን እንዳልቀረ አስረድተዋል፡፡ስለጉዳዩ ለማጣራት ባደረግነው ሙከራ የአንበሳ ባንክ ጉርድ ሾላ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ‹‹ፖሊስ የያዘው ጉዳይ ስለሆነ ምንም መረጃ የለኝም›› በማለት ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

# ኢትዮጵያ የእንስሳት ሀብቷን በአግባቡ መጠቀም አልቻለችም ተባለ

ኢትዮጵያ ካላት የእንስሳት ሀብት መጠን አንፃር የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች የኢንዱስትሪ ዘርፉን በሚገባ እንዳልተጠቀመችበት የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ2004ዓ.ም. በጀት አመት የ9 ወራት እቅድ አፈፃፀሙን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትላንትና ባቀረበበት ወቅት ‹‹ኢትዮጵያ ከአፍሪካ በእንስሳት ሀብት አንደኛ ነች ነገር ግን በቆዳው ኢንዱስትሪ ለሚመጡ ባለሀብቶች በበቂ ሁኔታ እያቀረበች አይደለም፡፡ ለዚህም ችግር መንስኤ የሆኑት ትክክለኛ የቆዳ አያያዝ፣ የከብት በሽታ እና ያልተስተካከለ የግብይት ስርዓት ናቸው›› ሲሉ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴሩ አቶ መኮንን ማንያዘዋል ተናግረዋል፡፡

ሚኒስቴሩ በቆዳ ኢንዱስትሪ ላይ ያለውን ችግር ለመፍታት እና አምራቹ የሚፈልገውን ጥሬ እቃ ለማቅረብ እየሰራ ነው፡፡ በጨማሪ ለአራት አለም አቀፍ የኬሚካል አምራቾች ፍቃድ ሰጥቷል፡፡ አምራቾቹም በከፊል ያለቀለትን የቆዳ ውጤት በማምረት ለገበያ ማቅረብ እንደጀመሩ ገልጿል፡፡

# ቻይናዊውን የገደለው ኢትዮጵያዊ ተፈረደበት

ቻይናዊ ዜግነት ያለውን ሚ/ር ሊ.ኪንግ ሻንግን በጠመንጃ ተኩሶ የገደለው ኢትዮጵያዊ ባሳለፍነው ማክሰኞ ዕለት በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በእድሜ ልክ እስራት እንዲቀጣ ተወሰነበት፡፡

ተከሳሽ ብርብርሶ ዳባ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 539/1/ሀ ላይ የተደነገገውን መተላለፉ የክስ ዝርዝሩ ያስረዳል፡፡ በዚህም መሰረት ተከሳሽ ሰውን ለመግደል አስቦ ጥር 29/2004 ዓ.ም. በግምት ከቀኑ 12፡00 ሰዓት አካባቢ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሸዋ ዞን በአዳ አበርጋ ወረዳ ኡላ ጉራ ቀበሌ ልዩ ቦታው ዳንጉቴ ከተባለው የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ማከፋፈያ ፕሮጀክት አካባቢ ይገኛል፡፡ከዚያም ቻይናዊ ዜግነት ያለውን ሟች ሚ/ር ሊ.ኪንግ ሻንግን ‹‹ለምን በፋብሪካው በጥበቃ ሥራ አልቀጠራችሁኝም?›› በማለት መንግስት ባስታጠቀው የውል ቁጥር 2421043 በሆነ ኤስ.ኬ.ኤስ የጦር መሳሪያ በቀኝ ትከሻው አካባቢ እና በግራ ደረቱ ትይዩ ጀርባው ላይ በሁለት ጥይት ተኩሶ በመምታት ይገድለዋል፡፡

በ26/07/2004 ዓ.ም በነበረው ችሎት ክሱ ተነብቦ ተከሳሽ ሲጠየቅ ክሱን በዝርዝር በማመኑ ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ በቅጣት አስተያየት አቃቤ ሕግ ምንም ያቀረበው ነገር አልነበረም፡፡ ሆኖም የተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ተከሳሽ ጥፋቱን ማመኑን፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን፣ በወቅቱ የድርጊቱን ውጤት ያለመገንዘብ ንቃተ ህሊና ላይ እንደነበረ እና ከዚህ ቀደም የወንጀል ሪከርድ እንደሌለበት በመጥቀስ የቅጣት ማቅለያ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱምየግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ማክሰኞ ዕለት በዋለው ችሎት ተከሳሹ በእድሜ ልክ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

# 13ኛው ዓለም አቀፍ የጤና ጉባዔ ሰኞ በአዲስ አበባ ይጀመራል

‹‹የዓለም አቀፍ ፍትሐዊ የህዝብ ጤና-ምቹ አጋጣሚዎችና ስጋቶች›› የሚል መልዕክት የያዘው 13ኛው ዓለም አቀፍ የጤና ጉባዔ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቅቆ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ሰኞ እንደሚጀመር ከትናንት በስትያ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር በሰጡት የጋራ ጋዜጣዊ መግለጫ አስታወቁ፡፡ በየሶስት ዓመቱ በህዝብ ጤና ጉዳዮች ላይ የሚመክረው የዓለም ሕዝብ አጠባበቅ ማኅበራት ፌደሬሽን /WFPHA/ ዓለም አቀፍ ጉባኤ፣ ከሁሉም የዓለም ማዕዘናት የሚመጡ የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ እስከ 3000 የሚደርሱ ተሳታፊዎች እንደሚካፈሉበት የተጠቀሰ ሲሆን ጉባዔው ከሚያዝያ 15-27/2004 ዓ.ም. ይካሄዳል፡፡

በዚህ ጉባኤ ላይ ባደጉትና በማደግ ላይ ካሉ አገሮች የህዝብ ጤንነት ጉዳዮች፣ የጋራ የሆኑ ተዛማጅ ጠቃሚ ተሞክሮዎችና ልማዶች፣ በጤና መስክ የተሰማሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ለጋራ ጥረቶቻቸው መሰናክል የሆኑ ከፍተኛ ችግሮችን እና ምቹ ሁኔታዎችን በዝርዝር እንደሚያቀርቡ በጋዜጣዊ መግለጫው ተገልጿል፡፡

እንዲሁም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ወቅታዊና ፍትሐዊ የሆነ የህዝብ ጤናን ከማስፈን አኳያ ስለሚያጋጥሙ ችግሮችና ምቹ ሁኔታዎች አመላካች ጥናታዊ ስራዎቻቸውን በሚመለከት ፍሬ ሃሳቦችን የያዙ አጭር ዘገባዎች /Abstracts/ ያቀርባሉ፡፡

# የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ጥያቄ ምላሽ አላገኘም ተባለ

የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከመታጠፍ እንዲቆጠብና እንዲታጠፍ የተወሰነው ውሳኔ ድጋሚ እንዲታይ በትምህርት ክፍሉ የቀረበው ጥያቄ ምላሽ አለማግኘቱ ተገለፀ፡፡

የትምህርት ክፍሉ መጋቢት 17 ቀን 2004 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጉዳዩን እንዲያጤነው የጠየቀ ቢሆንም እስካሁን ምላሽ አለማግኘቱን ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

ትምህርት ክፍሉ በጻፈው ደብዳቤ ‹‹አዲሱና በቅርቡ ስራ ላይ እንዲውል የተወሰነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ መዋቅር፣ እስካሁን በሰብዓዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ ስር የነበረውንና የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት የሚባለውን ክፍለ-ትምህርታችንን ከስሩ የሚነቅል ሆኖ አግኝተነዋል›› በማለት ውሳኔው የክፍለ ትምህርቱን መዘጋት ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ብሔራዊ ማንነትና አንድነት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ሊያስከትል ይችላል በሚል እንደሚሰጋ ገልጿል፡፡

ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ቀርቶ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት፤ የትግርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎ ክፍለ-ትምህርት፣ የኦሮምኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ- ትምህርት በሚባሉ የትምህርት ክፍሎች ብቻ እንዲጠቃለል ተደርጓል፡፡

እንዲሁም ‹‹አዲሱ የቋንቋና ስነ-ጽሑፍ ፎክሎር ትምህርት አደረጃጀት ከሰፊው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ማንነትና አንድነት ይልቅ ለተናጠላዊ ብሔር-ብሔረሰባዊ ማንነቶች (Fragmented ethnic identities) ትኩረት ከመስጠቱም በላይ፣ በጠቅላላው ከ80 በላይ ከሚሆኑት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባህሎችና ባህላዊ ጥበባት መካከል ለሶስቱ ብቻ ቦታ በመስጠት ሌሎቹን ትኩረት የሚነፍግ በመሆኑ ሀገሪቱ ዛሬ ከምትመራበት የፌዴራሊዝም ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ፖሊሲ ጋርም የሚጋጭ ሆኗል›› ብሏል - ደብዳቤው፡፡

# ‹‹ፊት ለፊት ስንኞች›› እና ‹‹ብርሃን›› የተሰኙ የግጥም መድብሎች ለገበያ ቀረቡ

ፊት ለፊት ስንኞች፣ ስልክሽን ልያዘው እና ሌሎች አጫጭር መጣጥፎችን በአንድ ላይ ያዘጋጀው ገነነ ግርማ (የካሰች ልጅ) መጽሐፍ ለሽያጭ መቃረቡን ደራሲው ለፍትህ ገለፁ፡፡ የፊት ለፊት ስንኞች በሚለው ስር 58 ግጥሞችን ያካተተው መፅሀፉ ስልክሽን ሊያዘው በሚለው ሁለተኛ ርዕሱ ውስጥ አጫጭር መጣጥፎችን በማካተት ለንባብ የቀረበው መጽሐፍ 163 ገፆች ያሉት ሲሆን 29.00 ብር ዋጋ እንዳለው ጨምረው ገልሰፀዋል፡፡

በመላከ ስሜነህ የተፃፈው ‹‹ብርሃን›› የግጥም መድብል በያዝነው ሳምንት ለንባብ በቅቷል፡፡ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተዘጋጀው ግጥም መድብል 120 ገጾች ሲኖሩት 23.00 ብር ለሽያጭ መቅረቡን ደራሲው ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

# ‹‹አሉ›› ፊልም ሰኞ ይመረቃል

ባሏ የሞተባት ሴት በባሏ ሞት ምክንያት መገለል ሲደርስባት በጥንካሬ አልፋ ስኬት ላይ ስትደርስ የሚያሳየው ‹‹አሉ›› ፊልም በራኬብ ፊልም ፕሮዳክሽን ተዘጋጅቶ በደራሲና ዳይሬክተር ራኬብ በቀለ የተሰራው የፍቅር ፊልም ሰኞ ሚያዝያ 15 ቀን 2004ዓ.ም. በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ (ማዘጋጃ ቤት) ይመረቃል፡፡

በፊልሙ ላይ ቴዎድሮስ ስዩም፣ ማርታ ጌታቸው፣ ደንኤል ታደሰ እና ሌሎች የተወኑበት ሲሆን ፊልሙን ሰርቶ ለማጠናቀቅ 2 ዓመት ያህል መፍጀቱን አዘጋጆቹ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

# ‹‹ማኅርሚሳቢብ›› መጽሐፍ ለገበያ ቀረበ

‹‹ኮብላይ››፣ ‹‹ጥብቅ ምስጢር›› እና ‹‹ነፀብራቅ›› የሚባሉትን መጽሐፍ ለአንባቢያን በመቅረብ የሚታወቁት ደራሲ አሰግድ መኮንን 4ኛ መጽሐፋቸውን ‹‹ማኅርሚሳቢብ›› በሚል ርዕስ ለአንባቢያን ማቅረባቸውን በተለይ ለፍትህ ገለፁ፡፡

ለአንባቢያን የቀረበው ይህ መጽሐፍ 304 ገፆች ሲኖሩት ዋጋው 65.80 ብር ነው፡፡ መጽሐፉ በሁሉም መጽሐፍት ቤቶች እንደሚገኝ ደራሲው ጨምረው ተናግረዋል፡፡


## አስቸኳይ ክፍት የስራ ቦታ

ፍትህ ጋዜጣ ከዚህ በታች በተመለከቱት ክፍት የስራ ዘርፎች ሰራተኞችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል

1. የህግ አማካሪ - በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው /ያላት/ እና ከ5 አመት በላይ የሰራ/ች/
2. የፅሁፍ አርታይ /ኮፒ ኤዲተር/

አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ በወጣ ባሉት አምስት የስራ ቀናቶች ውስጥ በጋዜጣው ቢሮ ማመልከት ትችላላችሁ


## የህይወት አድን ጥሪ



የ7 ዓመት ህፃን ልጃችን የታች አገጩና የላይ አፉ እየጠበቡ መጥተው አፉ በመግጠሙ ህፃኑ ምግብ እያማረው ምግብ መብላት ወደማይችልበት ውሃ መጣት እያማረው ውሃ መጣት ወደማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ለህክምና ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብንወስደውም በአስቸኳይ ወደ ውጪ አገር ተወስዶ ካልታከመ በአጭር ጊዜ ውስጥ አፉ ሙሉ በሙሉ ገጥሞ ምግብ መብላትና ውሃ መጠጣት ወደማይችልበት ደረጃ ደርሶ ህይወቱ ሊያልፍ እንደሚችል በማስንቀቅ የቦርድ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

ስለዚህ ወደ ውጪ አገር ወስዶ ለማሳከም ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺህ ብር) የተጠየቅን ስልሆነ ችግሩ ከአቅማችን በላይ ስለሆነብን ህፃን ልጃችንን አይን አይኑን እያየነው የመጨረሻ ህይወቱን የሚያልፍበትን ያን ክፉ ቀን በመጠባበቅ ላይ በመሆናችን እርስዎም አቅምዎን የፈቀደው ርዳታ በማድረግ ህፃን ልጃችንን ከመቀጠፍ እንዲያድኑልን በፈጣሪ ስም እንማፀናለን፡፡

አባቱ አክሊሉ ሙሉጌታ፡- 0912-06 98 57
እናቱ ደስታ ሟርጋ፡- 0912-39 89 05
የባንክ አካውንት 000103 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጉንችሬ ቅርንጫፍ

# ነስአ ደዌነ ወፆረ ሕማመነ ኢሳ ፶፫÷፬

ኄናግ ግርማ ክንፈ

*““...መልክና ውበት የለውም፤እነሆ አየነው፤ደም ግባት የለውም፣ ውበትም የለውም። መልኩም የተናቀ፣ ከሰውም ልጆች ሁሉ የተዋረደ፣ የተገረፈ ሰው፣ መከራንም የተቀበለ ነው፤ ፊቱንም መልሷልና አቃለሉት፣ አላከበሩትምም፡ ፡ በእውነት ደዌአችንን ተቀበለ፣ ሕማማችንንም ተሸከመ፣ እኛ ግን እንደተመታ፣ በእግዚአብሔርም እንደተቀሰፈ፣ እንደተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ፣ የደኅንነታችም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ፣ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።” ኢሳ ፶፫፥፪-፭*

ኢሳይያስ ነቢይ በትንቢት መነጽር ተመልክቶ ያስፈረው ይህ ቃል ዘመነ ትንቢቱ ተፈጽሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለድኅነተ አለም ወደ ምድር ሲመጣ የሚጠብቀውን አቀባበልና የሚቀበለውን ሕማም (መከራና ስቃይ) ያጠይቃል፡ ፡ ባለፈው ሳምንት “ሰሙነ ሕማማት” ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ተከብሮ አልፏል። ዕለተ አርብ ደግሞ የአዳም የ፭ ሺህ ፭፻ ዘመን የመርገም ኑሮ፣ የስቃይ ሕይወት ያበቃ ዘንድ የሕማሙ ቁንጮ የሆነ ስነ ስቅለቱ የተፈጸመበት የዓለም ሁሉ መድኃኒት የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳምና ልጆቹ ቤዛ ሆኖ በመልዕልተ መስቀል የዋለበት እለት ነው። እግረ መንገዴን እንኳን አደረሰን! እያልኩ ስለ ሰሙነ ሕማማት እና ተያያዥ ነገሮች አንዳንድ እንባባል።

ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ በስጋዌ በምድር ላይ ሲመላለስ የተቀበለው ጸዋትወ መከራ የሚዘከርበት ሳምንት ነው- ሰሙነ ሕማማት። ይህም ከሆሣዕና ማግስት እስከ ትንሣኤ ያለውን የአቢይ ጾም መዝጊያ ሳምንት ያጠቃልላል።

በሰሙነ ሕማማት በየእለቱ የተደረጉትን ግብራት ስንመለከት፡- **ሰኞ**፡- ጌታ ቢታንያ ከምትባል መንደር ሲወጣ ይራባል (ማር ፲፩፥፲፬)፡ ፡ ወዲያውም ቅጠሏ የለመለመች በለስ አይቶ ወደ እርሷ ቀረበ፣ ከቅጠልም በቀር ለርሃቡ ማስታገሻ ፍሬን አላገኘባትም፤ረገማት። በዚህም እለተ ሰኑይ መርገመ በለስ እየተባለች ትጠራለች።

እንደበለሷ ላያቸው አምሮ፣ ደምቀው የሚታዩ ሲጠጓቸው ግን ውስጣችን ባዶ የሆነ እልፍ ሰዎች አለን። በተለይ ደግሞ በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ፈጣሪ በጎቹን ያስማሩለት፣ ይጠብቁለት ዘንድ ያስቀመጣቸው “መንፈሳውያን” አባቶች ባማረ ቀሚስ ላያቸው አሸብርቆ (እዚህ ላይ ጥቂት ንጹኃን አማናዊ አባቶችን አይጨምርም) ውስጣቸው ግን በተንኮል የተሞላ ብዙዎች ናቸው። ከምዕመኑ እና በተለያየ መንገድ የሚሰበሰብን ንዋይ (ገንዘብ) የሚሞጨልፉ፣ አንዳንዴማ ቤተ ክህነቱ ግዙፍ የሙስና ማዕከል እስኪመስል ድረስ የሚሰርቁት በግልጽ ነው።

በዚሁ እለት ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ ሌላ ድንቅ ስራ አደረገ። ቤተ መቅደሱ ቤተ ጸሎት ቤተ አምልኮ መሆኑ ቀርቶ መሸጫና መለወጫ (ቤተ ምስያጥ) ሆኖ አገኘው። “ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት” (ማቴ. ፳፩፥፲፫) ብሎ የሚሸጡትን ገለባበጠባቸው፣ ገርፎም አባረራቸው። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ቤተ መቅደስን ስላጸዳ ሰኞ አንጽሖተ ቤተ መቅደስ ትባላለች፤ ዳግመኛም ስለ ሥልጣኑ በጸሐፍት ፈሪሳውያን ተጠይቋልና የጥያቄ ቀንም ትባላለች።

በአሁኑ ወቅትም ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ድርጊት በቤተ መቅደሱ ይፈጸማል፡ ፡ ይህንንም ለማስረገጥ በየአጋጣሚው በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሞንታርቦ የሚያስጮሁ፣ የተጧጧፈ የንግድ እንቅስቃሴ የሚያከናውኑትን መመልከት እንችላለን። በዋናነት ግን ጌታ “የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት” እንዳለ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የተሰገሰጉ የውስጥ ወንበዴዎች ህልቆ መሳፍርት (ስፍር ቁጥር) የሌላቸው ናቸው። ጌታ በደሙ የመሰረታት ቤተ መቅደስ የጸሎት ቤት መሆኗ ቀርቶ ከመንፈሳዊነት- አለማዊነትን፣ ከእምነት- ፖለቲካን፣ ከፈቃደ እግዚአብሄር-ፈቃደ ጉቦን፣ ከእግዚአብሔራዊነት- ጎሰኝነትን እንደዋነኛ አላማ ያነገቡ አያሌ ወንበዴዎች ዋሻ ሆናለች። እኒህን ነው መድኅን አለም ክርስቶስ ተመልክቶ “ቤቴን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት” ብሎ የተናገራቸው። ዳግመኛም በፍሬ የተመሰለች ሃይማኖትና ምግባርን ቢያጣባቸው በበለሷ ምሳሌነት ረገማቸው።

**ማክሰኞ**፡- ረዣዥም ትምህርቶችን በቤተ መቅደስ እየተገኘ አስተምሯል፤ ስለዚህም የትምህርት ቀን ትባላለች። የአይሁድ ሊቀ ካህናት ጸሐፍት ጌታን እንዴት መያዝ እንደሚችሉ የመከሩበት ቀን ነውና እለቱ ምክረ አይሁድም ይባላል። በምክሩ ጊዜ ይሁዳ ተገኝቷል። **ረቡዕ**፡- የመልካም መዓዛ ቀን ይባላል።ጌታ በስምዖን (ዘለምጽ) ቤት አርፎ ሳለ ዘማዊት የነበረች ባለ ሽቱዋ የተባለች ማርያም እንተ እፍረት ዋጋው ውድ የሆነ በአልባስጥሮስ ብልቃጥ የተሞላ መልካም ሽቱ ይዛ በመሔድ ጌታዋን ስለ ቀባችው ዕለቱ የመልካም መዓዛ ቀን ተብሏል። በዚህ ጊዜ ሽቶው ሦስት መቶ ዲናር ያክል ዋጋ ያለው ስለነበር ይሁዳ በቅናት ተቃጥሏል። የእንባ ቀንም ይባላል፤ማርያም እንተ እፍረት በጌታችን እግር ላይ ተደፍታ ስለበደሏ እያለቀሰች በእንባዋ እግሩን ስላጠበች (ማቴ ፳፮÷፮፣ ማር ፲፬÷፱፣ ዮሐ ፲፪÷፰)፡ ፡ ይህ እለት አይሁድ በጌታ ላይ የ‘ይሙት’ በቃ ፍርዳቸውን የፈረዱበት ቀን እንደሆነም ይነገራል።

**ሐሙስ**፡- ጸሎተ ሐሙስ ይባላል፣ (ማቴ ፳፮ ዮሐ ፲፮)። ጠላቶቹ መጥተው ሊይዙት በተቃረቡ ጊዜ ለአርአያነት፣ አንድም አምላክ ቢሆን ስጋን የተዋሐደ መሆኑን ለማጠየቅ ሲጸልይ አድሯል፡ ፡ ሕጽበተ ሐሙስም ይባላል። ጌታችን በፍጹም ትህትና ዝቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቧልና። “እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ...” (ዮሐ ፲፫÷፲፮)። የምስጢር ቀንም ይባላል ምስጢረ ቁርባንን (በመስቀል ላይ የሚቆረስና የሚፈሰውን ሥጋና ደሙን) የሰጠበት ቀን ነውና ሉቃ ፳፪÷፳፡ ፡ የነጻነት ሐሙስ ይባላል፤ ለኃጢአትና ለጥንተ ጠላት ዲያቢሎስ ባርያ ሆኖ መኖር ማብቃቱ፣ የአዳም ልጅ ሁሉ ያጣውን ክብር መልሶ ማግኘቱ “ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም...ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ” (ዮሐ ፲፭÷፲፭) በሚለው አምላካዊ ቃል ከባርነት ወደ ልጅነት የተሸጋገርንበት ዕለት ነውና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የነጻነት ሃሙስ ይሉታል። ጌታ በይሁዳ አማካኝነት ተላልፎ የተሰጠውም በዚሁ እለት አመሻሽ ላይ ነው።

በጸሎተ ሐሙስ ለዚህ ዘመን ትምህርት ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ቁም ነገሮች ከጌታ ሕማም ጋር በተያያዘ ተፈጽመዋል። ይሁዳ በመሳም ጌታውን፣ መምህሩን፣ አሳልፎ ሰጥቷል፡ ፡ በባህርይው ሃሰት የሌለበት እውነት ክርስቶስን አሳልፎ እንደሰጠው ይሁዳ ሁሉ በጎነትን መልካም ነገርን፣ መንፈሳዊነትን አሳልፈው የሚሰጡ በምዕመናን ላይ ግፍን የሚሰሩ አሉ፤ እውነትን በአደባባይ የሚሰቅሉም አሉ። ክርስቶስ በደሙ የሰጠንን ነጻነትም ሊሽሩ፣ ወደ ባርነት ሊመልሱን የሚታትሩ አሉ። ጌታ “እናንተም ለወንድማችሁ እንዲህ አድርጉ” ሲል ነበር የደቀ መዛሙርቱን እግር በትህትና ያጠበው፤ ዛሬ ግን በተቃራኒው ክርስቶሳዊውን ትተው ፖለቲካዊውን መንገድ በመምረጥ መንጎቻቸውን የሚበትኑ የሃይማኖት አለቆች ብዙ ናቸው።

**አርብ**፡- መድኃኒተ ዓለም የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ ሆኖ በመልዕልተ መስቀል ላይ ተሰቅሎ የዋለበት ቀን ነውና የስቅለት አርብ እየተባለ ይጠራል:: በሞቱ ሞትን ድል አድርገን ሕይወትን ስላገኘን እለተ አርብ መልካሙ አርብ (Good Friday) እየተባለም ይጠራል። የሕማሙ ሁሉ ሕማም፣ የስቃዩ ሁሉ ፍጻሜ የነበረው በእለተ አርብ ነው። በዚች ቀን ጌታ ስለሰው ልጆች በደል ሲል ምንም በደል ሳይኖርበት ‘ይሙት በቃ’ ተፈርዶበት ሞተ። “ነፍሱን ስለወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር ለማንም የለውም” እንዲል ቅዱስ መጽሐፍ ስለወዳጆቹ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ግርፋትን ስጋው አልቆ አጥንቱ እስኪታይ ተገረፈ፣ መጸፋትን ተጸፋ፣ ወደቀ ተነሳ፣ ምድርን አረንጓዴ ያለበሰ አምላክ ተራቆተ እርቃኑንም ተሰቀለ፣ በባህርይው የማይሞት ህያው አምላክ በለበሰው ስጋ ስለሰው ልጅ ፍቅር ሰውን ከዘላለም ፍዳ ያድነው ዘንድ ሞተ፣ የማይሞተው ሞተ። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስ “ታመመ ሞትን ከተቀበለበት ከሥጋ ጋር ተዋሕዶ በመስቀል ላይ በፈቃዱ ለስጋውያን ሞተ” ይላል፡ ፡ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ደግሞ “ምትሐት ያይደለ በእውነት ተራበ፣ ተጠማ እንጂ። ራሱን አሳልፎ ለመስቀል ሰጠ፤እጁን እግሩን ተቸነከረ፤ጎኑን በጦር ተወጋ” ሲል ሕማሙን ይገልጣል።

ጌታ ለእስራኤላውያን ወይም ለሮማውያን አልሞተም፣ ለኢትዮጵያውያን አሊያም ለግሪካውያን አልሞተም፣ ለምስራቃውያን ወይም ለምዕራባውያን አልሞተም፣ ለአማራው ወይም ለኦሮሞው አልሞተም፣ ለሚያምኑ ወይም ለማያምኑ አልሞተም፣ ለጥቁሮች ወይም ለነጮች አልሞተም፣ ይልቁንም ከመጀመርያዎቹ አዳምና ሔዋን ለተገኙ ምድርንም ለሞሉ ለሰው ልጆች ሁሉ እንጂ። ታድያ ጌታ ሳይለይ የሞተለትን የሰው ልጅ ምድራውያኑ በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በሚከተለው ሃይማኖት፣ በሚያራምደው አመለካከት ለምን አድሎን ይፈጽማሉ? **ቅዳሜ**፡- ቀዳም ሥዑር ትባላለች። ምክንያቱም ለወትሮው ጾም የማይጾምባት ቅዳሜ የጌታን መከራ በማሰብ በጾም ታስባ ስለምትውል ቀዳም ሥዑር (የተሻረችው ቅዳሜ) ተባለች። ለምለም ቅዳሜ፣ ቅዱስ ቅዳሜ እየተባለችም ትጠራለች።

አሁንም ቢሆን ጻላኤ ሰናያት የሆኑ አንዳንድ ሰዎች በተለይም ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይነት የቀረቡት ለመጥፎ ነገሮች መማክርት የሚሆኑ፣ ከሃሰት ጋር ምክር የሚቀመጡ፣ ዛሬም ጌታን አሳልፈው የሚሰጡ አሉ። የሃይማኖት አባቶችም ጌታችን ሳይሰስት ራሱን አሳልፎ እስከመስጠት የሰጠንን ፍቅር አትንፈጉን። የዳግማ ትንሳኤ በአል መልካም ይሁንልን። ያብጽሐነ ያብጽሕክሙ እግዚአብሔር በሰላም! ሰላም፣ ፍቅርና አንድነት ለአንዲት ኢትዮጵያ!!!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!

